የብሉይ ኪዳን ቀኖና

በዮሐንስ አቤል

ቴሌግራም ቻነል ..... https://t.me/ZANCHOR

ጥያቄና አስተያየት ካሎት ..... https://t.me/abesus

ማውጫ

የብሉይ ኪዳን ቀኖና

- መግቢያ ---------- 2
- የአይሁዳውያን ብልጫ 3

I. የብሉይ መፅሀፍት አመጣጥ አጠር ተደርጎ ---------- 3
II. በቤተክርስቲያን ብቻ ? ---------- 5
III. የሰይጣን ማህበር ? ---------- 5
IV. የተለያዩ የአይሁዳውያን ማህበረሰብ - የተለያየ አቋም ? ---------- 7
V. ብዙ ቁጥር ያለው የእስክንድርያው ቀኖና ? ---------- 11

- የሰባ ሊቃናቱ ትርጉም | Septuagint 13

I. የሰባ-ሊቃናቱ ትርጎሜ ምክንያቱና ውጤቱ ---------- 13
II. ሰባ-ሊቃናቱና 7ቱ መፅሃፍት ---------- 14
III. የሙት ባህር ጥቅልሎች - The dead sea scroll ---------- 15
IV. የማዞሬቲኩ ቴክስት - Masoretic Text ---------- 15

- ምንጭ ከአይሁድ 17

I. ፊሎ - Philo of Alexanderia ---------- 17
II. ዮሴፍ ወልደ ቆርዮን - Flavius Josephus ---------- 17
III. የጀምኒያው ጉባ - Council Of Jamnia ---------- 20
IV. የዝምታው ዘመን ---------- 20
V. የሶስትዮሽ አቀማመጥ - Jews Traditional Threefold Structure ---------- 25

- የቤተክርስቲያን ታሪክ በቀኖና ላይ | Church History 27

1. ጉባኤያት | Church Councils ---------- 27
II. በቤተክርስቲያን አባቶች ቀጥታ የተቀመጡ ዝርዝሮች - Lists ---------- 30
III. የቤተክርስቲያን አባቶች አጠቃቀም - Quotations ---------- 40

- ጥያቄዎችና መልሶቻቸው 46

1. ይሁዳ 14-15 ---------- 46
II. ማቲዎስ 27:9 ---------- 47
III. የቃየን ሚስት ከየት መጣች ? ---------- 50

መግቢያ

ዛሬ በእጃችን ላይ የሚገኘው የአምላክ እስትንፋስ ብለን የምንቀበለው መፅሐፍ ቅዱስ (66ቱ) ድንገት ከሰማይ የወረደ ወይም በሆነ ተአምር እዚ የተገኘ ነገር አይደለም! እግዚአብሔር ለመረጣቸው ህዝብ ለአይሁዳውያን የፍጥረትን ታሪክና የሚኖሩበትን ህግጋቶች ገና ከጥንት በሙሴ በኩል ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ከዚያም በሌሎች ቅዱሳን እየተፃፈ የቀጠለ ነበር። ብሉዩ በባለቤቶቹ አይሁዳውያን ተቀዳጅቶ የተቀመጠ ሆኖ ሀዲሳት ደግሞ በሐዋርያት ተፅፈው በቤተክርስቲያን ተለይተውና ተበጥረው ወጥተው ዛሬ የያዝነውን መፅሀፍ ሆኑ!

ዛሬ ላይ በክርስትና ውስጥ በመፅሀፍ ቅዱስ ቀኖና ዙሪያ የተለያየ አመለካከትና አቀባበል እንዳለ እሙን ነው። በካቶሊክ ቤተክርስቲያን 73 መፅሀፍት ቀኖናዊ ተደርገው ይወሰዳሉ ፤ በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን 81 መፅሀፍት ቀኖናዊ ተደርገው ይወሰዳሉ ፤ በፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን 66 መፅሀፍት ቀኖናዊ ተደርገው ይወሰዳሉ ። የምስራቋ ኦርቶዶክስ 76 መፅሀፍትን ቀኖናዊ አድርጋ ትቀበላለች ፤ ይህ አቋሟ ከምታዘነብልበት አጋር ቤተክርስቲያን እነኚህም ከግሪክና ከጆርጂያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አንፃር ሊጨምርም ሊቀንስም ይችላል። በክርስቶስና እምነት ውስጥ ያሉት ዋነኛ ምልከታዎች እነኚህ ናቸው።[1] የመፅሀፍ ቅዱስ ቀኖና ቁጥር በዚህ መልኩ የተለያየው ወይም ልዩነቱ የመጣው በዋነኝነት በብሉይ በጥቂቱ ድግሞ በሀዲሳት መፅሀፍት ብዛትና አይነት ላይ እነዚህ የእምነት ክፍሎች ባላቸው የተለያየ አቀባበል ነው። ይህ የቀኖና ጉዳይ ዛሬ ላይ በሁላችን እጅ ገብቶ በቀላሉ ማግኘትና ማንበብ እንደምንችለው እንዲህ በቀላሉ አልተዋቀረም። በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የአምላክ እስትንፋስ የሆኑ መፅሀፍትን ለመለየት የተሄደው ሂደት ቀላልና የጠራ ሳይሆን እጅግ ውስብስብና ብዙ ውዝግቦች (controversies) ያሉበት ነው። ለረዥም ዘመናትም ጥያቄ ሆኖ የዘለቀ ፤ አሁንም ድረስ የመለያየት ምክንያት የሆነ ጉዳይ ነው። ነጥለን በብሉያት ቀኖና ላይ ስንመለከት ደግሞ ጉዳዩ የቤተክርስቲያን ብቻ ሳይሆን መፅሀፍቶቹ የተቀዱባቸው የአይሁዳውያንን አቋም በዋነኝነት መመልከትን ስለሚያካትት ይህ ርዕሱን እጅግ ሰፊና ይበልጥ አወዛጋቢ (Controversial) ያደርገዋል። ነገር ግን ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ለዛሬው መፅሀፍ ቅዱሳችን ብዛትና አይነት ከላይ ከተዘረዘሩት የተለያዩ ምልከታዎች ውስጥ የቱኛው ይበልጥ ምክንያታዊና ተአማኝነት ያለው ነው የሚለውን ለማወቅ መሠረት የሚሆነን በዚህ ጉዳይ ላይ የሚካተቱ የትኛውንም ታሪካዊ እውነታዎችን ሁሉ ያማከለ ግንዛቤና አስተውሎት ሲኖረን እና ሁሉን ወዳማከለ ድምዳሜ መድረስ ስንችል ነው። በዚህ ርእስ ላይ ብዙ ልሂቃን ብዙ አጥነተዋል ብዙ መፅሀፍትም ተፅፈዋል። በዚህም አጭር መፅሀፍ ያለውን የዘመናት እጅግ ሰፊ ሀሳብ ጨርሶ ማቅረብ ማይታሰብ ነው። ነገር ግን በቀኖና ዙሪያ ሊታወቁ የሚገቡና መሠረት የሚሆኑ ዋነኛ ጭብጦች በዚህ ይቀርባሉ።

በዚህ መፅሀፍ በጥልቀት ለመመልከት የምንጥረው በዋነኝነት ልዩነት የመጣባቸው በብሉያት ውስጥ ያሉትን መፅሀፍት እንዴት ነው መቀበል ያለብን ፤ ያላቸው ድርሻ ምንያህልና እስከምን ድረስ ነው መሆን ያለበት በሚለው ላይ ነው። ይህን ስናጠና ምንመለከታቸው እጅግ ብዙ አስፈላጊና ወሳኝ የሆኑ እውነታዎች ይኖራሉ። በተቻለ አቅምም ማንኛውም ከዚህ ጋር የሚገናኙ ነጥቦችን ለመዳሰስና ሁሉን ወዳማከለ ድምዳሜ ለመድረስ እንሞክራለን። እነዚህ መፅሀፍት የአምላክ እስትንፋስ ናቸው ? መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ አስገብተን መቀበል አለብን ? ስለምንስ በኛ የወንጌላውያን አማኞች ቤተክርስቲያን እነኚህን መፅሀፍት እንደ አምላክ እስትንፋስ አንቀበላቸውም ? የወንጌላውያን አማኞች ቤተክርስቲያን ? የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ ልናውቃቸው ከሚገቡ መሠረታዊ ነጥቦች ጋር በማብራራት እንመለከታለን! ሊነሱ የሚችሉ ሙግቶችንም መልሰን እንሞግታለን!

[1] Anke Wanger , The Biblical Canon of the Ethiopian Orthodox Tewahdo Church , P 2

የአይሁዳውያን ብልጫ!

የአይሁዳውያን ታሪክ ከአብርሀም በእግዚያብሄር መጠራት ጀምሮ የሚመዘዝ ነው። በዘፍጥረት 12 ላይ እንደተዘገበልን እግዚአብሔር አብርሀምን መርጦ ታላቅ ሕዝብም እንደሚያደርገው ቃል ገብቶለት ከወገኑ ፤ ከቤተሰቡና ከሀገሩ እንዲወጣና እርሱ ወደሚያሳየው ምድር እንዲሄድ አዞት ነበር። የእስራኤል ታሪክም ከዚህ የሚጀመር ነው ፤ እነርሱም ከአብርሀም የልጅ ልጅ ከያዕቆብ የወጡ 12ቱ ነገዶች ናቸው (ዘፍ 35፡22)። እነዚህ ህዝቦች በእግዚያብሄር የተመረጡ ህዝቦች ናቸው። ከመጀመርያው ጊዜ አንስቶም እግዚአብሔር እንደቃሉ ሲጠብቃቸው ፤ ሲታደጋቸው ፤ አብሯቸውም ሲቆም ነበር። ከግብፅ ከወጡ በኋላም ይመሩበትና ይኖሩበት ዘንድ ሕግና ስርአትን ቀጥታ በሙሴ በኩል ሰጧቸዋል። ሙሴ ከሞተ በኋላም የእርሱን ቦታ ተክቶ ኢያሱ ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥታ በመነጋገር ለህዝቡ መልእክትን ሲያደርስና የእግዚአብሔርን ፍቃድ ሲፈፅም ነበር። በዚህም መልክ እግዚአብሔር ለረዥም ዘመናት ለመረጣቸው ለአይሁዳውያን በተለያየ መንገድ ሲገለጥና ሀሳቡን ሲያስታውቅ ነበር። ሕግና ስርአትን ሲሰጣቸው ደግሞ ተገዝተውለት እንዲኖሩና ለልጅ ልጆቻቸውም እንዲያስተምሩ አዟቸዋል።

“እግዚአብሔር፦ ሕዝቡን ወደ እኔ ሰብስብ፥ በምድርም በሕይወት በሚኖሩበት ዘመን ሁሉ እኔን መፍራት ይማሩ ዘንድ፥ ልጆቻቸውንም ያስተምሩ ዘንድ ቃሌን አሰማቸዋለሁ ብሎ በተናገረኝ ጊዜ፥ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት በኮሬብ በቆምህበት ቀን ዓይኖችህ ያዩትን ነገር እንዳትረሳ፥ በሕይወትህም ዘመን ሁሉ ከልብህ እንዳይወድቅ ተጠንቀቅ፥ ነፍስህንም በትጋት ጠብቅ፤ ለልጆችህም ለልጅ ልጆችህም አስታውቀው።”

— ዘዳግም 4፥9-10

“ 6 እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። 7 ለልጆችህም አስተምረው፥ በቤትህም ስትቀመጥ፥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሣም ተጫወተው። ”

— ዘዳግም 6፡6

ሙሴ ይህንን ሕግጋቶች ቀጥታ ከእግዚአብሔር እንደተቀበለው(ዘፀ 24:3) ፤ በመፅሀፍም ትእዛዛቱን እንዲፅፍ እንደታዘዘ (ዘፀ 34:4 , 27) ፤ ከዚህም በዘለለ አስርቱ ትእዛዛት የተፃፉት በእግዚአብሔር እንደሆነ (ዘፀ 34:1 , ዘዳ 4:13 , 10:4) በአይሁዳውያን ዘንድ ይታመናል። ከዚህም በዘለለ አምስቱን የመጀመሪያ የመፅሀፍቅዱስ መፅሀፍት (Pentateuch) ሙሴ እንደፃፋቸው ይታመናል። የዘዳግም መፅሀፍ የመጨረሻ ክፍሎች በኢያሱ እንደተፃፉ ብዙ ልሂቃን ይናገራሉ። የዚህም ምክንያት በዚህ መፅሀፍ የሙሴ ሞት የተዘገበ ስለሆነ ነው። ከዚህ ከሙሴ አገልግሎት አንስቶም የነብያት አገልግሎት በእስራኤል መሀከል ይገለጥ ነበር! ሙሴ እንደሞተም እርሱን የተካው ኢያሱ ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥታ ይነጋገር የነበረ ሲሆን መፅሀፍንም ከትቧል።(ዘፍ 24 : 26) በአይሁድ እምነት መሠረትም ከሙሴ መፅሀፍትና ከኢያሱ ቀጥሎ የሚመጣው መሳፍንት በሳሙኤል የተፃፈ እንደሆነ ይታመናል። ነገር ግን በዚህ ሰአት ልሂቃን የመሳፍንት መፅሀፍት ከሳሙኤል በፊት በነበረ ነብይ ግለሰብ የተፃፈ

እንደሆነ ይናገራሉ።[2] ይሄው የነብያት መፅሀፍትን የመፃፍ አገልግሎት በሳሙኤልም የቀጠለ ነበር። (1ኛ ሳሙ 10:25 ፤ 1 ዜና 29:29) በዚህ ጊዜም በነብያት የሚፃፉ እጅግ ብዙ ፅሁፎች ታሪካዊ ነበሩ ፤ እነዚህም ለዜና መዋእል መፅሀፍ መሠረት ሆነዋል። {1ዜና 29:29 ፤ 2ዜና 9:29 ፤ 2 ዜና 12:15 ፤ 2ዜና 13:22 ፤ 2 ዜና 20:34 ፤ 2 ዜና 26:22 ፤ 2 ዜና 32:32 ፤ 2 ዜና 33:18 } የሳሙኤልና የነገስት መፅሀፍም ከዜና መዋዕል ጋር ብዙ መረጃዎችን ይጋራሉ። ከዚህ በኋላም የተነሱ ከእግዚአብሔር ጋር በመነጋገርና መልእክትን ለእስራኤል ሲያደርሱ የነበሩ ነብያት መፅሀፍትን ፅፈዋል። {ኢሳ 30:8 ፤ ኤር 25:13 ፤ ኤር 29:1 ፤ ኤር 30:2 ፤ ኤር 36: 1-32 ፤ ሕዝ 43:11 ፤ ዕም 2:2 ፤ ዳን 7:1 ፤ 2 ዜና 21:12} መዝሙራትም በብዛት በዳዊት የተፃፉ ሲሆን የሌሎች አካትም ፅሁፍ ውጤት ነው። ለምሳሌ መዝሙር 90ን የከተበው ሙሴ ነው! በአይሁድ መሀከልም ይዘመሩ ነበር። የምሳሌም መፅሀፍ የረዥም ዘመናት የተለያዩ አካላት የጥበብ ንግግሮችን የያዘ እንደሆነ ይነገርለታል። በብዛትም ሰለሞን የፅሁፍ ከታቢ ሲሆን ሌሎች ብዙዎችም በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ተካተዋል። በዚህ መንገድ የብሉይ መፅሀፍት በእግዜር ምሪትና አነሳሽነት ተፅፈው እጅግ ረዥም ዘመናትን ተሸጋግረዋል። በዚህም የሙሴ አምስቱ መፅሀፍት ከክርስቶስ ልደት ከ5 ክፍለ ዘመን በፊት አንስቶ በመላው አይሁዳውያን ዘንድ እንደ አምላክ እስትንፋስ ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር ፤ የነብያት መፅሀፍት ተብለው በአይሁድ የተከፈሉት መፅሀፍትም በሶስተኛው ክፍለ ዘመን ውስጥና ከዚያም በስቲያ በአይሁድ ዘንድ በአምላክ ቃልነት ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር ፤ እንዲሁም ፀሀፍት ተብለው የተከፈሉት የመጨረሻው ክፍል መፅሀፍትም ከክርስቶስ ልደት በፊት በሶስትና በሁለተኛ ክፍለ ዘመን እስከዛም ድረስ በእስትንፍሰ አምላክነት ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር።

የረዥም ዘመናት ውጤት የሆነው የብሉይ መፅሀፍት አመጣጥ አጠር ተደርጎ ከላይ እንደቀረበው አይሁዳውያን ከመጀመሪያው አንስቶ በእግዚአብሔር ተመርጠው ፤ ከዛም በእግዚአብሔር ምሪት ይጓዙ እንደነበር በዚህም ውስጥ ደግሞ እግዚአብሔር በዘመናት ልዩነት ሕግጋቱን ስርአቱንና መልእክቱን በተለያዩ መልእክተኞቹ (ነብያት) እያሳወቀ ፤ ፅፈው ያስቀምጡትም ዘንድ እያሳሰበ እንደዘለቀ እንረዳለን። እስራኤላውያንም ደግሞ ይህንን የእግዚአብሔርን ሕግ ፤ ስርአትና መልእክት በመፅሀፍት ከትበው በልባቸውም ይዘው ፤ ልክ እንደታዘዙትም ለልጅ ልጆቻቸው በጥብቅ በማስተማርና ለትውልድ በማስተላለፍ ለዚህን የብሉይ መፅሀፍ እንዲህ መዋቀር ትልቅና ወሳኝ ሚና እንደተጫወቱ መመልከት ይቻላል። ይህ እርግጥ ከሆነ ያለምንም ጥርጥር እነዚህ ህዝቦች መፅሀፍትን ከእግዚአብሔር ተቀብለው ጠብቀው ካስተላለፉ ስለነዚህ መፅሀፍቶቻቸው ጠንቅቀው የሚያውቁ ናቸው ማለት ነው። የቱኞቹ መፅሀፈት ከአምላክ የተሰጧቸው እንደሆነ የቱኞቹ መፅሀፈት ከአምላክ የተሰጧቸው እንዳልሆኑ ያውቃሉ። ስለዚህ ደግሞ መፅሀፍቅዱስ ራሱ በተደጋጋሚ ያሳውቀናል።

- መዝሙር 147 1ቃሉን ለያዕቆብ፥ ሥርዓቱንና ፍርዱን ለእስራኤል ይናገራል። 2 ለሌሎች አሕዛብ ሁሉ እንዲህ አላደረገም፥ ፍርዱንም አልገለጠላቸውም።

- መዝሙር 78 5 ለልጆቻቸው ያስታውቅ ዘንድ፥ ለአባቶቻችን ያዘዘውን ምስክር በያዕቆብ አቆመ፥ በእስራኤልም ሕግን ሠራ፤ 6 የሚመጣ፥ ትውልድ የሚወለዱም ልጆች ያውቁ ዘንድ፥ ተነሥተው ለልጆቻቸው ይነግራሉ፤ 7 ተስፋቸውን በእግዚአብሔር እንዲያደርጉ፥ የእግዚአብሔርንም ሥራ እንዳይረሱ፥ ትእዛዙንም እንዲጠብቁ ።

- ሮሜ 3 1 እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድር ነው ? ወይስ የመገረዝ ጥቅሙ ምንድር ነው? በሁሉ ነገር ብዙ ነው። 2አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃላት አደራ ተሰጡአቸው።

[2] Oxford Bible Dictionary , 167

- ሮሜ 9 ⁴እነርሱ እስራኤላውያን ናቸውና፥ ልጅነትና ክብር ኪዳንም የሕግም መሰጠት የመቅደስም ሥርዓት የተስፋውም ቃላት ለእነርሱ ናቸውና፤ ⁵ አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና፤ ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ፥ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን።

- ኢሳይያስ 2፥3 “ ሕግ ከጽዮን የእግዚአብሔርም ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣልና ብዙዎች አሕዛብ ሄደው፦ ኑ፥ ወደ እግዚአብሔር ተራራ፥ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ፤ እርሱም መንገዱን ያስተምረናል፥ በጎዳናውም እንሄዳለን ይላሉ።”

እንግዲህ የብሉይ መፅሀፍትን ብዛትና አይነት ለማወቅ በምናደርገው ጥረት እነዚህ መፅሀፍቶች በጠቅላላ የአይሁዳውያን ናቸውና ፤ እነርሱም ደግሞ የረዥም ዘመናት ባለቤትነትና እውቀት አላቸውና ከሁሉ አስቀድመን በዋነኝነት መፅሀፍቱ ዙሪያ ያላቸውን አቋም መመልከት ይጠበቅብናል። ይህ ከሁሉ በፊት ማወቅና መገንዘብ ያለብን ትልቅ ነገር ነው። ከላይ እንዳየነው የብሉይ መፅሀፍት እንዲሁም መካተት አለባቸው ወይም የለባቸውም ተብለው ልዩነት የፈጠሩት መፅሀፍትም ሳይቀሩ የአይሁድ ባለቤትነት ያላቸው ስለሆኑ እስትንፋሰ አምላክ የሆኑትን መፅሀፍት ብዛትና አይነት ለመወሰን እነኚሁ አይሁዳውያንን መመልከትና ባላቸው እምነት መሠረት ማድረግ አማራጭ የሌለው ግዴታችን ነው። በርግጥ በዚህ ዙሪያ ታሪክን ስናጠና ከቤተክርስቲያን ታሪክ በስተቀር (እርሱም ቢሆን ከአይሁድ ተፅእኖ አያመልጥም) ዋነኝነት ልናገኝ የምንችለው ቀንደኛ ማስረጃ ፤ ሁሉም ማለት በሚቻል መልኩ ከአይሁዳውያን ከራሳቸው ነው!

በዚህ ላይ አንዳንዶች የመፅሀፍቱ ብዛትና አይነት መወሰን ያለበት በአይሁዳውያን ሳይሆን በቤተክርስቲያን ብቻ ነው ይላሉ። በርግጥ በሀዲሳት መፅሀፍት ላይ የቀኖናን ውሳኔ ልትሰጥ የምትችለው ቤተክርስቲያን ነች! ነገር ግን አሁን የምናወራው ስለብሉያት መፅሀፍ እስከሆነ ድረስ ‘ብቻ’ በሚል ቃለ እጅግ ተለጥጦ የተዋቀረው ይህ አመለካከት ስህተት ነው! ምክንያቱም ከላይ እንደተገለፀው እነዚህ መፅሀፍት የፃፉት ፤ ቀጥታም አደራ ተሰቷቸው ጠብቀው የቆዩት አይሁዳውያን ናቸውና የቱኞቹ መፅሀፍት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣቸው እንደሆነ ፤ የቱኞቹ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል አይደሉም የሚለውን የሚያውቁ ናቸው። ቤተክርስቲያን ይህን ከነሱ ትቀበላለችጂ በነርሱ ዘንድ የማይታወቅን አዲስን ቀኖና ልትቀንና ልታስቀምጥ አትችልም። በተጨማሪም የብሉይን መፅሀፍት ብዛትና አይነትን ቤተክርስቲያን ልትወስን ስልጣን እንዳላትም የሚያሳይ ምንም መፅሐፍቅዱሳዊ መሠረት የለም! ይህ ከሁሉ በፊት መገንዘብ የሚገባን መሠረታዊ ነጥብ ነው!

በተጨማሪም ይህን የአይሁዳውያንን ብልጫ አፅንኦት ሰተን ስንናገር አንዳንዶች የሚያነሱት ሌላ የሙግት ሀሳብ አለ ፤ ይህም ሀሳብ ባጭሩ ሲገለፅ እንዲህ የሚል ነው :-" ክርስቶስ በ30 አመቱ አገልግሉት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ አይሁዳውያን ሲቃወሙትና ሊገሉትም ሲፈልጉት እንደነበር እርግጥ ነው! ይህ ተቃውሞ ደግሞ ከትንሳኤው በኋላም ክርስቶስን ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ ተከታዮች ክርስቲያኖችን ጨምሮ የቀጠለ ነበር! ይህ የአይሁዳውያን የክርስቶስ ተቃዋሚነት ደግሞ በመፅሀፍ ቅዱስም የተመዘገበ ነው! ይህ እርግጥ ከሆነ ከክርስቶስ መገለጥ በኋላ የመጡት አይሁዳውያን ባስቀመጡት ነገር መታመን የለብንም! "

ይህ የሙግት ነጥብ አይሁዳውያን የክርስቶስ ተቃዋሚ መሆናቸው ላይ መሠረት አርጎ የሚያውጠነጥን ነው! በዚህ ላይ ቀደም ተብሎ ፥ ይህ የአይሁዳውያን ተቃውሞ መሠረቱ ምንድነው? ወይም ፥ ለምን ተቃወሙ ? ፥ የሚለው ጥያቄ መጠየቅ አለበት ! በዚህ ሰአት ከሁሉ በፊት እርግጠኛ ሆነን መናገር የምንችለው አንድ ነገር አለ! ይህም ኢየሱስ በየትኛውም ዘመን ወደዚች ምድር በስጋዌ ቢገለጥ ፥ አይሁዳውያን ለኢየሱስ የሚሰጡት ተመሳሳይ የሆነ የተቃውም ምላሽ እንደሆነ ነው! ከማርያም ከመወለዱ ከብዙ አመት በፊት (ምናልባትም

ከ100- 200 አመታት) ቀድሞ ቢመጣም ፤ አልያም ደግሞ ከተወለደበት ዘመን አልፎ ብዙ አመታትን ቆይቶ (ምናልባትም ከ100- እስከ ዛሬ ድረስ ባለው ዘመናት ውስጥ) ቢመጣም ፤ በየትኛውም ዘመን ቢገለጥ ፥ አይሁዳውያን በመጣበት ጊዜ የተቃወሙትን ተመሳሳይ ተቃውሞ በሱ ላይ እንደሚያደርሱ እርግጥ ነው! ይህንን እርግጠኛ የሚያደርገን ደግሞ አይሁዳውያን በዘመናቸው ሁሉ መሲሑን ይመጣል ብለው ይጠብቁ የነበረበት አጠባበቅ ኢየሱስ ይመጣበት ከነበረው አመጣጥ አንፃር ፍፁም በተቃራኒ መንገድ መሆኑ ነው! ይህን ነገር ዛሬም ድረስ በአይሁዳውያን ዘንድ የምንመለከተው እውነት ነው! ስለዚህ ከዚህ ምንረዳው ነጥብ የአይሁዳውያን ተቃውሞ ዋነኛ ምክንያትና መሠረት በመሲሁ ላይ ያላቸው የተሳሳተ አጠባበቅ እንደሆነ ነው! ከላይ በሙግት ሀሳቡ ከተነሳው ጭብጥ አንፃር ይህ መታወቅ ያለበት ምክንያት አይሁዳውያንን በዘመን ልዩነት ከፋፍለን የሆኑትን የክርስቶስ ተቀባይ ሌሎቹን ተቃዋሚ አድርገን ማስቀመጥ ስህተት እንደሆነ ለማስገንዘብ ነው!

ይህ እውነት እንዳለ ሆኖ አይሁዳውያን ክርስቶስን በምድር በነበረበት ጊዜ ቢቃወሙትም ፤ እንደውም ክርስቶስንም ሆነ ሐዋርያቱን ለመግደል እስከመፈለግና እስከመግደል ቢደርሱም ፥ በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን በሁለቱ መሀከል በብሉይ በመፅሐፍት ብዛትና አይነት ዙሪያ ልዩነትና አለመግባባት አልነበረም ፤ እንደነበረም ሊያስረግጥልን የሚችል መፅሀፍ ቅዱሳዊም ሆነ ታሪካዊ ማስረጃ አልተመዘገበልንም። እንደውም በመፅሀፍ ቅዱስ ከተነገሩን እውነታዎች ተነስተን ልንሰጥ የምንችለው ድምዳሜ በዚህ ጉዳይ ተመሳሳይ አቋም እንዳላቸው ነው። ለምሳሌ ኢየሱስ ከአይሁዳውያን ጋር ሲነጋገር እየጠቀሰ ሲሞግትባቸው የነበሩት መፅሀፍት Already በራሳቸው በአይሁዳውያን ዘንድ ተቀባይነት የነበራቸው መፅለፍት ነበሩ። "መፅሃፍትን ትመረምራላችሁ እነሱም ስለኔ የሚመሰክሩ ናቸው" እያለ ፤ ከዚህም አልፎ በተለያየ ስፍራ ከመፅሀፍቶቻቸው እየጠቀሰ አላነበባችሁምን? በሚል ጥያቄያዊ ሙግት በእጃቸው የያዙትን መፅሀፍት ለራሱ መሲህነት ማስረገጫ አርጎ ይጠቀም ነበር። ይህ ሁሉ የሚያረጋግጥልን ምንምኳ አይሁዳውያን ተቃዋሚዎቹ ፤ ከዛም አልፎ ገዳዮቹም ጭምር ቢሆኑም በያዙት የብሉይ መፅሀፍት ብዛትና አይነት ዙሪያ ግን ይህ ርዕሰ ጉዳይ ሆኖ ተነስቶ በመሀከላቸው አለመግባባትና ልዩነት እንዳልነበረና እንደውም ይልቁኑም ኢየሱስና አይሁዳውያን አንድአይነት የመፅሀፍት አቀባበል እንደነበራቸው ነው። በዚህ ላይ እውቁ ብሩስም (F.F. Bruce) ሲናገር እንዲህ ይላል

" When we think of Jesus and his Palestine apostles , then we may be confident that they agreed with contemporary leaders in Israel about the content of the can-on. ... when in debate with Jewish theologian Jesus and the apostles appealed to an authority which was equally acknowledged by their opponent. "[3]

በኢየሱስና በሐዋርያቱ ዘመን ያሉትን ብቻም ሳይሆን ከዛ በኋላ የመጡትን አይሁዳውያንንም ብንመለከት ምንምኳ በተመሳሳይ ልክ ክርስቲያኖችን የሚቃወሙ ቢሆኑም ከዚህ ተንተርሰን ፥ አባቶቻቸው የተጠቀሙባቸውንና በትውልድ ሰንሰለት ወርዶ እነሱ ጋር የደረሰውን መፅሐፍት ብዛትና አይነት አያውቁም ወይም ጥለዋል ፥ ለማለት የሚያስችለን መሠረት የለንም። ይህንንም የሚያስረግጥ አንድም ማስረጃ የለም። ስለዚህ ይህ የሙግት ሀሳብ መቃረኒያ ምክንያት ብቻጂ ፤ ከሚወራው የብሉይን መፅሀፍት ብዛትና አይነት ከነሱ

3 F.F. Bruce , The Canon Of Scripture , p 48

ከመቀበል ሂደት ጋር አግባብ የሆነ ግንኙነት የሌለው ሙግት (Irrelevant) ነው። ስለዚህ የየቱም ጊዜ ይሁን የአይሁዳውያንን እምነትና አመለካከት ዳሰን መመልከት ግዴታችን ነው!

ከላይ በመግቢያችን እንደተመለከትነው ቀኖና ክስተት ሳይሆን የዘመናት ሂደት ውጤት ነው! የአምላክ እስትንፋስ የሆኑትን መፅሀፍት ለመለየትና ለማወቅ እጅግ በጠነከረ የፅሁፍና {Written} የቃል {Oral} ባህላቸው ለዘመናት ጠብቀው ያቆዩልንን የመፅሀፍቱን ባለቤቶች የአይሁዳውያንን አቋም መመልከት እንዳለብን አፅእኦት ሰተን ተመልክተናል። ይህን ስንል አንዳንዶች በአይሁዳውያን ማህበረሰብ ዘንድ የተለያዩ ወገኖች {sects} መኖራቸውንና እነዚህም ወገኖች (sects) የተለያየ አቋም እንደነበራቸው በማንሳት 'የአይሁዳውንን አቋም መመልከት አለብን!' የሚለውን ሀሳብ ለማጣጣልና ለመሞገት ይሞክራሉ።

በአይሁዳውያን መሀከል በዋነኝነት ሶስት ማህበረሰቦች አሉ። የአይሁድ ታሪክ ፅሀፊው ጆሴፈስ እነዚህ ሶስት ማህበረሰቦች ፈሪሳውያን ፤ ሰዱቃውያንና ኢሲን እንደሆኑ ይነግረናል።[4] እነዚህ ማህበረሰቦች በመፅሀፍት ይዘታቸው ያላቸውን አቋም ስንመለከት ልዩነት ነበራቸው ወደሚመል ድምዳሜ የሚያደርሰን መሠረት የለንም! ከላይ የተነሳው ሙግት መሰረት አድርጎ የሚሞግተው ፈሪሳውያን የሶስትዮሹን የመፅሀፍት አቀማመጥና ብዛት ይቀበላሉ ፤ ሰዱቃውያን አምስቱን መፅሀፍት ብቻ ይቀበላሉ ፤ ኢሲን የተባሉት ከአይሁድ ማህበረሰብ ተገንጥለው በቁምራን ዋሻ ሰፍረው የነበሩትና ትንሽ ቁጥር ያላቸው ወገኖች (Sects) ደግሞ ከሁሉም ማህበረሰብ የሚበልጥንና ዛሬ ላይ በ81ዱ ወይም በ73ቱ ውስጥ ብቻ ያሉትን መፅሀፍት ጨምረው ይቀበላሉ ከሚል ግምታዊ እሳቤ በመነሳት ነው! ነገር ግን ይህ እይታ በዚህ ሰአት በModern Scholarship ውስጥ ተቀባይነት የሌለውና ብዙ ቁጥር ያላቸው ልሂቃንም የማይዙት እሳቤ ነው። የፈሪሳውያን አቀባበል መላው አይሁድን ሊወክል የሚችል ጥያቄ የማይነሳበትና ግልጥ አቀባበል የሆነ ስለሆነ በሰዱቃውያንና በኢሲን ላይ የሚሰጠውን ከላይ ያየነውን እይታ እንመልከት።

- **<u>ሰዱቃውያን</u>**

አምስቱን የሙሴ መፅሀፍት {Pentateuch} ብቻ እንደሚቀበሉ ለተደረሰበት ድምዳሜ የሚቀርቡት ማስረጃዎች በዋነኝነት አራት ሲሆኑ እጅግ ደካናማና በጭራሽ ወደዚህ ድምዳሜ የማያስደርሱ ናቸው። አንድ በአንድ እንመልከታቸው!

1 - ሰዱቃውያን ትንሳኤን አይቀበሉም! በነብያትና መፅሀፍት ላይ ደግሞ ትንሳኤ በግልጥ ተብራርቶና ተገልፆ ይገኛል። (ኢሳ 26:19 ፤ ህዝ 37:1-14 ፤ ዳን 12:2) ስለዚህ የሙሴን አምስት መፅሀፍት ብቻ ነው ሚቀበሉት!

ነገር ግን ከዚህ በተቃራኒ ሂፖሊተስ[5] ስለትንሳኤው የተነገሩትን ክፍሎች ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ (in non-literal Manner) እንደሚያብራሯቸው ይነግረናል። ከዚህ በዘለለ ደግሞ በዚሁ የሙግት አወቃቀር መንገድ መልሰን ሰዱቃውያን በመላእክት ላይ እምነት ስለሌላቸውና በሙሴ አምስቱ መፅሀፍት ላይ ደግሞ በተደጋጋሚና በብዛት የመላእክት አገልግሎት ተገልፆ ስላለ የሙሴን መፅሀፍት ራሱ አይቀበሉም ነበር ወደሚል ድምዳሜ ልንደርስ ነው ማለት ነው። ስለዚህ ይህ የሙግት መንገድ ካለው መረጃ አንፃር የማይዛመድ ድምዳሜ በመስጠት የተሳሳተ አካሄድ ነው።

[4] The wars of jews, Bk. 2, chap 8 , no 2

[5] በሁለተኛ ክፍለ-ዘመን የነበረ ክርስቲያንና የስነ-መለኮት አዋቂ ነው!

2 - ኢየሱስ ከሰዱቃውያን ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ትንሳኤን ተቃመው ሲሞግቱት መልሶ የሞገታቸው ይህን ሊያስረግጡለት የሚችሉ እጅግ ብዙ የነብያትና የፀሀፍት ክፍል ባሉበት እሱ ግን የሙሴን አምስቱን መፅሀፍት መርጦ ከነሱ በመጥቀስ ነው! (ማር 12:18-27) ስለዚህም ኢየሱስ ይህን ያደረገው ሰዱቃውያን የሙሴን መፅሀፍት ብቻ ቢቀበሉ ነው!።

ይህም ሙግት ወደተደረሰበት ድምዳሜ የሚያስደርስ አቅም ያለው አይደለም። የሙሴ አምስቱ መፅሀፍት በመላው የአይሁድ ማህበረሰብ ዘንዳ ወሳኝና ቀንደኛው የመፅሀፍቅዱስ ክፍል ነው። ስለዚህ ሰዱቃውያኑ ከዚህ ጠቅሰው ሲሞግቱት ኢየሱስም በነሱ አካሄድ ሀሳባቸውን ያስረግጥልናል ብለው ጠቅሰው ከሞገቱበት ከዛው መፅሀፍ ጠቅሶ ታድያ ይህንንስ እንዴት አላነበባችሁም በሚል መጠይቅ ሙግታቸውን ከንቱ አደረገ። ይህ በጭራሽ የሙሴን መፅሀፍት ብቻ ይቀበሉ ነበር ወደሚል ድምዳሜ አያስደርስም። በዚህ ላይ N.R.M De Lange የተባለ ልሂቅም የነብያትንና የፀሀፍትን መፅሀፍ የሚቀበሉ የአይሁድ ራባዮች ራሳቸው የትንሳኤን ሀሳብ ለማስረገጥ ከነብያትና ከፀሀፍት መፅሀፍት ይልቅ የሙሴን መፅሀፍት ይጠቀሙ እንደነበር ያስቀምጣል።[6]

3 - ጆሴፈስ ስለሰዲቃውያውን "ከህጉ (Pentateuch) ውጪ ሌላ ምንም አይነት ነገር ይዘው እንደማይመለከቱ" አስቀምጧል።[7]

ይህን ክፍል ነጥለን ከመውሰድና ወደ ድምዳሜ ከመድረስ ይልቅ ጆሴፈስ በሌሎች ስራዎቹ ስለሰዱቃውያን ያስቀመጣቸውንና ከላይ ከተጠቀሱ ክፍል ጋር ተነፃፃሪ የሆኑ ክፍሎችን ስንመለከት [8] ጆሴፈስ እያነፃፀረ ያለው የሙሴን መፅሀፍትና ሌሎቹን የመፅሀፍ-ቅዱስ ክፍሎች(የነብያትንና የፀሀፍትን መፅሀፍ) ሳይሆን በሙሴ መፅሀፍትና በአፋዊ ባህል (Oral tradition) መሀከል ነው። ከዚህም በዘለለ ጆሴፈስ በሌላ ስራው መላው የአይሁድ ማህበረሰብ ባጠቃላይ 22 መፅሀፍትን እንደሚቀበሉ አስቀምጧል። ስለዚህ ይህም ሙግት የጆሴፈስን አቋም የማያንፀባርቅ ደካማ ሀሳብ ነው!

4 - ጥንታዊ የቤተክርስቲያን አባቶች (ለአብነት ያህል ሂፖሊተስ[9]፤ አርጌን[10]) በርግጥም ሰዱቃውያን የሙሴን መፅሀፍት ብቻ እንደሚቀበሉ አስቀምጠዋል።

ይህ ሀሳብ ከላይ ከተነሱት ሙግት ይልቅ የሚነሳው ትንሽ የተሻለው ሙግት ነው! ነገር ግን ይህም ቢሆን ወደድምዳሜው ሊያደርሰን የሚችል በቂ የሆነ አቅም ያለው አይደለም። ከሁለተኛው ክፍለዘመን ቅ.ኢ.አ አንስቶ ሰዱቃውያን የቤተ-መቅደስን ሙሉ አገልግሎት የሚዘውሩና የሚቆጣጠሩ ነበሩ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ በቤተ-መቅደሱ የሚቀመጡት መፅሀፍት ደግሞ የሙሴ መፅሀፍት ብቻ ሳይሆኑ የነብያትና የፀሀፍትም ጭምር ናቸው። [11] ፈሪሳውያን ካላቸው የቁጥር ብዛትና ከማህበረሰቡ የአብላጫ ድምፅ ግፊት ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ ሰዱቃውያን

[6] Origen and the Jews,pp.46, 173.

[7] Ant 18.1.4 ፤ Ant 18.16

[8] Ibid 13.10.6 or Ant 13.297

[9] Refutation 9:29

[10] Against celsus 1:49 ፤ commentary on mattew 17:35

[11] Rogor Beckwith , The old testament conon in the new testament church , 82-5

ወደ ፈሪሳውያንን አቋም ያዘነብላሉ። ነገር ግን ይህ ከሆነና በርግጥም እንደታሰበው ሰዱቃውያን የሙሴን መፅሀፍት ብቻ የሚቀበሉ ቢሆኑ ኖሮ የቤተመቅደሱ ሰዱቃዊ ሊቀ-ካህን (chief priest) ፈሪሳውያንን በቤተመቅደሱ አዲስ መፅሀፍትን እንዲያስገቡ ይፈቅድ ነበር ማለት ነው ፤ ከዚህም አልፎ በማለዳ ለሚኖረው የመስዋእት አገልግሎቱ ሌሊቱን ሙሉ ቅዱሳት መፅሀፍትን ስለሚያነብ እነዚህን በፈሪሳውያውያን ብቻ የተያዙትን አዲስ መፅሀፍት ጨምሮ እንደ ሙሴ መፅሀፍት እኩል ሲናነብ ነው የሚያድረው እያልን ነው ማለት ነው። ይሄ ከሆነ ደግሞ በአይሁድ ማህበረሰብ መሀከል ከፍተኛ መለያየትንና ክርክርን በፈጠረ ነበር ፤ ከዚህም መሀከል ደግሞ አንዱ በሊቀካህኑ ላይ የሚነሳ ቅሬታ ይሆን ነበር። እንግዲ ይህን በሰዱቃውያን ላይ ይህን አቋም መያዝ ይህን አይነት ተፃርኖ የሚያመጣ ከሆነ ከዚህ ሁሉ አሳማኝና የተሻለውና ይበልጥ የሚያስኬደው እይታ ሲጀመርም መፅሀፍቱ (የሙሴ የነብያትና የፀሀፍት) ሰዱቃውያን የቤተመቅደሱን አገልግሎት ከመቆጣጠራቸው በፊትም በቤተ-መቅደሱ ከነበሩና ይህን ያህልም ጥንታዊነት ከነበራቸው በርግጥም ፈሪሳውያንም ይሁኑ ሰዱቃውያን በጋራ የወረሷቸውና በሁለቱም ማህበረሰብ መሀከል ተቀባይነት የነበራቸው መሆናቸው ነው።

ከላይ የተመለከትነው እውነት እንዳለ ሆኖ በክርስቶስ ዘመን የቤተ-መቅደሱ ሊቀካህን የነበረው ቀያፋ ሰዱቃዊ ነበር። እርሱም ብቻ ሳይሆን በሱ ዙሪያ ያሉ ፃፎች ሽማግሌዎችና መሪዎች ሰዱቃውያን ነበሩ።[12] የወንጌላት መፅሀፍት እንደሚነግሩን በሄሮድስ የመጨረሻ ዘመናት የጊዜው ሊቀካህናትና ፃፎች የመሲሁን መምጣት የት ፤ መቼና እንዴት እንደሚሆን ከሙሴ መፅሀፍት ይልቅ የነብያትንና የፀሀፍትን መፅሀፍት በመመርመርና በማገላበጥ ለማወቅ እንደሞከሩ ፤ ሚክ 4:2 ጠቅሰው መሲሁ የት እንደሚወለድ ለንጉሱ እንደነገሩት ፤ ቀያፋ ሊቀካህን በነበረበት በዛው ጊዜም ኢየሱስ "የዳዊት ልጅ" መባሉን እነዚሁ ካህናትና ፀሀፍት ባዩ ጊዜ እንደተቃወሙ ተቀምጧል። (ማቲ 2:4-6 ; 21:15) ግን ሰዱቃውያን የነብያትንና የፀሀፍትን መፅሀፍት ማይቀበሉ ቢሆን ይህ ሁሉ እንዴት ሊከሰት ይችላል? ከላይ በጥልቀት እንደተብራራው ሰዱቃውያን አምስቱን የሙሴ መፅሀፍት ብቻ ይይዛሉ የሚለው እሳቤ በቂ ማስረጃ የሌለውና ይዟቸው የሚመጣቸው ከእውነታ ጋር አለመጣጣሞች አሉትና ተቀባይነት የለውም። ይልቁኑ ሰዱቃውያን ልክ እንደፈሪሳውያን ሶስቱንም የመፅሀፍት ክፍል የሚቀበሉ ናቸው። ከዚህ አንፃር እነዚህን ማህበረሰብ በመጥቀስ አይሁዳውያን መሀከል አንድ አቋም አልነበረም የሚለው ሙግት እጅግ የሳተ ይሆናል ማለት ነው።[13]

- <u>ኢሲኖች</u>

ጆሴፈስ የአይሁድ ማህበረሰብን በሶስት ክፍል ሲከፍል በሶስተኛ የጠቀሳቸው ኢሲንስ ናቸው። እኚህ የአይሁድ ማህበረሰብ ከክርስቶስ ልደት ሁለት ክፍለ-ዘመን በፊት ከመደበኛው አይሁድ ማህበረሰብ ተገንጥለው በሙት ባህር አካባቢ በሚገኝ የፍልስጤም ምዕራባዊ ክፍል ከትመው የነበሩ የአይሁድ ክፍሎች ሲሆኑ እጅግ ብዙ ጥቅሎችንና ፅሁፎችን በመዛግብቶቻቸው የያዘ ነበሩ። በ1945 በተደረገው የአርኪዮሎጂ ጥናንም በቁምራን አካባቢ ወደ ፲፩ በሚደርሱ ዋሻዎች ይዘዋቸው የነበሯቸው እነዚህ መዛግብቶች ተገኝተዋል። ከዚህ ግኝትም በመነሳት ስለ እነዚህ ማህበረሰብ በጥልቀት ማወቅ ተችሏል። እኚህ ማህበረሰብ ከመደበኛው የአይሁድ ማህበረሰብ የበለጠ ቁጥር ያለው መፅሀፍትን እንደሚቀበሉ አድርጎ የሚነሳው እይታ እጅጉን የተለጠጠና ዛሬ ላይ በእጃችን ካለው ማስረጃዎች አንፃር ጭራሽ ሊደረስበት የማይቻል ድምዳሜ ነው። በሙት ባህር ከተገኙት ማስረጃዎች አንፃር እነዚህ ማህበረሰብ የአምላክ እስትንፋስ አድርገው ይቀበሉት የነበሩትን መፅሀፍትና ብዛት በእርግጠኝነት ለመናገር ሚያስችል አይደለም። ብሩስ ይህንን እንዲህ ያስቀምጣል ;-

[13]Joachim Jeremias, Jerusalem in the Time of Jesus, pp. 194, 229f., 377f.

“But the men of Qumran have left no statement indicating precisely which the books represented in their library ranked as holy scripture in their estimation, and which did not." [14]

ብሩስ ከዚህ በዘለለ እንደውም በመጀመሪያዎቹ የክርስትና ክፍለዘመናት ኢሲንስ ከፈሪሳውቻንና ከሰዱቃውያን አንፃር ተዛማጅነትና ተነፃፃሪነት ያለው አቋም እንደነበራቸው ያስቀምጣል።

" It is probable, indeed, that by beginning of the Christian era the Essenes (including the Qumran community) were in substantial agreement with the Pharisees and the Saducees about the limits of Hebrew scripture." [15]

ከቁምራን የምናገኘው ማስረጃ ኢሲኖች የነበራቸውን አቋም በእርግጠኝነት ሊያሳየንና ሊያስረግጥልን የሚችል እንዳልሆነ በዚሁ ላይ ያጠና ሌላኛው ልሂቅ James C. VanderKam ያስረግጣል።

" In view of the evidence from Qumran, we should avoid using the words Bible and biblical for this period and this community. This is not to deny the group had authoritative writings; the difficulty is that we, at our remove of a couple of thousand years, cannot always be sure which of those writings were authoritative and which were not. " [16]

ራጀር እንደሚሞግተው ኢሲኖች የከተቧቸውን የእጅግ ብዙ ስራዎቻቸው ምክንያት የአምላክ እስትንፋስ አድርገው ለሚቀበሏቸው ጥንታዊ መፅሀፍት ፍታቴና ማብራሪያ ማዘጋጀታቸው ነበር። ከእነዚህም ስራዎቻቸው ውስጥ Damascus Document ፤ Community rule or manual of Discipline ፤ Rule annex or Messianic rule ፤ Book of Blessing ፤ War Scroll ፤ Hymn Scroll ፤ Halakik Letter ፤ Genesis Apocryphon ፤ Temple Scroll ናቸው። በእነዚህ ውስጥ የሄኖክና የኩፋሌ መፅሀፍትም የሚካተቱ ናቸው። የቁምራን ሰነዶች ልክ እንዴሎቹ የአይሁድ ሰነዶች የአምላክ ቃል አድርገው ከሚቀበሏቸው መፅሀፍት በተደጋጋሚ ይጠቅሳሉ ፤ አጠቃቀሳቸውም የአምላክ እስትንፋስነታቸውን በሚያስረግጥ የተለመደ መንገድ ነው። ከሌሎቹ ሰነዶች ግን እጅግ በጥቂቱ ሲጠቅሱ እነዚህም ደግሞ ለሰነዶቹ ቀኖናዊነት ምንም አይነት ፍንጭ በማይሰጥ መንገድ ያለ ነው። ከዚህና ከሌሎች እውነቶች በመነሳት ኢሲኖች ከአባቶቻቸው ወርዶ በመጣላቸው መፅሀፍት ላይ ሌሎችን ጨምረው ሳይሆን በነሱ ላይ ማብራሪያ እየሰሩ ብቻ እንደሆነ ይህ ልሂቅ ያስቀምጣል። (365)

" lt is now clear that the main purpose of some of the pseudepigrapha, lately identified as Essene or proto-Essene, was to expoundand maintain the Essene interpretation of the Pentateuch, over against rival interpretations. This is particularly clear in the case of the newly - discovered Qumran Temple Scroll, but it also applies to the Astronomical Book in 1 Enoch (1 En. 72-82), to Jubilees and to an extensive section of the Aramaic Testament ofLevi. "[17]

[14] FF Bruce , The canon of scripture , pdf page 29 – 30

[15] FF Bruce , The canon of scripture , pdf page 32 - 31

[16] The Canon Debate , p 109

[17] Roger Beckwith , The old testament Canon , p 360

ከራጀር ሀሳብ ጋር በተወሰነ መልኩ የሚዛመድ እይታ ያለው የአይሁድ ልሂቅ ኮኸን ሼይም ኢሲኖችን በቀኖና ላይ ግልፅ ያለ ነገረ እንደሌላቸውና በእርግጠኝነት ልንናገርለት የሚያስቸለንን ምንም ፍንጭም እንዳልተው ያስቀምጣል።[18] እነዚህ ማህበረሰብ ልክ እንደሌሎቹ አይሁዳውያን ነብያት መልእክት መስጠትን ከጥንት እንዳቆሙ ስለሚቀበሉ እነርሱ የሰሩት በቀደሙት መፅሀፍት ላይ የትርጓሜና የፍታቴ ስራ እንደሆነም ይናገራል። እነዚህ ማህበረሰብ ታናክንም ይሁን ሌሎች ስራዎቻቸውን በአንድነት ይቀበሉ እንደነበርነና በመሀከላቸውም የተለያየ አቀባበል እንደነበራቸው ምንም አይነት መለኪያ ሊያሳይ እንደማይችል ያስቀምጣል። በጥያቄ መልክም ለምን እነዚህን ተቀብለው እነዛን አልተቀበሉም በማለት ይጠይቃል። ነገር ግን በሁለቱ መሀከል ማለትም ቀድሞውም በሁሉ ዘንድ ተቀባይነት ባላቸውና (22ቱ መፅሀፍት) እራሳቸው በከተቧቸው እንዲሁም በነሱ ዘንድ ብቻ ባሉ መፅሀፍት መሀከል የአቀባበል ልዩነት የመጣበትን ምክንያትና ለምን አንዱን ተቀብሎ ሌሎቹን አልተቀበሉም ለሚለው ጥያቄው የሰጠው ምላሽ የሰነዶቹ በማህበረሰቡ መሀከል በነበራቸው ስርአት ምክንያት ("The social setting of the literature") እንደሆነ ነው። ይህም ማለት እራሱ እንደሚያምነው መፅሀፍቶቹ ቀኖናዊ ለመሆን በሰፊው የአይሁድ ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ሊኖራቸው ስለሚገባ ነገር ግን እነኚህ በቁምራን የተገኙ የቁምራን ማህበረሰብ ብቻ ሰነዶች ተቀባይነት ካላቸውም በነሱ ዘንዳ ብቻ ስለሆነና በመላው የአይሁድ ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት የላቸውምና ከዚህ አንፃር ቀኖና ውስጥ ተካተው ወይም የአምላክ እስትንፋስ ተብለው እንዳልተወሰዱ ያስቀምጣል። ከዚህ ምክንያት በዘለለ ግን ለምን ? የሚለውን "አናውቅም" በማለት ይዘጋዋል።[19] ይህ ልሂቅ የአሌክሳንደርያ ቀኖናን (Jews of the Dias-pora) እና የፍልስጤም ቀኖናን (Palestine canon - Including Josephus , Rabbis) በመጥቀስ የተለያዩ የአይሁድ ማህበረሰብ የተለያየ ቀኖና ይቀበላሉ በማለት ሁሉን የሚያስማማ አቀባበል እንደሌለ ለማቅረብ ሞክሯል። ለዚህ ግን እርግጠኛ ያልሆነና ቅደመ-እሳቤ ላይ የተመሠረተ መላምት ነው ያቀረበው! ይህ እሳቤ አሳማኝነት የሌለውና በዚህ ሰአትም በብዙ ልሂቃን ተቀባይነት የሌለው እንደሆነ ከላይ በሰፊ አስቀምጠናል።

ከላይ የተብራሩትን የአይሁድ ክፍሎች ከመጥቀስ በዘለለ በአይሁዳውያን መሀከል የመፅሀፍት ልዩነት እንደነበር ለማረጋገጥ የአሌክሳንደርያንና በሌሎች ቦታ የተበተኑ አይሁዳውያን (Jews of the Diaspora) ቁጥሩ ከፍ የሚል መፅሀፍትን የአምላክ ቃል አድርገው እንደሚቀበሉ በማስቀመጥ የሚነሳ ሙግት አለ።

ይህ የአሌክሳንደርያ ቀኖና (The Alexandrian canon) እሳቤ እስከቅርብ አመታት (up until Moder scholarship) በቀኖና ዙሪያ ላይ ያጠኑ አንዳንድ ልሂቃን ይዘውት የነበረ እይታ ወይም መላምት ነበር። ይኸውም ከ3ኛው ክፍለዘመንና ከዛ በኋላ ባለው ዘመን ውስጥ በፍልስጤምና {Palestine} በአሌክሳንደርያ (የጊዜው የግብፅ ዋና ከተማ) መሀከል የቀኖና ልዩነት እንደነበር ፤ አሌክሳንደሪያዎችም ከፍልስጤም አይሁዶች በቁጥር የበለጠን መፅሀፍት እንደሚቀበሉ ነው። ይህን እሳቤ በዋነኝነት ያስቀመጠውና ብዙዎች መሠረት የሚያደርጉበት ልሂቅ ራይል (H.E. Ryle , 1890) ነው። "The Canon of Old testament" በተሰኘ ስራው በዘመኑ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተሰሩትን ስራዎች ባጠቃላይ አጣምሮ ያስቀመጠና ይበልጥ ጥልቀት የታየበት ስራ የሰራ ፤ ከሱ በኋላም የመጡ ብዙ ልሂቃኖች ላይ ተፅእኖ የፈጠረ ግለሰብ ነው። ከሱ በኋላ የመጡ ይህን እሳቤ የያዙ ልሂቃንም በዋነኝነት ሚጠቅሱት የሱን ስራ ነው። ከሱና በጊዜው ከነበሩ ጥቂት ልሂቃን በፊት በዚህ በቀኖና ዙሪያ የተሰራ የጠለቀ ስራ አልነበረም። በቀኖና ዙሪያ ጥልቀት ያላቸው ብዙ ስራዎች የተሰሩት በ20 ክፍለ ዘመን ፤ በተለይ ደግሞ ከሙት ባህር ጥቅልሎች ግኝት በኋላ ነው።[20] ራይል በዚህ ስራው ካስቀመጣቸው እሳቤዎች መሀከል አንዱ የአሌክሳንደሪያ ቀኖና ከፍልስጤም አይሁዳውያን ይበልጥ እንደነበር ነው። ይህን እሳቤ A.C. Sundberg 'The Old Testament Of the early church' በተሰኘ

[18] Cohen Shaye , From Maccabees to the Mishnah , 2nd ed , p 169 , 179

[19] Ibid , p 183 - 4

[20] Roger Beckwith , The old testament Canon , p 4 - 7

መፅሀፉ በጥልቀት ሞግቶታል። በዚሁ ላይ በቀኖና ዙሪያ ሙሉ ህይወቱን ሰቶ የሰራው እውቁ Lee Martin McDonald እይታውን እንዲህ በማለት ያስቀምጣል :

“What is more, there is no evidence that the Alexandrian Jews, or the other Jews of the Diaspora, were any more likely to adopt additional writings into their sacred Scriptures than were the Jews of Palestine in the last two centuries B.C.E. and the first century C.E. Further, no evidence shows the existence of a biblical canon in Alexandria in the second century B.C.E. or up to the second century C.E. that dif-fers from the one in Palestine.” [21]

በዚሁ ላይ እውቁ ራጀር ቤክዊዝም በዚሁ በአሌክሳንደርያን ቀኖና ላይ ሰፊ ሙግት ካቀረበ በኋላ የሰጠው ድምዳሜ እንዲህ ነው :-

" One must therefore conclude that, on the canon as on other matters, the Hellenis-tic Jewry of the Dispersion took its lead mainly from Palestine. .... Egypt did not create any tradition of its own on the matter. lt certainly valued various uncanoni-cal books in their Greek form, just as Palestine valued some of the same books and some other books in their Semitic form, but the idea that it added them to the can-on has no significant evidence in its favour and considerable evidence against it." [22]

የአሌክሳንደርያ አይሁዳውያንና በሌሎች ስፍራዎች ላይ የተበተኑ አይሁዳውያን በቁጥር ከፍልስጤም አይሁዳውያን የሚበልጥ መፅሀፍትን የአምላክ እስትንፋስ አድርገው እንደሚቀበሉ የሚቀርበው እሳቤ በዚህ ሰአት ተቀባይነት እንደሌለው ከላይ የጠቀስናቸው እውቅ ልሂቃን ጥቂት ምስክሮች ናቸው።

በአጠቃላይ በዚህ ክፍል ለመዳሰስ እንደሞከርነው እግዚአብሔር ከጥንት ከሙሴ ጀምሮ መልእክትን ለመረጣቸው ለአይሁድ ማህበረሰብ እየሰጠ እነርሱም ከእግዜር የሰሙትና የተቀበሉትን መልእክት በመያዝ በጠነከረ የፅሁፍና በቃል ባህላቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ ጠብቀው በማቆየት ዘመናትን ተሻግረዋል። በዚህም ዛሬ ላይ ስለብሉይ መፅሀፍት ብዛትና አይነትም ለማወቅ ቀጥታ ወደነዚህ በእግዜር ታምነው የቃሉ አደራ ወደተሰጣቸውና የእግዚአብሔር ቃል ወደ ወጣባቸው ማህበረሰብ መመልከት ግድ እንደሚለን ተመልክተናል። በዚህም እውነት ላይ ሊነሱ የሚችሉ የተለያዩ ሙግቶችን በማንሳት ሰፋ ያለ መልስ አስቀምጠናል። በዚህ ክፍል የተብራራውን እውነት መረዳት ከሁሉ በፊት ቀዳሚና እጅግ አስፈላጊ ነው።

[21] The bible canon , p - 138
[22] Roger Beckwith , The old testament Canon , p 386

የሰባውሊቃናት ትርጎሜ - SEPTUAGINT (Lxx)

ከእብራይስጥ ወደ ግሪክ ~ የመጀመሪያው የአይሁዳውያን ትርጓሜ (translation)

ከክርስቶስ ልደት ከሶስት ክፍለዘመን አጋማሽ በፊት የግብጽ ሀገር ገዢ የነበረው ሁለተኛው ፊላደልፈስ ቶለሚ (285-247 B.C.) ትልቅ ቤተ መፅሐፍ ለመገንባት አቅዶ በመላው አለም የሚገኙ መፅሀፍትን ወደ ግሪክ ማስተርጎም በጀመረበት ጊዜ ነበር በእየሩሳሌም ለሚገኙ የአይሁድ ሊቃናትንም የትርጓሜ ጥያቄ በደብዳቤ ያቀረበላቸው። ይህም ደብዳቤ "The Latter Of Aristeas" በመባል የሚታወቅ ሲሆን አሪስቲስ በተባለው በቶለሚ ግዛት ውስጥ በፍርድ ቤት የሚያገለግል ሰው ሲሆን በሱ የተፃፈ ደብዳቤ ነው። የላከውም ፊሎክራተስ ለሚባለው ወንድሙ ነበር። በዚህ ደብዳቤ ውስጥም እንደተገለፀው የአይሁዳውያን ሊቃውንት አምስቱን የሙሴን መፅሀፍት {Pentateuch} ወደ ግሪክ እንዲተረጉሙ የሚያጠይቅ ነበር። ከእያንዳንዱም 12ቱ የእስራኤል ነገዶች 6 ሊቃናት ተውጣጥተው በጠቅላላ 72 በሚደርሱ ሊቃናት የእብራይስጡን አምስቱን የሙሴን መፅሀፍት በመያዝ ከኢየሩሳሌም ወደ ግብፅ ዋና ከተማ አሌግዛንደሪያ አምርተው በዛ የመጀመሪያው ትርጓሜ ከክርስቶስ ልደት 250 አመታት በፊት ከእብራይስጥ ወደ ግሪክ ተተረጎመ። ይህም ትርጓሜ በሰባ ሁለት ሊቃናት የተተረጎመ ቢሆንምኳ ለመጠሪያነት እንዲቀል ሲባል ሰባ ሊቃናት {Septuagint Or Lxx} በመባል ይጠራል። በጊዜውም የእብራይስጥ ቋንቋ በእለት ተእለት ኑሮ ውስጥ ተጠቃሚነቱ እየደበዘዘ በመምጣቱና በተቃራኒው ደግሞ የግሪክ ቋንቋ ተጠቃሚው በፍጥነት እየሰፍና እየበዛ በመምጣቱ በጊዜው ይህ ትርጓሜ አይሁዳውያንን ያስደሰተና ያረካም ነበር።

ይህ ከላይ ስለሰባሊቃናቱ የተሰጠው ማብራሪያ በዋነንነት መሰረት የሚያደርገው The letter of Aristeas በተሰኘው ሰነድ ላይ ነው። ይህም የሰባላቃናቱን ምንጭ ታሪክ የሚዘግብልን ያለን ብቸኛ ጥንታዊ ማስረጃ ነው። ይህ መፅሀፍ/ ደብዳቤ በራሱ እራሱን የቻለ የጠለቀ ትችት የሚደርስበት ቢሆንም በዚህ ላይ የሚሰጠው ትረካ ለሰብአሊቃናቱ ምንጭ ታሪክ ማብራሪያ ሆኖ ይቀርባል። ነገር ግን ይህ ሰነድ ከሚሰጠን ከላይ ከተገለፀው ዘገባ በተለየ መልኩ የሰባሊቃናቱ ትርጎሜ ምክንያቱም ውጤቱም እራሳቸው አይሁዳው እንደሆኑ አንዳንድ ልሂቃን ይናገራሉ። ከክርስቶስ ልደት በፊት በሶስተኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ የግሪክ ቋንቋ እጅግ በመንሰራፋቱ እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸው አይሁዳውያን ግሪክ ብቻ ተናጋሪ በመሆናቸውና ፤ በቤተመቅደስም ዘወትር የሚሰጠው ስርአት ከእብራይስጥ ወደ ግሪክ በመተርጎም ይከናወን ስለነበር ፤ በተያያዥ በተቃራኒው ደግሞ የእብራይስጥ ቋንቋ ተጠቃሚነቱ እጅግ እየወረደና እየሞተ የመጣ ቋንቋ በመሆኑ ምክንያት አይሁዳውያን መፅሀፍቶቻቸውን ወደ ግሪክ የመተርጎም እሳቤ ይዘው እንደተነሱ እንዲሁም በተለያዩ ሀገራት ተበትነው ለሚገኙት ግሪክ ተናጋሪ አይሁዶች ያላቸውን ባህልና ታሪክ እንዲያውቁ ከማድረግ አንፃር እንደነበር ፤ የዚህም እሳቤ የመጀመሪያ ውጤት ሰባሊቃናቱ እንሆነና ከዚህም በኋላ አይሁዳውያን እጅግ በርካታ ፅሁፎቻቸውን ማለትም መፅሀፍቅዱሳዊ ይዘት

ያላቸውን ብቻ ሳይሆን ሌሎች መዛግብቶቻቸውን ወደ ግሪክ መተርጎም እንደጀመሩና ብዙ ርቀትም እንደሄዱበት ይነገራል።[23]

በዚህ በኤርስቲስ ደብዳቤ በተገለፀልን ታሪክ ውስጥ ሌሎቹ ከሙሴ መፅሀፍት{Pentateuch} ውጪ ያሉት የብሉይ መፅሀፍት እንዲሁም Apocryphal በመባል የሚታወቁት መፅሀፍት መቼናት በማን ወደ ግሪክ እንደተተረጎሙ አልተገለፀም። በርግጥ ብዙ scolars የሰባሊቃናቱን Pentateuchንና የቀሩት መፅሀፍቶችን (Nevim , Ketuvim and apocryphals) እርስ በርስ እያስተያዩ የአፃፃፍ ዘዴአቸውን ፤ የቃላት አጠቃቀማቸውንና ፤ ጠቅላላ የሰዋሰውና የስነፅሁፍ አቀማመጣቸውን ሲመለከቱ በሁለቱ መሀከል ከፍተኛ የአፃፃፍ ልዩነት እንዳለ በማረጋገጥ የፀሀፊያን ልዩነት አለ በማለት ድምዳሜን ይሰጣሉ።

በዚህ ላይ የሚነሳው አንደኛው ስሁት አረዳድ የሰባሊቃናቱ ትርጓሜ በሚተረጎምበት ጊዜ ሰባ ሁለቱ ሊቃናቶች አፖክሪፋልን (በ8ነዱ ወይም በ73ቱ ብቻ የሚገኙትን 7ቱን መፅሃፍት) አብረው እንደተረጎሙ አድርጎ ማሰብ ነው። ለዚህ አንዳች ማስረጃ የለም! ያሉን ማስረጃዎች ሁሉ የሚጠቁሙን (ከላይ የተጠቀሰው የአርስቲስ ደብዳቤ - ሙሉ ለሙሉ የትርጎሜው ታሪክ የተቀዳው ከሱ በመሆኑ ትልቁ ማስረጃ ነው!) እንደውም ይብስ አምስቱን የሙሴ መፅሀፊት ብቻ እንደተረጎሙ ነው። ሌሎቹን የብሉይ ክፍሎች ማለትም የነብያት እና የፀሀፍት መፅሀፍትን እንደተረጎሙ ራሱ ፍንጭ የምናኘው አንዳንድ የቤተክርስቲያን አባቶች ካሉት በመነሳት ብቻ ነው። እነዚህ አባቶች ያሉት ነገር ከግምት ውስጥ የሚገባ ቢሆንም ነገር ግን ይህንን አቋም ከየት እንዳመጡት ብንጠይቅ በሚገርም ሁኔታ ለእነርሱ ምንጭ የሚሆናቸው ይህን ሚድግፍ ምናገኘው አንዳች ማስረጃ የለም። ይህም ድግሞ ለሰባሊቃናቱ ታሪክ መሠረት ከሆኑ ሌሎች ቀዳሚና ወሳኝ ማስረጃዎች የምናገኘው እውነት ከእነርሱ አቋም ጋር የማይዛመድ ነው። ይህን እውነት አልፎ ጭራሽ አፖክሪፋልንም (በ8ነዱ ወይም በ73ቱ ውስጥ ብቻ የሚገኙትን 7ቱን መፅሃፍት) ተርጉመዋል ማለት ደግሞ ምንም ማስረጃ የሌለው ባዶ ጩኸት ነው። ስለዚህ ከነዚህ እውነቶች በመነሳት ሁሉን ማስረጃ ያማከለ ድምዳሜ ስንሰጥ ድምዳሜው የሚሆነው ፦

- ሰባ ሁለቱ ሊቃናት አምስቱን መፅሀፍት እንደተረጎሙ ሙሉ ለሙሉ እርግጥ ነው! (Certain)
- የነብያትንና የፀሀፍትን መፅሀፍትንም ተርጉመው ሊሆን ይችላል! (uncertain)
- ነገር ግን አፖክሪፋን በጭራሽ አልተረጎሙም! (certain)

ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ አንድ እርግጠኛ መሆን የሚቻለው ነገር ከሙሴ መፅሀፍት{pentateuch} ውጪ ያሉት መፅሀፍት ክርስቶስ ልደት በፊት ተተርጉመው እንደነበረ ነው። እነዚህም ትርጓሜዎች ምንም እንኳ በመጀመሪያዎቹ ሰባ ሁለቱ ሊቃናት ሳይሆን በሌሎች የአይሁድ ሊቃናት የተተረጎሙ ቢሆንም ግን በተለምዶ በጠቅላላው ሁሉም የግሪክ ትርጓሜዎች የሰባሊቃናቱ ትርጉም (Septuagint) የሚል ስያሜ አላቸው። ከላይ እንዳልኩት የግሪክ ቋንቋ ሰፊ ተናጋሪ ስለነበረውና በፍልስጤም ፣ በሲሪያ ፣ በሜሶፖታሚያ ፣ በኤሽያ በተጨማሪም በሰሜን አፍሪካ ይኖሩ የነበሩ ትልቅ ቁጥር ያላቸው ግሪክ ተናጋሪ አይሁዳውያን ይህ ትርጎሜ በፍጥነት በየቦታው እንዲንሰራፋ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

የሰባው-ሊቃናት ትርጎሜ እስትንፋሰ አምላክ የሆኑትን መፅሀፍትን ብቻ ቀንኖ ከመተርጎም ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም! ከላይ በተብራራው ጉዳይ ላይ ማስተዋል ያለብን ትልቅ ነገር አይሁዳውያን መፃህፎቻቸውን {24ቱን ብሉያትንም ይሁን ከሱ ውጪ ያሉትን} ወደ ግሪክ ሲተረጉሙ ትርጓሜ ብቻ እየሰሩጂ አዲስን ቀኖና

[23] Cohen Shaye , From Maccabee to Mishnah , 2nd edition , P 201

እየቀነኑ ወይም እየፈጠሩ እንዳልሆነ ነው። ትርጓሜ ብቻ እየሰሩ ነው ማለት በዚህ የመተርጎም ሂደት ውስጥ ከዛ በፊት ከሚያምኑበት አቋማቸው አንዳች የተለወጠ አቋም አልያዙም ደግሞም አንዳች አቋም አልጨመሩም ማለት ነው። ብዙዎች በዚህ ላይ የተሳሳተ አመለካከት እንዳላቸው ተመልክቻለሁ። ለምሳሌ ከ24ቱ ውጪ ያሉትን የአይሁዳውያንን መፅሀፍት ማለትም በ81ዱ ወይም በ73ቱ ውስጥ ብቻ የሚገኙትን 7ቱን የብሉይ መፅሃፍት እንደ አምላክ እስትንፋስ የሚቀበሉ ወገኖች በምን መሠረት እንዲህ እንደሚቀበሏቸው ሲጠየቁ "በሰባሊቃናቱ ውስጥ ስላሉ" የሚል ምላሽ ይሰጣሉ! ይህ ትክክለኛ አመክንዮ አይደለም። ምክንያቱም ሲጀመርም እነኚህ መፅሃፍት (Apocryphal) በሰባ ሁለቱ ሊቃናት የተተረጎሙ አለመሆናቸው ነው! እነሱ እንደተረጎሟቸው የሚያሳይ ምንም ማስረጃ የለም! ከላይ እንደተገለፀው በተለምዶ እነኚህ ሰባሊቃናት የሙሴ መፅሀፍትን ከተረጎሙ በኋላ ወደ ግሪክ የሚተረጎሙ የአይሁዳውያን መፅሀፍት ሁሉ የሰባሊቃናቱ ትርጉም (Septuagint) ተብለው ተጠቅልለው ስለሚጠሩ ብዙዎች ሁሉንም የእብራይስጥ ቅጂዎችን እነሱ እንደተረጎሙ እንዲገነዘቡ አድርጓል። ይህ ግን በተለምዶ የተጠሩበት ስያሜያቸው ብቻ እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው! ሲቀጥል ደግሞ ዋነኛው ነጥብ ከላይ እንደተገለፀው; አይሁዳውያን መፅሃፍትን ወደ ግሪክ ሲተረጉሙ የመተርጎም ስራ እንደሰሩ ብቻጂ የአምላክ እስትንፋስ የሆኑትን መፅሀፍት ብቻ ወስነውና ቀንነው የመተርጎም ስራ እንደሰሩ የሚያስረግጥ ምንም ማስረጃ አለመኖሩ ነው። ስለዚህ ወደ ግሪክ ተርጉመዋቸዋልና ከዚህ ተነስቶ የአምላክ እስትንፋስ አድርገው ተቀብለዋቸዋል የሚል ድምዳሜ በምንም መሰረት ሊሰጥ አይችልም!። ይህን መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው!

ይህ የግሪክ ትርጓሜ ኢየሱስም ሐዋርያቱም ጭምር የተጠቀሙት ትርጓሜ ነበር። እዚህ ላይም ማስተዋል ያለብን ነገር አለ። የሰባ ሊቃናቱ ትርጉም {Septuagint} ከክርስትስ ልደት በኋላ እስከ 4ተኛውና ክፍለ ዘመን ድረስ በጥቅልል መልክ የነበር ሲሆን ሁሉም ትርጓሜዎች በአንድ ላይ ሆነው እንደዚህ ዘመን መፅሀፍ የተቀመጡ ሳይሆን የተለያዩ ጥቅልሎች ጥርቅም ነበር። ሁሉንም ተርጓሜዎች ተሰባስበው በአንድ ላይ መቀመጥ የጀመሩት {በScroll Form ሳይሆን በCodex Form} ከ4ኛውና ክፍለዘመን ጀመሮ ነው። አሁንም በእጃችን ላይ የሚገኘው 7ቱን መፅሀፍት አጠቃሎ የያዘው የሰባሊቃናቱ ጥንታዊ እደክታባት በ4ተኛውና በ5ተኛው ክፍለዘመን በክርስቲያን የተፃፉት Codex Vanatict , Codex Sanaticus እና Codex Alexanderius ናቸው።

ምናልባት በዚህ ላይ የሚቀርብ ሌላ ሙግት አለ። ይህ የሰባሊቃናቱ ከክርስቶስ መወለድ በፊት የነበረ ነው። እንዲሁም በምዕራፍ ፍልስጤም (Western Palestine) በሙት ባህር አካባቢ በቁምራን ዋሻ በተገኙት እጅግ ጥንታዊ በሆኑት ጥቅልሎች (The Dead See Scroll) ውስጥ ከ7ቱ መፅሀፍት አብዛኛው ተገኝተውበታል። በዚህም ምክንያት በሰባሊቃናቱ ትርጉም ውስጥ የተካተቱት እነኚህ መፅሀፍት ትክክል ናቸው ማለት ነውና ስለዚህም በቀኖና መልክ መቀበል አለብን!! የሚል ሙግት ነው። ይህ ሙግት እጅግ የሳተ ድምዳሜ ላይ የተደረሰበት ደካማ ሙግት ነው! በቁምራን ዋሾች ውስጥ 7ቱ መፅሀፍት በመገኘታቸው ብቻ አይሁዳውያን የአምላክ ቃል አድርገው ተቀብለዋቸዋል ወደሚል ድምዳሜ በጭራሽ አያስደርስም። ምክንያቱም ደግሞ በአይሁዳውያን ሰፊ ማህበረሰብ ዘንድ እነዚህ መፅሀፍት ቀኖናዊ አርገው ተቀብለው እንደማያውቁ እርግጥ ስለሆነና ይህን አስታኮም በቁምራን ዋሻ ውስጥ እንደአምላክ ቃል የሚታዩ የአይሁድ መፅሐፍት ብቻ ባለመገኘታቸውም ጭምር ነው ፤ ስለዚህም እነዚህን ለይቶ መቀበል አለብን ለማለት የሚያደርስ በቂ ምክንያት የለም። በዛ ዋሻ ውስጥ መገኘታቸው እነኚህ መፅሀፎችን በፀጥታው ዘመን መፃፋቸውንና የራሳቸው የአድሀዳውያን የፅሁፍ ውጤት መሆናቸውን የሚያስረግጥ ብቻ እንጂ ከቀኖና ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም።

ከሰባሊቃናቱ ትርጉም ጋር በተያያዘ ሌላው በተደጋጋሚ ሲነሳ የሚሰማው ፤ ማንሳት ብቻም ሳይሆን አጠንክሮ ሙግት ሲቀርብበት የሚስተዋለው ሀሳብ የማዞሬቲኩ ቴክስት {Masoretic text} ነው። የማዞሬቲክ ቴክስት የሚባሉት ከስድስተኛ ክፍለ ዘመን አንስቶ ማዞሬት የተባሉ የአይሁድ ወገኖች (sects) የብሉይን መፅሀፍትን በተለየ የአፃፃፍ ዘዴና አይነት የፃፏቸው እጅግ ብዙ የእብራይስጥ እደክታባት ናቸው። እነዚህ ወገኖች መፅሀፍትን ሲገለብጡ ሆን ብለውም ይሁን በግልበጣ ስህተት (copy error) ከጥንት ከነበረው የብሉይ መፅሀፍት አንፃር የማይስማሙ እጅግ አዳዲስ ቃላቶችንና ሀረጎችን በተለያዩ ምንባባት ላይ ለውጠዋል። እንዲህ የማድረጋቸው ዋነኛ ምክንያት ሆኖ የሚቀርበው በዛ ጊዜ አይሁዳውያን ክርስትናን እጅግ አጥብቀው ይቃወሙ ስለነበርና ክርስቲያኖች ደግሞ ብሉያትን እየጠቀሱ የኢየሱስን መሲህነት ሲያስረግጡ ይህ ተቃውመው በመሸሽ ነበር። ዛሬ ላይ የፕሮቴስታንቱ 66ቱ መፅሀፍት እነዚህን እደክታባት በበለጠ ተጠቅሞታል። ታድያ አንዳንድ ሰዎች ይህን በማንሳት 66ቱ ከተበረዘና ከተበላሸ ምንጭ መሠረት የሚያደርግ ስለሆነ መፅሀፍቶቻቹ ተቀባይነት አይኖራቸውም በማለት በቀኖና ልዩነት ላይ ሙግት አርገው ያቀርቡታል። ምንምኳ ስለማዞሬቲኩ ቴክስት ያለው እውነት እንዳለ ሆኖ ነገር ግን ከዚህ በመነሳት የተደረሰበት ድምዳሜ እጅግ የተለጠጠና ጭራሹኑም አውዱን የጠበቀ አይደለም። Ketef Hinnom Scroll ፤ Septuagint ፤ Dead Sea Scrolls ፤ Peshitta ፤ Samaritan Pentateuch ፤ Coptic ፤ Targum ... እናም ሌሎችም ብዙ የመፅሀፍ-ቅዱስ እደክታባት ዛሬ ላይ በእጃችን ደርሰዋል። የማዞሬቲኩ ቴክስትም ከነዚህ መሀከል አንዱ ምንጭ ነው ፤ ስለዚህም ከሌሎቹ ጋር ትይዩ በመደረግ ተገምግሞ ጥቅም ላይ ሚውል ነውጂ የሚጣል አይደለም።

ሲጀመር ይህን ሀሳብ በዚህ የአምላክ እስትንፋስ የሆኑትን መፅሀፍት በመለየት ሂደት ላይ መነሳት የሌለበት ጉዳይ ነው። ይህ ሀሳብ ቀጥታ ሚገናኘው ያሉንን እጅግ ብዙ ጥንታዊ እደክታባት እንዴት እያመሳከርን መጠቀም አለብን ፤ የቱኛውስ የበለጠ ተአማኒነትና እውነተኝነት አለው ከሚሉ ራሳቸውን ችለው ሰፊ ማብራሪያ ከሚፈልጉ ርዕሰ ጉዳዮች ጋር ነው። የአምላክ እስትንፋስ አድርገንንኳ ተቀብለናቸው ነገር ግን ከተለያዩ ምንጮች አንፃር የተለያየ መረጃ ያላቸው (Discrepancies) የተለያዩ ክፍሎች አሉ። የዚህ ወጥነተ መታጣት ምክንያቱ በእጃችን ላይ እጅግ ብዙ ምንጮች ስላሉ ነው። ማይካደው እውነት ደግሞ በመፅሀፍ ቅዱስ ምንጮች ላይ ውዝግብ ያለባቸውና የማይናበቡ ክፍሎች እጅግ በጣም በጥቂት ቦታዎች ላይ ብቻ አሳማኝነት ያለውን መውሰድ ነው። ስለዚህ የፕሮቴስታንት 66ቱ መፅሀፍ የማዞሬቲኩን ቴክስት መጠቀም ምክንያት በማድረግ የያዛቸሁት 66ቱ መፅሀፍት የአምላክ እስትንፋስ አይደሉም ብሎ ማለት እጅግ አላዋቂነት ነው። ይህን በቀላሉ ለመረዳት በዚሁ በኛው ሀገር አውድ በብዛት በውይይት ከሚደጋገመው ርዕስ በምሳሌ እናስቀምጥ። በሮሜ 8:34 ላይ የሚገኘውንና ጳውሎስ ሲፅፈው በግሪኩ " ἐντυγχάνω " ብሎ ያስቀመጠውን ቃል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ "የሚፈርደው" በማለት ተርጉማዋለች። ይህንኑ ቃል በፕሮቴስታንት ዘንድ "የሚማልደው" በመባል ተተርጉሞዓል። ከሁለቱ የአተረጓጎም ልዩነት በመነሳት በጠቅላላው የሮሜ መፅሀፍ የአምላክ እስትንፋስ አይደለም ወደሚል ድምዳሜ አይደረስም። ይልቁኑም በዚ ላይ ያሉንን የእደክታብ ምንጮች ፤ የክፍሉን አውድ ፤ ታሪካዊ ዳራውንና የአበው አጠቃቀምን በመመልከት አሳማኙ ተቀባይነት ያገኛል። ልክ እንደዚሁ የቃላትን ወይም የሐረግን ወጥ አለመሆን (Discrepancy) ይዞ 'የቱኞቹ መፅሀፍት አፊዎተ አምላክ ናቸው? ' በሚል ርዕስ ውስጥ በማንሳት ሙግት አዋቅሮ መሰንዘር አውዱን የጠበቀ ሙግት አይደለም። ስለዚህ ከሁሉ በፊት በመጀመሪያ የመፅሀፍቱን የአምላክ ቃልነት አረጋግጦ ፤ ደግሞም በውስጡ የሚገኙትን የቃላት ልዩነት {discrepancy} መፈተሸና መቀበል ቀጣይ ጉዳይ ይሆናል ማለት ነው።

ምንጭ ከአይሁድ!

1 ፊሎ - Philo

ይህ ሰው ከ 20bc - 50ad የኖረ ነው። ይህ ማለት በርግጥም ኢየሱስ በኖረበት ዘመን የነበረ ነው! ፊሎ አይሁዳዊ ሲሆን ታላቅ ፈላስፋና ፀሀፊም ጭምር ነው። ይህ ሰው በነበረበት ጊዜ ተጠቃሚነት የነበራቸው መፅሀፍት የሰባሊቃናቱ ትርጉም ነበሩ። እርሱም ይጠቀም የነበረው ይህንኑ ነበር። ይህ ሰው በፅሁፎቹ ውስጥ በብዛት የሙሴን መፅሀፍትን ፤ የነብያትንንና ፀሀፍትን (hagiographa) እየጠቀሰና እያብራራ ሲፅፍ አንድም ጊዜ ግን ከ7ቱ መፅሀፍት (apocryphal) አልጠቀሰም ፣ አልተጠቀመምም። ይህ ፊሎ እነዚህን መፅሀፍት እንደአምላክ ቃል እንደማይቀበላቸው ፍንጭን የሚሰጥና ከዚህም በተጨማሪ በዛ ጊዜ የሰባሊቃናቱን ትርጉም ስለሚጠቀሙ 7ቱን መፅሀፍት እንደ አምላክ ቃል አርገው ይቀበሉ ነበር የሚለውን ሀሳብ የሚያፈርስ ነው። ምክንያቱም ምንምኳ ፊሎ የሰባሊቃናቱን ቢጠቀምም ከነዚህ 7 መፅሀፍት አንዱም አልጠቀሰምም ፣ አልተጠቀመምምና።

2 ዮሴፍ ወልደ ቆርዮን - Flavius Josephus

ጆሴፈስ የአሌክሳንድሪያው አፒዮንን አቋም በመቃወም በከተበው ፅሁፍ ላይ ስለ አይሁድ መፅሀፍት ብዛት በመግለፅ አልፏል። አፒዮን የግሪክ መፅሀፈት ስለ አይሁዳውያን ጥንታዊ ታሪክ ማስረጃ የላቸውም በዚህም ምክንያት አይሁዳውያን የሩቅ ዘመን ታሪክ የሌላቸው እንደሆኑ የሚናገር ነበር። ጆሴፈስም Against apion በተባለው ስራው ይህንን በመቃወም ነው ለመሞገት የሞከረው። ጆሴፈስ በagainst apion ላይ ባስቀመጠው ማስረጃ መሠረት 22 መፅሀፍት እንዳላቸው እነዚህም መፅሀፍት ታሪካቸውን ሙሉ ለሙሉ የሚይዙ እንደሆኑ ፤ ከአዳም ጀምሮ እስከ ከሙሴ ሞት ፤ ከሙሴም ሞት እስከ አርጤክስስ ዘመን ድርስ ያሉትን ታሪክና ክስቶች ሁሉ ጠቅልሎ እንደሚይዙ ፤ እነዚህም ሁሉ ደግም በነብያት የተፃፉ እንደሆኑ ያስቀምጣል።

" ... Our books, those which are justly accredited, are but two and twenty, and contain the record of all time. ..." [24]

ከአርጤክስስ ዘመን በኋላ እስከሱ ዘመን ድረስ ያለው ታሪክ ተፅፎ እንዳለ ፤ ነገር ግን ስክትክት(exact) ያለ የነብያት ቅብብሎሽ ባለመኖሩ ምክንያት እነዚህ ዘገባዎች ከ22ቶቹ ጋር እኩል ዋጋ እንደሌላቸው ይናገራል። ይህ

[24] A.A 1.37 – 44

መፅሀፍ በመጀመሪያው ክ/ዘ የፃፈው መፅሀፍ ነው። ይህ ቁጥርና አቀማመጥም የግል እምነቱን ብቻ የሚወክል ሳይሆን ምንምኳ በሶስተኛው የመፅሀፍ ክፍል ዙሪያ የተለያየ ምልከታ ቢኖርም በዋነኝነት ግን ከዛ በፊትና በዛ ጊዜ የነበረውን የአይሁዳውያንን አመለካከት ጭምር የሚያንፀባርቅ ነው። በዚህ መፅሀፍ ዝርዝሩ ውስጥ ዛሬ በ81ዱ ወይም በ73ቱ ውስጥ ከተካተቱት 7ቱ የብሉይ መፅሐፍት ወደ 6-7 መፅሀፍት ሳያካት ጥሏል ፤ በዛ ዘመን እንደ አምላክ እስትንፋስ እንደማይቀበሏቸውም አረጋግጧል። በዚህ በጆሴፈስ ማስረጃ ላይ በሙግት መልክ ሊነሱ የሚችሉና ሊታወቁ የሚገቡ ሁለት መሠረታዊ እውነቶችን ቀጥለን እንመልከት።

22 ወይስ 24 ?

ጆሴፈስ በዚህ ስፍራ 22 በማለት መፅሀፍቶቻቸውን በቁጥር ቢያስቀምጥም በዝርዝር አይነታቸውን አላስቀመጠምና እርግጠኛ ሆነን የቱኞቹን መፅሀፍት ተቀብሎ እንደነበርና የቱኞቹን ጥሎ እንደነበር መናገር አንችልም። ጆን ባርተን (John Barton) የተባለ በብሉይ ቀኖና ላይ ያጠና ልሂቅም ስለዚህ ሲናገር እንዲህ ይላል ፦ " .. *ያካተታቸውን መፅሀፍት ወይም እንዴት እንደቆጠራቸው በእርግጠኝነት ማወቅ አይቻልም*"።[25] ነገር ግን ይህ እውነት እንዳለ ባስቀጠው ማስረጃ ላይ የአዋቂ ግምት (Intellectual Gus) መስጠት እንችላለን ፤ ብዙ ልሂቃንም ያላቸውን የተለያየ ግምት ይሰጣሉ።

አይሁዳውያን {በተለይ Rabbinical Judaism} መፅሀፍትን በ24 ቁጥር ሲያስቀምጡ ፤ ጆሴፈስ ግን የ22 ቁጥር አቆጣጠርን ማስቀመጡ 'እንዴት?' የሚል ጥያቄን ይጭራል። ነገር ግን ብዙ ልሂቃን ይህንን ትልቅ ልዩነት ወይም ቅዋሜ አድርገው አይመለከቱትም። በዚሁ በቀኖና ዙሪያ በጥልቀት ያለጠናው እውቁ የአይሁድ ልሂቅ ሌይማን (S.Z Leiman) ጆሴፈስ 22 በማለት ያስቀመጠው መሳፍንት ከሩት ጋር አንድ ላይ በማድረግ እንዲሁም ሰቆቃወ ኤርሚያስን ከኤርሚያስ ጋር አንድ በማድረግ ቆጥሮት እንደሆነና ይህም ደግሞ በእብራይስጥ የፊደላት አልፋቤት ቁጥር (22) ልክ ማስቀመጡ እንደሆነ ያስቀምጣል።[26] ይሁም ብቻ ሳይሆን ብሩስ (F.F Bruce) ይህንኑ እይታ አስቀምጧል። ከዚህ በተያያዘ ሌላኛው የአይሁድ ሊቅ ኮኸን ሼይ (Cohen shaye) እንደሚለው ከሆነም በRabbinical Canon መሠረት መፅሀፍቱ 24 ስለሆኑና ፤ ጆሴፈስ ግን 22 በማለት መፅሀፍቱን {በ5 - 13 - 4} ማስቀመጡ ደካማ መረጃ መሠረት አርጎ ወይም አውቆ እያሳሳተ እንደሆነ ግምቱን ቢናገርም ነገር ግን በዛው ስፍራ ዝቅ ብሎ ፦ ይህ 22 ወይም 24 የሚል የተለያየ የቁጥር አቀማመጥ የተለያዩ ቀኖናዎችን ሚያሳይ ሳይሆን አንዱን ቀኖና በሁለት የተለያየ መንገድ በመቁጠርና ማስቀመጥ እንደሆነ ድምዳሜውን ያስቀምጣል።[27] በዚህ ርዕስ ላይ አጅግ እውቅና የጠለቀ ስራ ከሰሩ ልሂቃን ለአብነት ነውና እየጠቀስን ያለነው ፤ በዚህ ውስጥ ራጀር ቤክዊዝን (Roger T.Beckwith) ሳንጠቅስ ማለፍ ማይታሰብ ነው። ይህ ልሂቅም ጆሴፈስ 22 በማለት ያስቀመጠው ሩትን ከመሳፍንት ወይም ከመዝሙር ጋር አጣምሮት እንደሆነና ሰቆቃወ ኤርሚያስን ደግሞ ከማሕልየ መሐልይ ወይም ከመክብብ ጋር በአንድነት አስቀምጦት እንደሆነ ግምቱን ያስቀምጣል።[28]

በጠቅላላው ከብዙ ማስረጃዎችና ልሂቃን ምልከታ አንፃር የምንረዳው ቁምነገር ጆሴፈስ 22 ማለቱ በአይሁድ ዘንዳ የነበረን አቋም እያንፀባረቀ መሆኑን ነው። በአይሁዳውያን ዘንድ 24ቱ ወይም 22ቱ መፅሀፍት የኛን የብሉይ

25 The old testament canon , P 159

26 Josephus and Bible canon , P 53 - 54

27 From Maccabees to the midras , 3rd edt , p 251

28 The old Testament canon of the new Testament church , P 80

39 መፅሀፍት የሚወክሉ ናቸው። የእኛን 5ቱን የሙሴን መፅሀፍት አይሁዳውያን አንድ መፅሀፍ አርገው ነው የሚቆጥሩት... ልክ እንደዚህ ሌሎቹንም በአንድ አርገው ቆጥረዋቸው የ24(22) አቀማመጥ ይከተላሉ። በአጭሩ ልዩነቱ የአቀማመጥ ብቻ እንደሆነ ለማስገንዘብ ነው።

3 የጀምኒያ ጉባኤ - Council Of Jamnia

እስከቅርብ አመታት ድረስ ልሂቃን በ90-100 ዓ/ም የአይሁድ ልሂቃን ተሰባስበው በሰነሀድሪም መፅሀፍትን እንደቀነኑ ያስቀምጡ ነበር። ይህን እሳቤ እጅግ እንዲስፋፋ ያደረገውና ብዙዎች ላይ ተፅኖ የተፈጠረ ስራ የሰራው ራይል የተባለ ልሂቅ ነው። አንዳንዶች እጅግ በሚያስገርም መልኩ ጀምኒያን በመጥቀስ አይሁዳውያን መፅሀፍትን አበላሽተው ፤ አውጥተው ፤ ገነጣጥለው 24ቱን (በኛ 39ኙን) መፅሀፍት አስቀርተዋል በማለት ሲናገሩ ይሰማል። ይህ ግን መፅሀፍትን ካለማገላበጥና ታሪክን ጠንቅቆ ካለማወቅ የሚመጣ ነው።

ሲጀመር ዛሬ ላይ ይህ መላምት በልሂቃን ዘንዳ ተቀባይነት ያጣና የተጣለ ነው። የዚህም ምክንያት እንደታሰበው የአይሁድን መፅሀፍት የወሰነ ጉባኤ አልተካሄደምና ነው። ብሩስ ስለዚህ አጠር አድርጎ እንዲህ ያስቀምጣል ፦

"It is probably unwise to talk as if there was a Council or Synod of Jamnia which laid down the limits of the Old Testament canon."

J.P Lewis የተባለው የአይሁድ ልሂቅ ሲጀመር ጉባኤ የተባለው ነገር ተካሂዶ ነበር? ወይስ የተለመደ የአዋቂዎች ውይይት ብቻ ነበር? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት በምላሹ የመጨረሻ ስልጣን ያለውን ድምዳሜ እንዳልተሰጠበት ለማስቀመጥ ሞክሯል።[29] በአይሁድ ታሪክ ላይ በጥልቀት ያጠናውና በኒው ዮርክ የብሮክሊን ዩኒቨርሲቲ የአይሁድ ታሪክና ፅሁፎች ፕሮፌሰር የሆነው አይሁዳዊ ሊቅ ሊማን (S.Z Leiman) እንደሚለው ከሆነም የአይሁድ የፀሀፍት {Hagiographa} መፅሀፍት ተጣምሮ የተጠናቀቀው ከክርስቶስ ልደት በፊት በሁለተኛው ክፍለዘመን እንደሆነ ያስቀምጣል።[30] ከዚህ በዘለለ ሮውሌይ (H.H Rowley) የተባለ ልሂቅም ስለዚህ ነገር እንዲህ በማለት አስቀምጧል ፦

"It is indeed doubtful how far it is correct to speak of the Council of Jamnia. We know of discussion that took place there amongst the ribbis but we know of no formal or binding decition that were made .. "

ምንምኳ ጀምኒያ ላይ ቀኖናዊ ጉባኤ እንደተካሄደ በዚህ ሰአት በሁሉም ልሂቃን ዘንዳ ተቀባይነት ቢኖረውም አይሁዳውያን በሰነሀድሪም የተለመደው ውይይት ማድረጋቸው አይካድም። በዚህ ጉባኤም ውይይት የነበረው በዋነኝነት በሁለት መፅሀፍት ላይ ብቻ ነበር ፤ እነርሱም መሀልየ መሀልይ ዘሰለሞንና መክብብ ናቸው። ከላይ እንዳየነው በጭራሽ አዲስ ነገር በጀምኒያ ውይይት አልተከሰተም።

---

29 What do we mean by Jabeneh ? P 125 - 32

30 An Historiacal study of the canonization of the Hebrew Scripture

4 - የዝምታው ዘመን

በአይሁድ ዘንድ ከዘካሪያስ ዘመን አንስቶ የእግዚአብሔር መንፈስ ከእስራኤል እንደተለየና ይህም ማለት ደግሞ እግዚአብሔር መልእክትን መስጠት እንዳቆመ ነብያትም እንደጠፉ ይታመናል። ይህን እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸው ልሂቃንም የሚቀበሉት እውነት ነው። ነብይ ሲባል ግን ማስተዋል ያለብን ነገር አለ። ነብይ የሚለው ቃል ቀጥታ ያለው ፍቺ ወደፊት ስለሚፈፀሙ ነገሮች ከእግዚአብሔር ተገልጦለት ቀድሞ የሚናገር ወይም የሚተነብይ ሰው ነው። ነገር ግን በአይሁድ ማህበረሰብ ዘንድ "ነብይ " ከዚህ የዘለለና የሰፋ ትርጉም ያለው ነው። ነብይ ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ቅርበት ያለው በእግዚአብሔር የተመረጠ ፤ የእግዚአብሔርንም ፍቃድ የሚፈፅም ፤ እግዚአብሔርም ለህዝቡ ያለውን ሀሳብና ፍቃዱን የሚያስታውቀው ፤ ተአምራትን በእጁ የሚያደርግ ፤ ከእግዚአብሔር የተቀበለውንም መልእክት ለትውልድ ፅፎ የሚያስተላለፍ (ሙሴ ፣ ኢያሱ ፣ ሳሙኤል ..) ፤ ለህዝቡም ወደ እግዚአብሔር የሚቃትትና የሚማልድ ግለሰብ ነው። ከዚህ አንፃር በአብነት በሉቃስ 24 ላይ አቤል በነብይነት መጠቀሱን መመልከት እንችላለን። ስለዚህ ነብይ ተብሎ ሲገለፅ ግዴታ ወደፊት የሚፈፀምን ነገር የሚተነብይ እየተባለ አይደለም። ይልቁኑ በዚህ አውድ ከእግዜር መልእክትን የተቀበሉና ከትበው ያስተላለፉ አካላትን የሚወክል ነው። አይሁድም ቶራ ፤ የነብያት መፅሀፍትና የፀሀፍት መፅሀፍት በእግዜር መንፈስ መሪነት በነብያት የተከተቡ እንደሆኑ ያምናሉ።

በአይሁድ ማህበረሰብ ዘንዳ የነብያት መጥፋት ቀጥታ የሚያመላክተው እግዚያብሄር ዝም ማለቱንና መልእክትን አለመስጠቱን ነው። በዚህ ላይ ቀድመን መረዳት ያለብን በዘመናት ውስጥ እግዚያብሄር ዝም የሚልበት ፤ መልእክትንም የማይሰጥበት ሁኔታዎች ሊፈጠሩ መቻላቸውንና በርግጥም ደግሞ በታሪክ ውስጥ የተከሰተ እውነት መሆኑን ነው።

የመዝሙር መፅሀፍ ምዕራፍ 74 ላይ የእስራኤል ህዝብ ምልክት ማየት ማቆሙን ፤ ነብያትም አለመኖራቸውን ይናገራል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጠላቶች በእግዜር ማህበር ላይ ስላደረሱት በደል ፤ መቅደሱም ማቃጠላቸውን ፤ በቅዱሳኑም ላይ ክፋትን ማድረጋቸውን ፤ የእግዜርንም ስም ማቃለላቸውን እየጠቀሰ እግዚያብሄርን ስለምን ጣልከን በማለት ሲማፀን እንዲሁም እንዲነሳና እንዲያስባቸው ሲጠይቅ ይነበባል። በዚህ መሀከል በቁጥር ዘጠኝ ላይ በዛ ጊዜ ምልክትን አለማየታቸውንና ነብያት አለመኖራቸውን ፤ ይህም ደግሞ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ አለማወቃቸውን ይናገራል። ከዚህ ምንረዳው በዚህ ዘመን እግዚያብሄር ዝም ማለቱን ይህም ማለት ቀጥታ ነብያት አለመኖራቸውን ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በነኛ ሳሙ 3 ላይ በዚያ ዘመን የእግዚያብሄር ቃል ብርቅ እንደነበር ፤ ራዕይም ይገለጥ እንዳልነበር ይናገራል። ምዕራፉን በዚህ መንገድ የሚከፍትልን ቀጥሎ እግዚያብሄር መልእክት የሰጠው ነብይ እንደተነሳ ሊነግረን መሆኑ በቀጣዮቹ ቁጥሮች ማረጋገጥ ይቻላል። ከዚህም በዚያ ዘመን ነብያት አለመኖራቸውን ይህም ማለት ደግሞ እግዚያብሄር ቃሉ ብርቅ እስኪሆን ድረስ ዝም ብሎ እንደነበር ያሳውቀናል። ከዚህ በዘለለ በትንቢተ አሞፅ ላይም እግዚያብሄር የቃሉን ርሀብ እንደሚሰድ ማለትም በዝምታው እንደሚቀጣቸው ሲናገር እንመለከታለን። በዚህ ሁሉ እግዚያብሄር በዘመናት ውስጥ ነብያትን ማያስነሳበትና ዝም የሚልበት ጊዜያት መኖራቸውን ፤ ይህም ደግሞ ከሚልኪያስ ዘመን ባለው ጊዜ ብቻ የተከሰተ አዲስ ነገር እንዳልሆነ እንረዳለን።

ከላይ እንደተመለከትነው በአይሁድ ማህበረሰብ ዘንድ ከዘካሪያስ ዘመን በኋላ ነብያት እንዳልተነሱ እግዚያብሄርም መልእክትን እንዳልሰጠ ይታመናል። ይህ ዘካሪያስ በዜና መዋዕል 24 የተገለፀልን በእግዜር ቤት አደባባይ የተገደለው ነብይ ነው። ይህም ደግሞ ከክርስቶስ በፊት በዚሁ "የዝምታው ዘመን" በተባለው ዘመን ውስጥ ባሉ ምንጮች የተመሠከረ በመሆኑ ጉዳዩን ይበልጥ ተአማኝ ያደርገዋል። ከነዚህም መሀከል መቃብያን ተጠቃሹ ነው። በነኛ መቃብያን 4:48 እንዲህ ተቀምጧል ;

"And they thought it best to tear it down, so that it would not be a lasting shame to them that the Gentiles had defiled it. So they tore down the altar, 46 and stored

the stones in a convenient place on the temple hill until a prophet should come to tell what to do with them"

በዚህ ምዕራፍ ህዝበ እስራኤል ጠላት ተነስቶባቸው ከእርሱ ጋር ስላደረጉት ጦርነትና ድል ስለመንሳታቸው ፤ ነገር ግን ደግሞ ጠላቶች ቤተመቅደስንና ቅዱሳት ስፍራና መሠዊያውን እንዳወደሙባቸው ይናገራል። ቀጥሎም በመሰባሰብ ቤተመቅደሱንና መሰዊያውንም ለመስራትና ለማፅዳት መነሳታቸውን በአህዛብ ምክንያትም የረከሰውን መሰዊያ እንዳፈረሱትና በዚህ ላይ ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚነግራቸው ነብይም እስኪነሳ ድረስ በመቅደስ እንዳስቀመጡት ያስቀምጣል። ቀድመን እንደተመለከትነው ነብይ የእግዜርን ሀሳብና ፍቃድ የሚያሳውቅ ነውና በዚህ ዘመን ባለመኖሩ ምክንያት ምን ማድረግ እንዳለባቸው እግዛብሄር መልእክትን እስኪሰጣቸው ድረስ እንደሚጠብቁ ይናገራል። በዚህም ብቻ አይደለም በዚሁ መፅሀፍ በምዕራፍ 9:25-27 ላይ በዚሁ አውድ ተደግሞ እናነኛለን።

"Bacchides chose renegades and made them masters of the country. These sought out and hunted down the friends of Judas and brought them to Bacchides, who punished and derided them. There was great tribulation in Israel, the like of which had not been since the time prophets ceased to appear among them."

ቀድመን ከተመለከትነው ክፍል ከአምስት ምዕራፍ በኋላ በድጋሜ በእስራኤል መሀከል የነብያት መጥፋት እየታየ መምጣቱን በዚህም ደግሞ ታላቅ መከራ በእስራኤል እንደነበር ይናገራል። ዮሴፍ ወልደ ቆርዮን ይህንን የነብያት መጥፋት ቀጥታ ከእስራኤላውያን ከባቢሎን መውጣት አንስቶ እንደሆነ እንዳስቀመጠ ቀድመን ተመልክተናል። በድጋሜ ከአምስት ምዕራፍ በኋላ በዚሁ በ1መቃብያን 14:41 ላይ ተመሳሳይ እውነት ተቀምጦ እናነኛለን።

"This was because he had heard that the Romans had addressed the Jews as friends, allies, and brothers, that they had received Simon's envoys with honor, and that the Jewish people and their priests had decided the following: Simon shall be their leader and high priest forever until a trustworthy prophet arises. He shall act as governor over them, and shall have charge of the sanctuary, to make regulations."

ከዚህ መፅሀፍ ጋር ተነፃፃሪነት ባላቸው በዓዛርያስ ፀሎትና በ2ተኛ ባሮክ ይህንን እውነት ማረጋገጥ እንችላለን።

2ተኛ ባሮክ | 2 Baruch

"... But now, the righteous have been assembled, and the prophets are sleeping. Al-so we have left our land, and Zion has been taken away from us, and we have noth-ing now apart from YAHWEH the Mighty One and HIS Torah."[31]

Prayers of Azariah

---

31 2 Baruch 85:3

"In our day we have no ruler or prophet or leader, no burnt offering, or sacrifice, or oblation, or incense, no place to make an offering before you and to find mercy." [32]

ከላይ የተመለከትናቸው ባጠቃላይ የአይሁድን አቋም የሚወክሉ የራሳቸው ምንጮች ናቸው። ይህ ብቻ ግን አይደለም! አይሁዳዊ የሆነው የታሪክ ፀሀፊ ዮሴፍ ወልደ ቆርዮንም በዚህ ላይ ያስቀመጠው ነገር አለ።

" Our history has been written since Artaxerxes very thoroughly, but it has not been considered of equal authority with the earlier records by our forefathers, be-cause there has not been an exact succession of prophets since that time."[33]

ጆሴፈስ ስለ 22ቱ መፅሀፍት ከተናገረ በኋላ ከአርጤክስስ ዘመን በኋላ የተፃፉት መፅሀፍት ከ22ቱ እኩል ዋጋ እንደሌላቸው ይናገራል። ለዚህም ምክንያቱን ሲያስቀምጥ ስክትክት ወይም ቀጥ ያለ የነብያት ቅብብሎሽ ባለመኖሩ እንደሆነ ይናገራል {The failure of the exact succession of prophets}። ይህ አገላለፁ ለማለት የፈለገውን ነገር ለመረዳት የሚያከብድ ግልፅ ያልሆነ (Blurred or Vague) አገላለፅ ነው። ልሂቃንም ይህን ቀጥታ ለመረዳት ትንሽየሚያስቸግር እንደሆነ ይናገራሉ። ታድያ ጆሴፈስ ምን እያስተላለፈ እንደሆነ ለማወቅና እጅግ የተመጠነ (precise) መልእክቱን ለማግኘት መመልከት ያለብን ነገር አለ።

- ጆሴፈስ በRabbinical Judaism ውስጥ ያለ ግለሰብ እንደመሆኑ በዚህ ጊዜ በአይሁድ መህከል የነበረውን አቋም ይዞ የሚያንፀባርቅበት መጠን እጅግ የላቀ ነው። በዚህ ጊዜ ከአርጤክስስ ዘመን በኋላ ስለነበረው ጊዜና በነብያት ላይ በአይሁድ መህከል ያለውን አቋም ስንመለከት ልክ የመቃብያን እንዲሁም የሁለተኛ ባሮክ መፅሀፍት እንደሚመሰክሩት ከነሱ ጋር ተዛማጅ የሆነ አቋም ይህም ነብያት ከአርጤክስስ ዘመን በኋላ እንዳልነበሩና የእግዚአብሔር መንፈስ ከእስራኤል ተለይቶ እንደነበር ይቀበሉ ነበር። ይህ የጆሴፈስ አቋም ምን ሊሆን እንደሚችል ለማወቅ በር ከፋች ነው።

- ጆሴፈስ ይህን ፅሁፍ የሚፅፈው ለአይሁድ ታሪክና መፅሀፍት(literature) ጥንታዊነት በመቆምና አፒዮንን በመሞገት እንደመሆኑ ባጠቃላይ የሚያስቀምጠው ነገር እኛ ልናውቅ ከምንጥረው ታሪካዊ እውነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው።

- ጆሴፈስ Antiquity of Jews በተሰኘ መፅሀፉ የነኛ መቃብያን 9:27ን ክፍል Paraphrase በማድረግ የገለፀበትን ክፍል በምንመለከትበት ጊዜ ፤ እስራኤላውያን ከባቢሎን ግዛት ከወጡበት ጊዜ በኋላ ነብያት አለመነሳታቸውን ይቀበል እንደነበር እንገነዘባለን።

"Bacchides chose renegades and made them masters of the country. These sought out and hunted down the friends of Judas and brought them to Bacchides, who punished and derided them. There was great tribulation in Israel, the like of which had not been since the time prophets ceased to appear among them."[34]

---

32 Pr Azar 15

33 Against Apoin 1:41

34 1 Maccabees 9 : 25 - 27

" ..... who (bacchides) when he had , in the first place, tortured and tormented them at his pleasure, he, by that means, at length killed them. And when this ca-lamity of the Jews was become so great, as they had never had experience of the like since their return out of Babylon, those that remained of the companions of Judas ... "[35]

በዚህ paraphrasing ጆሴፈስ በነኛ መቃብያን ላይ "ነብያት መጥፋት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ " በማለት የሚገልፀውን ክፍል "እስራኤላውያን ከባቢሎን ከመውጣታቸው አንስቶ" በማለት ሲገልፀው ይታያል። ይህም ያለምንም ጥርጥር ጆሴፈ የነብያቱ መጥፋት እስራኤል ከባቢሎን መመለስ ጀምሮ እንደሆነ ይረዳ እንደነበር ትልቅ ፍንጭ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ማርከስ (Marcus) የተባለ ልሂቅ እንደሚለው ጆሴፈስ ከነኛ መቃብያን 9 Paraphrase በማድረግ ሲናገር ከዚሁ ሀሳብ ጋር ተያያዥ የሆነውንና ሀሳቡን የሚያጠናክርለት ክፍል ይኸውም ነ መቃ 4 :46 እያለለት ነገር ግን ያልጠቀሰበት ምክንያት በዛ ጊዜ ከሐጌ , ዘካሪያስና ሚልኪያስ በኋላ የነብያት አገልግሎት (Prophetic Inspiration) ተቋርጦ እንደነበር በሁሉ ዘንድ ተቀባይነት ያለው እውነት ስለነበር እንደሆነ ይናገራል። ይህም ብቻ ሳይሆን ጆሴፈስ በሌላ ስራው ታሪካዊያንና ነብያት ከጨረሱበት ነጥብ እሱ ስራውን እንደሚጀምር ተናግሯል። ይህ ከላይ የአይሁድ ታሪክን ከትበዋል ብሎ ያላቸው ነብያት ከአርጤክስስ ዘመን በፊት እንደነበሩ ከገለፀው ጋር ጥብቅ ተያያዥነት ያለው ይመስላል።

እነዚህን ሶስት መሠረቶች እንደመነፅር በመጠቀም ጆሴፈስ የተሰካካ የነብያት ስለአለመኖር ሲናገር እያለ ያለው ከአርጤክስስ ዘመን በኋላ መልእክትን ከእግዜር ተቀብለው ሊያስላልፉና በእግዜር መንፈስ በመነዳት መፅሀፍትን ሊፅፉ የሚችሉ ልክ ከአርጤክስስ ዘመን በፊት እንዳሉ ያሉ ነብያት እንዳልነበሩ ይቀበል እንደነበርና በዚህም ምክንያት ከአርጤክስስ ዘመን በኋላ የተፃፉትን መፅሀፍት ከዚህ በፊት ከተፃፉት እኩል ተአማኒነትንም ተቀባይነት ሊኖራቸው እንደማይገባ እየተናገረ እንደሆነ መገንዘብ እንችላለን።

በዚህ የጆሴፈስ ማስረጃ ላይ ስቲፈን ኩክ የተባለ ልሂቅ እጅግ ተፅእኖ በፈጠረ ስራው (L. Stephen Cook) ጆሴፈስ በዚህ ንግግሩ ውስጥ "exact" በማለት የተጠቀመውን ቃል በፅሁፎቹ ውስጥ ከተጠቀመበት ወጥ የሆነ አጠቃቀም አንፃር በዚህም ስፍራ "the exact succession of prophets" በማለት የገለፀው ጥራቱን ያልጠበቀ ወይም መጣ ጠፋ አይነት አካሄድ የነበረው ቅብብሎሽ መኖሩን መግለፁ ሳይሆን ያልተቋረጠና ወጥ የሆነ ተከታታይነት ያለው የነብያት መተካካት አለመኖሩን እየገለፀ እንደሆነ ይናገራል።

በዚህ ሀሳብ ላይ ከሚነሱ ሙግቶች መሀከል አንዱ በሉቃስ ምዕራፍ ሁለት ላይ የተገለፁትን ሁለት ሰዎች በመጥቀስ የሚቀርብ ነው። እነዚህም ስምኦንና ሐና ናቸው። ስምኦን የእስራኤልን መፅናናት የሚጠባበቅ ትጉህና ፃድቅ በመንፈስ ቅዱስም መሲሁን እንደሚያይ ተረድቶ ተስፋ የነበረው ሰው ነበር። ሀና ደግሞ ስለተወለደው መሲህ እያመሰገነች የእየሩሳሄምን ቤዛ ለሚጠባበቁ ስለሱ የምትናገር ነብይት ነበረች። በዚህ ክፍል ስምኦን መሲሁን እንደሚያይ በመንፈስቅዱስ እንደተረዳ እንዲሁም ሀናም ቀጥታ ነብይት እንደነበረች ከተነገረን ይህ ነብያት አልነበሩም ፤ እግዚያብሄርም መልእክትን አልሰጠም ነበር ከሚለው እሳቤ ጋር እንዴት የሚሄድ ነው ?

በመጀመሪያ መረዳት ያለብን በአይሁድ እምነት ነብያት የጠፉት ከዘካርያስ ዘመን አንስቶ ነው ይህም ማለት ደግሞ እስራኤላውያን ከባቢሎን ከተመለሱበት ጊዜ ጀምሮ የሆነ ነው። በሉቃስ መፅሀፍ የተቀመጡልን ሰዎች የሚወክሉት ከዘካርያስ ዘመን አንስቶ መሲሁ እስከተወለደበት የነበሩትን ዘመናት ሳይሆን በተናጥል መሲሁ የተወለደበትን ጊዜ ብቻ ነው። በዚህ ጊዜያት እግዚያብሄር መልእትን መስጠት ጀመረ ወይም ነብያት ተነሱ ማለት

[35] Antiquity of Jews , Book I , Chptr I , I (ሙሉን እንዲነበብ ይመከራል)

በጭራሽ ባለፉት ረዥም ዘመናት ይሄውኑ ክስተት ነበር ማለት አይደለም። ስለዚህ ከመጀመሪያው ይህ ሙግት ውድቅ የሚሆነው የቀረበውን የሙግት ክስተት ዘመን ያልጠበቀ በመሆኑ ነው።

የሰው ልጅ በኤደን ባለመታዘዝ ከወደቀበት እለት አንስቶ እግዚአብሔር ስለ መሲሁን መምጣት ተስፋ ሲሰጥ ነበር። እግዚያብሄር ይህ መሲህ የሚመጣበትን የራሱን ወገን በአብርሀም በኩል አድርጎ የእስራኤልን ህዝብ ከመረጠ በኋላም በተደጋጋሚ በግልፅም ይሁን በተዘዋዋሪ ስለመሲሁ መምጣት ለመረጣቸው ህዝብ ተስፋን ሲሰጣቸውና ሲያስታውቃቸው ነበር። እነኚህም ህዝብ መሲሁን በጉጉትና በላቀ ተስፋ ይጠባበቁ ነበር። እግዚያብሄርም ይህን የሰጠውን ተስፋ ሊፈፅም በወሰነው ዘመንና ሰአት አደረገው። ስምኦንና ሀናም የዚህ አካል ናቸው። እግዚአብሔር የዘመናት አጀንዳውን ሊፈፅም ሲነሳ መሲሁን ከመላኩ በፊት ለመሲሁ መንገድ የሚሆኑ ሰዎችን አስነስቶ ነበር። ለምሳሌ ዮሐንስ የእግዚአብሔር መንግስት መቅረቧን እየሰበከና ንስሀ የገቡትን እያጠመቀ የመሲሁን መንገድን የሚጠርግ ነበር። በሉቃስ ምዕራፍ አንድና ሁለት ላይ የተቀመጡልን ሰዎችም ከዚሁ አንፃር መታየት ያለባቸው ናቸው። ዘካርያስ ፤ ኤልሳቤጥ ፤ ዮሐንስ ፤ ማርያም ፤ ዮሴፍ ፤ ስምኦን ፤ ሀና .. ባጠቃላይ እነዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ቀድሞ በነብያት የተናገረውንና የተሰጠውን ተስፋ ሊፈፅም በወሰነው የመጨረሻ ዘመን በመሲሁ መምጣት ምክንያትነት የተገለገለባቸው የሀዲሱ የእግዜር የምህረት ኪዳን መክፈቻዎች ናቸው።

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው በአይሁዳውያን መሀከል እግዚአብሔር ዝም የሚልበት ይህም ማለት ደግሞ ነብያት የሚጠፉበት ጊዜያት ነበሩ። የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ እስኪሆን ድረስ እግዜሩ መልእክትን የማይሰጥበት ፤ ከዚህም ሲብስ ደግሞ የቃሉን ርሀብ የሚሰድበት ዘመን እንደሚመጣ እግዚአብሔር የተናገረበትን ክፍል ተመልክተናል። ይህ ማለት በዘመናት ውስጥ እግዚአብሔር ዝም ሊል ይችላል። ከቅዱሳት መፅሀፍት እንደምናረጋግጠው ከዝምታው በኋላ ግን መናገርንና መፈፀምን ይቀጥላል። ስለዚህ የጥያቄው መልስ ነብያት አልነበሩም ፤ የእግዚአብሔር መንፈስም መልእክትን አልሰጠም የተባለበትን ዘመን ሀናና ስምኦን የሚወክሉ ሳይሆኑ እንደውም እነርሱ የዚህ የዝምታ ዘመን መዝጊያዎችና የእግዚአብሔር ዘላለማዊ የመጨረሻ እቅድ መፈፀሚያ መንገዶች ናቸው የሚል ነው። ይህን እውነት ከቤተክርስቲያን አበው መሀከል እውቅ የሆነው አውግስጢኖስ እንዲህ ያስቀምጠዋል :-

"Now during the whole period after the return from Babylonia , after Malachi , Haggai and Zacharias who were prophets at the time and Ezra , they had no prophets until the savior's Coming , exept the other Zechariah the father of John , and his wife Elizabeth , when christ's nativity was now at hand and after his birth the old simeon and anna a widow and already advanced in age and john himself , the last among them..... But the prophecies of these five are known to us from the
Gosple , in which the virgin herself , the mother of the lord is found to have proph-esied before john did."[36]

N.M. Flanagan የተባለ ልሂቅ ሉቃስ በወንጌሉና በሐዋርያት ስራው ወንድና ሴትን ከ13 የማያንስ ጊዜ እንዳጣመረ ያስቀምጣል።[37] በዚህም ላይ በመመስረት Larry R. Helyer የተባለ ልሂቅ በሉቃስ መፅሀፍ ውስጥ ወንድና ሴትን በተደጋጋሚ መጣምሩ የአጋጣሚ ጉዳይ እንዳልሆነ ይልቁኑም በኢዮኤል 2:28 ላይ ወንዶችና ሴቶች ትንቢትን እንደሚናገሩ የተተነበየው ትንቢት አካል የለበሰባቸው እንደሆኑ እንዲሁም ሁሉም አዲሱን የእግዚአብሔር የማዳን ስራ የሚናገሩ እንደሆኑ ፤ በዚህም ደግሞ ቀድሞ በሁሉ ላይ እንዲገዙ

36 Civ 17.24

37 "The Position of Women in the Writings of St. Luke", *Marianum* 40 (1978): 292–93

የተሰጣቸውን የመለኮት ፍቃድና ፍላጎት እንደተረዱ ይናገራል።[38] ከዚሁ ጋር በተያያዘ Gary Smith የተባለ ልሂቅ በዚሁ በነብያት ላይ ነጥሎ በሰራው ሰፋ ያለ ስራው ውስጥ ሉቃስ ላይ በመመስረት በዘረዘራቸው የሀዲስ ኪዳን የመጀመራያ የነብያት ዝርዝሮች ውስጥ ስምአንንና ሀናን ከነ ዮሐንስ ፣ ዘካርያስ ፣ ድንግል ማርያምና ኤልሳቤጥ ጋር በአንድነተ አካቷቸው የብሉይ ወይም የዝምታው ዘመን አካላት ሳያደርጋቸው አስቀምጧቸዋል።[39]

ሌሎች ምንጮ

- ✓ በታልሙዳቸዉ

"And more than they, my son, beware; making many books has no end, and study-ing much is a weariness of the flesh."

SEDER OLAM RABBAH 30

“After the letter prophets Haggis , Zacharias and Malachi had died , the Holy spir-it departed from israel , yet they were still able to avail themselves to bath kol.”[40]

Midrash And Tosefta

ሚድራሽና ቶሴፍታ አይሁዳውያን በጠነከረ ባህላቸው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን አፋዊ ባህል በፅሁፍ ያስቀመጡበት ፅሁፍ ነው። በዚህም ተመሳሳይ እውነት እናገኛለን!

- ✓ Tosefta

"... Neither the books of Ben Sira nor any of the books written thereafter [in post-prophetic times] render the hands unclean "[41]

“render the hands unclean” ማለት በአጭሩ የአምላክ ቃል - Inspired ናቸው ማለት ነው! አይሁዳውያን የሚጠቀሙት አገላለጽ ነው! ስለዚህ ይህ ማስረጃ እያለን ያለው በፀጥታው ዘመን የተፃፉት መፅሀፍት ሁሉ የአምላክ ቃል አይደሉም ነው።

- ✓ Midrash

38 what about ana , internet article

39 Prophet - International Standard Bible Encyclopedia, 3rd ed. , ed. G. W. Bromiley

40 Babylonian Talmud , YOMA 98

41 Yad. ii. 13, ed. Zuckermandel, p. 683

The Midrash forbids adding another book such as that of Ben Sira or Ben Tigla to the twenty-four books; but says they may be read.

" And more than they, my son, beware; making many books has no end, and stud-ying much is a weariness of the flesh. " [42]

7 - የሶስትዮሽ አቀማመጥ - JEWS TRADITIONAL THREEFOLD STRUCTURE

አይሁዳውያን መፅሀፍቶቻቸውን የሚያስቀምጡበት የሶስትዮሽ አቀማመጥ ባህል አላቸው። ይህን ያነሳሁበት ምክንያት ይህ ባህላዊ አቀማመጣቸው በራሱ 7ቱን መፅሀፍት ሙሉ ዝርዝር ስለማያካትትና ይህም ላለመቀበላቸው ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ ስለሚችል ነው። ይህ አቀማመጣቸው ደግሞ ከክርስቶስ ልደት በኋላ የመጣ ሳይሆን ከዛ በፊት እስከ 130BC ወደኋላ የሚዘልቅ መሆኑ ይህ ለዚህ ትልቅ ቦታና አፅንኦት እንዲሰጠው ያደርገዋል።

❖ PROLOGUE OF ECCLESIASTICS

Ben Sira የፃፈውን የሲራቅ መፅሐፍ ፤ የልጅ ልጁ ራሱን መፅሀፍ ከእብራይስጥ ወደ ግሪክ ባስተረጎመ ጊዜ በመግቢያው ላይ ከአባቶቻቸው የተላለፈላቸውን መፅሀፍት በሶስዮሽ አቀማመጥ አስቀምጧል። እንግዲህ ይህ ከክርስቶስ ልደት 130 አመት በፊት የተፃፈ እጅግ ጥንታዊው ማስረጃ ነው።

"Whereas many and great things have been delivered unto us by the Law and the Prophets and the others (Hagiographa) that have followed in their steps ... my grandfather Jesus, having much given himself to the reading of the Law and the Prophets and the other Books (hagiographa) of the fathers and having gained great familiarity therein,... "[43]

❖ ፊሎ - Philo

የአይሁድ ፈላስፋ የሆነው የእስክንድርያው ፊሎ ደግሞ The Contemplative life በተሰኘው መፅሀፉ የሚቀበሏቸው መፅሀፍትን በሶስዮሽ አቀማመጥ አስቀምጧል። ከዚሁም ጋር ሌሎች መፅሀፍቶችም መኖራቸውን ሳይናገርም አላለፈም።

---

[42] Midrash Eccl. xii. 12

[43] PROLOGUE OF ECCLESIASTICS

"(the) Laws, and (the) Oracles given by inspiration through (the) Prophets, and (the) Psalms (Hagiographa), and the other books whereby knowledge and piety are increased and completed , ..."[44]

- **ቁምራን** - Qumran (Dated c. 150 B. C.)

"For on account of [these things] we have [written] for you that you may perceive in the book o f Moses and in the words of the prophets and in David and in the words o f the days (= Chronicles)] from generation to generation ."[45]

- **ኢየሱስ**

ሚገርም ሁኔታ ኢየሱስ ራሱ በሉቃ 24;44 ላይ በዚህ በአይሁዳውያን ባህላዊ የሶስትዮሽ የመፅሀፍ አቀማመጥ መሠረት በማድረግ ተናግሯል።

" እርሱም፦ ከእናንተ ጋር ሳለሁ <u>በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም</u> ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። "

ሉቃስ 24፥44

አይሁዳውያን በዚህ ባህላዊ የሶስትዮሽ አቀማመጣቸው የሚያስቀምጧቸው መፅሀፍት ውስጥ 7ቱ መፅሀፍት እንደሚጠቃለሉ የሚያስረግጥ ምንም ማስረጃ የለም። ይልቁኑ ከራሳቸው ከአይሁዳውያን ከላይ ከተጠቀሱት ሙሉ ምንጭ ከብዙም የአይሁድን አም ካንፀባረቁ ቤተክርስቲያን አባቶች (በተለይ ከአይሁድ ጋር ቅርበት ከነበራቸው) የመፅሀፍ አቀማመጥ 24ቱን መፅሀፍት የሚመለከት እንደሆነ ይረጋገጣል።

ከላይ ካየናቸው ጥንታዊ የአይሁድ ምንጮች ምስክርነት ተነስተን 7ቱ መፅሀፍት በአይሁዳውያን ዘንድ እንደ አምላክ እስትንፋስ (as Inspired scripture) ተቀባይነት እንደሌላቸውና ይልቁኑ ተቀባይነት ያላቸው 24ቱ መፅሀፍት እንደሆኑ እርግጠኛ መሆን እንችላለ።

44 De Vita Contemplativa , 25.

45 4Q MMT (Miqsat Macase haTorah) B, II,

የቤተክርስቲያን ታሪክ በቀኖና ላይ | CHURCH HISTORY

የብሉይ መፅሀፍት ቀዳሚ ተደራሽና የመጀመሪያ ባለቤት አይሁዳውያን ቢሆኑም በክርስቶስ ምክንያት በክርስቲያኖች ተወርሶ የኛም ንብረት ሆኗል። እግዚአብሔር ከጥንት በመረጣቸው በአይሁድ በኩል አድርጎ በዘመናት ውስጥ ለአለም የሚሆን መልእክትን ሲያፅፍ እንደነበር ፤ የሰው ልጆችንም ያለልዩነት ለማዳን የገባውን ቃል ሊፈፅም የተጓዘበትን መንገድ እኛም አህዛቦች እናውቅ ዘንድ በዚሁ ብሉይ መፅሀፍት ሆኖልናል። ኢየሱስ አገልግሎት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በጊዜው ከነበሩ ከአይሁድ ሊቀካህናት ፤ ፀሀፍትና መላው ማህበረሰብ ጋር ሲነጋገር ይጠቀም የነበረው ይሄንኑ የብሉይ መፅሀፍ ነበር። እርሱም ብቻ ሳይሆን ሐዋርያቱ በአገልግሎታቸው ውስጥ ይጠቀሙ የነበሩት መፅሀፍት ይሄው የአይሁድን የብሉይ መፅሀፍ ነበር። በአጭሩ የቤተክርስቲያን የመጀመሪያ መፅሀፍ ብሉይ ኪዳን ነበር። ዛሬ ላይ የመፅሐፍ ቅዱስን ቀኖና ለማወቅ ወደ ኋላ በምንጓዝበት ጉዞ ውስጥ መገንዘብ ያለብን ትልቅ ነጥብ ከአንድ ነጠላ ማስረጃ ተነስተን ሙሉ ድምዳሜ መስጠት እንደማንችል ነው። ከሀሳቡ ጥልቀትና መሠረታዊነት አንፃር ብዙ ምልከታዎችንና ማስረጃዎችን አገላብጦና አንዱን ከአንዱ ፈትሸን ሁሉን ያማከለ ድምዳሜ መስጠት አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው። በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የብሉይ መፅሀፍት የነበራቸውን ስፍራና አቀባበል ለማወቅ ሶስት ጉዳዮችን መመልከት ግድ ይለናል። በሚገርም ሁኔታ በ81ዱ ወይም በ73ቱ ውስጥ ብቻ ያሉት 7ቱ መፅሀፍት የነበራቸውን እይታና አጠቃቀም ወደኋላ ሄደን ሰፊውን የቤተክርስቲያን ታሪክ ስናጤን ከጊዜ ወደጊዜ ፤ ከዘመን ወደዘመን እያደገ የመጣ ፤ ወጥነት የሌለውና እጅግ በውዝግብ የተሞላ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህንን የምናረጋግጠው ደግሞ ቀጥለን በምንመለከታቸው ሶስት መነፅሮች በኩል ነው።

- ጉባኤያት (Church Councils)
- በቤ/ክ አባቶች ቀጥታ የተቀመጡ ዝርዝሮች
- የቤ/ክ አባቶች አጠቃቀም (Quotations)

ጉባኤያት | Church Councils

በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የመፅሀፍት ቀኖና ያስቀመጡ ጉባኤያት በዋነኝነት ሶስት ናቸው። እነዚህም የሮሙ ጉባኤ ፤ የሂፖ ጉባኤ እና የካርቴጅ ጉባኤ ናቸው። ቀጥለን እንደምንመለከተው በነዚህ ጉባኤያት ቀኖናዊ የሆኑ የአምላክ እስትንፋስ መፅሀፍት በዝርዝር ተቀምጠዋል። እነዚህ ጉባኤያት ከግለሰብ የዘለለና ሰፋ ያለን የክርስቲያኑን ማህበረሰብ እሳቤ ሊያንፀባርቅ የሚችል ቢሆንም በዚህ መሀከል ራሱ ያለውን ወጥነት ማጣት እንመለከታለን።

1. የሮሙ ጉባኤ - Council of Rome

“Likewise it has been said: Now indeed we must treat of the divine Scriptures, what the universal Catholic Church accepts and what she ought to shun. The order of the Old Testament begins here: Genesis one book, Exodus one book, Leviticus one book, Numbers one book, Deuteronomy one book, Josue Nave one book, Judges one book, Ruth one book, Kings four books, Paralipomenon [i.e. Chroni-cles] two books, Psalms one book, Solomon three books, Proverbs one book, Eccle-siastes one book, Canticle of Canticles one book, likewise Wisdom one book, Eccle-siasticus [i.e. Sirach] one book. Likewise the order of the Prophets. Isaias one book, Jeremias one book, with Ginoth, that is, with his Lamentations, Ezechiel one book, Daniel one book, Osee one book, Micheas one book, Joel one book, Abdias one book, Jonas one book, Nahum one book, Habacuc one book, Sophonias one book, Aggeus one book, Zacharias one book, Malachias one book. Likewise the order of the histories. Job one book, Tobias one book, Esdras two books [i.e. Ezra & Nehe-miah], Esther one book, Judith one book, Machabees two books.”[46]

ይህ የሮሙ ጉባኤ በጊዜው የሮማ ጳጳስ በሆነው ደማስቆ መሪነት በ382 ዓ/ም የተካሄደ ጉባኤ ሲሆን በጉባኤውም ቀድሞ በተካሄደው በቁስጥንጥንያ ጉባኤ ላይ የነበሩ አበው ድጋሜ እንዲሰበሰቡ ታስቦ ከሚላን መንበረ ጵጵስና ደብዳቤ ለአብያተክርስቲያናት ተልኮ ነበር። በሩቅ ያሉት የምስራቅ አብያተክርስቲያናት ለቀደመው ጉባኤ ረዘም ላለ ጊዜያት ጉዞ ሲያደርጉ ስለነበርና የአቅራቦት ማነስ ስለነበረ ሙሉ ለሙሉ ሊገኙ አልቻሉም ነበር። ነገር ግን ሶስት ተወካዮችን እነዚህም ሲራከስ (syriacus) ፤ አውስጦስ (Eusebius) እና ፕሪስኪያን (Priscian) በመላክ ብዙ ቁጥር ያላቸው አበው የተገኙበት ተካሄደ ጉባኤ ነው። ይህ ጉባኤ አለማቀፋዊ ጉባኤ (Ecumenical Council) ሳይሆን ሀገራዊ ጉባኤ (Local Council) ነው። በዚህ ጉባኤም ከላይ እንደተጠቀሰው የአምላክ እስትንፋስ የሆኑትን መፅሀፍት ዘርዝረው አስቀምጠዋል። በዚህ ዝርዝር ውስጥም ከ7ቱ መፅሀፍት አምስት መፅሀፍትን አካተዋል። እነዚህም ደግሞ የጥበብ ፤ የጦቢት ፤ የዮዲት ፤ የመቃብያንና የሲራቅ መፅሀፍት ናቸው።

2. የካርቴጅ ጉባኤ - Council of Carthage

“It was also determined that besides the Canonical Scriptures nothing be read in the Church under the title of divine Scriptures. The Canonical Scriptures are these: Genesis, Exodus, Leviticus, Numbers, Deuteronomy, Joshua the son of Nun,

46 https://taylormarshall.com/2008/08/decree-of-council-of-rome-ad-382-on.html

Judges, Ruth, four books of Kings, 3 two books of Paraleipomena, 4 Job, the Psal-ter, five books of Solomon, 5 the books of the twelve prophets, Isaiah, Jeremiah, Ezechiel, Daniel, Tobit, Judith, Esther, two books of Esdras, 6 two books of the Maccabees ”[47]

በ393 ዓ/ም የሂፖ ጉባኤ በሰሜን አፍሪካ ተካሂዶ ነበር። ይህ ጉባኤ የክርስቲያኖች ቀኖናዊ መፅሀፍትን ዘርዝሮ ያስቀመጠና ያፀደቀ የመጀመሪያው ጉባኤ ነው። ይህ ጉባኤ አለማቀፋዊ ጉባኤ (Ecumenical Council) ሳይሆን ሀገራዊ ጉባኤ (Local Council) ነው። በዚህ ጉባኤ የተቀመጡት ውሳኔዎች ቀጥሎ በተደረገው የካርቴጁ ጉባኤ (397 ዓ/ም)ተደግመዋል። በርግጥ ለሂፖ ጉባኤ በቂ የሆኑ ጥንታዊ እደ ክታባት ስሌሉ በካርቴጁ በኩል የምንመለከተው ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው በዚህ ጉባኤ ቀኖናዊ የሆኑ የአምላክ እስትንፋስ መፅሀፍት ተዘርዝረው ተቀምጠዋል። በዚህም ውስጥ ከ7ቱ መፅሀፍት አራት መፅሀፍት ተካተው ተቀምጠው እናገኛለን። እነዚህም የጥበብ ፣ የጦቢት ፣ የዮዲትና የመቃብያን መፅሀፍት ናቸው። አንዳንዶች ዕዝራ ሱቱኤልም (1 Esdras or Esdras A) ተካቷል የሚሉ አሉና ምናልባት እርሱንም ከቆጠርን አምስት ይሆናሉ!

3. የሎዶቅያ ጉባኤ - Council Laodicean

ቀኖናዊ ቅዱሳት መፅሀፍትን አስቀምጧል ተብሎ የሚታሰበው ሌላኛው ጉባኤ የሎዶቅያ ጉባኤ (363 – 364 ዓ/ም) ነው። በዚህ ጉባኤ ውሳኔ በ60ኛው ድንጋጌ ላይ ቀኖናዊ የሆኑ የአምላክ እስትንፋስ መፅሀፍት የተቀመጡ ሲሆን በዚህ ዝርውር ውስጥ ከ7ቱ አፖክሪፋል መፅሀፍት ምንም አላካተተም። ነገር ግን 60ኛው ድንጋጌ በብዙ እደክታባት ላይ ባለመገኘቱ ምክንያት ልሂቃኖች በእውነተኝነቱ ላይ ጥርጣሬ አላቸው። የዚሁ ጉባኤ 59ነኛውን ድንጋጌ ስንመለከት ግን ቀኖናዊ ያልሆኑ ማንኛውም መፅሀፍት በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዳይነበቡ ይልቁኑ ቀኖናዊ የሆኑ መፅሀፎት ብቻ እንዲነበቡ ይደነግጋል።[48]

4. የቱሩሎ ጉባኤ

“Let the following books be counted venerable and sacred by all of you, both clergy and laity. Of the old testament , five book of moses , Genesis, Exodus, Leviticus, Numbers, Deuteronomy; of johsua the son of nun, one; of the Judges, one; of Ruth, one; of the Kings, four; of the Chronicles of the book of the days, two; of Ezra, two; of Esther, one; [some texts read of Judith, one;] of the Maccabees, three; of Job, one; of the Psalter, one; of Solomon, three, viz.: Proverbs, Ecclesiastes, and the Song of Songs; of the Prophets, twelve; of Isaiah, one; of Jeremiah, one; of Ezekiel, one; of Daniel, one. But besides these you are recommended to teach your young persons the Wisdom of the very learned Sirach.” [49]

ይህ ጉባኤ በሰባተኛው ክፍለዘመን የተካሄደ ሲሆን የብሉይ ኪዳንን ቅዱሳት መፅሀፍት በዚህ መልኩ ዘርዝሮ አስቀምጧል። በዚህም ውስጥ ከ7ቱ መፅሀፍት ሶስት መፅሀፍት ብቻ ተካተው እናገኛለን።

---

46 https://www.newadvent.org/fathers/3816.htm OR http://www.bible-researcher.com/carthage.html

47 https://www.newadvent.org/fathers/3806.htm

48 https://www.newadvent.org/fathers/3820.htm , canon 85

የሐዋርያት ቀኖና | Apostolic Canon

“Of the old testament, five books of moses, Genesis, Exodus, Leviticus, Numbers, Deuteronomy; of Joshua the son of Nun, one; of the Judges, one; of Ruth, one; of the Kings, four; of the Chronicles of the book of the days, two; of Ezra, two; of Es-ther, one; [some texts read of Judith, one;] of the Maccabees, three; of Job, one; of the Psalter, one; of Solomon, three, viz.: Proverbs, Ecclesiastes, and the Song of Songs; of the Prophets, twelve; of Isaiah, one; of Jeremiah, one; of Ezekiel, one; of Daniel, one. But besides these you are recommended to teach your young persons the Wisdom of the very learned Sirach.”[50]

ይህ የሐዋርያት ቀኖና ከአንድ ግለሰብ በላይ የሆነን አቋም የሚያንፀባርቅ የአራተኛ ክፍለዘመን የሲሪያ ክርስቲያን ፅሁፍ ጥንታዊ ምንጭ ነው። ይህን ምንጭ ቀጥታ የሐዋርያት አድርገው የሚቀበሉ አሉ! በዚህ ምንጭ ውስጥ የብሉያትና የሀዲሳት መፅሀፍት የተዘረዘሩ ሲሆን በብሉያት ውስጥ ከ7ቱ መፅሀፍት 3ቱ ሲካተቱ እነዚህም መቃብያን ፣ ሲራቅና ዮዲት ናቸው ፤ በሀዲሳት ውስጥ ደግሞ የቀለሜንጦስ ሁለት መልእክት ተካተው ይገኛል።

ከላይ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በመፅሀፍ ቅዱስ ቀኖናዊ መፅሀፍት ላይ የነበረውን አቋም በጉባኤ ደረጃ እንዲሁም ቤተክርስቲያንን አቋም ሊያንፀባርቅ በሚችልን ጥንታዊ ምንጭ ተመልክተናል። የተመለከትናቸው ጉባኤያት በአንድ ክፍለ ዘመን ውውጥ የነበሩ ወይም የተካሄዱ መሆናቸው አፅንኦት ይሰጠው ዘንድ ይገባል። በሮሙ ጉባኤ እንደተመለከትነው ከ7ቱ አፖክሪፋል መፅሀፍት ወደ አምስት የሚሆኑ መፅሀፍት ተካተው እናገኛለን። እነዚህም ደግሞ የጥበብ ፣ የጦቢት ፣ የዮዲት ፣ የመቃብያንና የሲራቅ መፅሀፍት ናቸው። ይህ ማለት ከ7ቱ መፅሀፍት ሁለቱን መፅሀፍት ተጥለዋል ማለት ነው። ከጥቂት አመታት በኋላ በሂፖ ከዛም ደግሞ በካርቴጅ የተቀመጠውን አቋም ስንመለከት ደግሞ ከ7ቱ አፖክሪፋል መፅሀፍት አምስት መፅሀፍት ተካተው እናገኛለን። እነዚህም ደግሞ ጥበብ ፣ ጦቢት ፣ ዮዲት ፣ እዝራ ሱቱኤልና መቃብያን ናቸው። በነዚህም ደግሞ እንደምናረጋግጠው ከ7ቱ መፅሀፍት ሁለት መፅፍትን ጥለዋል። በሰባተኛው ክፍለዘመን የተካሄደውን የቱሩሎ ጉባኤና ከላይ ከተጠቀሱት ጉባኤያት ጋር በተመሳሳይ ዘመን ተቀባይነት የነበረውን የሐዋርያትን ቀኖና ስንመለከት ደግሞ ከ7ቱ አፖክሪፋል መፅሀፍት ሶስቱ ብቻ ተካተው እናገኛለን። እነዚህም ደግሞ የመቃብያን ፣ የዮዲትና የሲራቅ መፅሀፍት ናቸው። በነዚህ ደግሞ ከ7ቱ መፅሀፍት 5ቱን ተጥሎ እናገኘዋለን። የሎዶቅያው ጉባኤ አቋም አጠራጣሪነት እንዳለ ሆኖ ነገር ግን ምንም አለማስቀመጡን ደግሞ ተመልክተናል። በሮሙ ጉባኤ ከተካተቱት አፖክሪፋል መፅሀፍት የሲራቅ መፅሀፍ በካርቴጁ ጉባኤ ላይ አልተካተተም ፤ በሐዋርያት ቀኖና ላይ ደግሞ የዮዲትና የጦቢት መፅሀፍት አልተካተቱም። በካርቴጅ ጉባኤ ላይ ከተካተቱት መፅሀፍት ደግሞ እዝራ ሱቱኤል በሮሙ ጉባኤም ፡ በቱሩሎ ጉባኤም ፡ በሐዋርያት ቀኖና ዉስጥም አልተካተተም ፤ በተጨማሪም የጥበብና የጦቢት መፅሀፍት በሐዋርያት ቀኖና ላይ አልተካተቱም። በሐዋርያት ቀኖና ላይ ከተካተቱት አፖክሪፋል መፅሀፍት ደግሞ የሲራቅ መፅሀፍ በካርቴጁ ጉባኤ ላይ አልተካተተም። ከዚህ ምንገነዘበው የማያሻማው ግልፅ እውነት በአንድ ክፍለዘመን ውስጥ ባሉና በአጭር አመታት ልዩነት በተካሄዱ ትልቅ ስፍራ ባላቸው ጉባኤያት መሀከል እንዲሁም ከነዚህ ጋር በእኩልነት በሚነፃፀር ምንጭ መሠረት እንደምንመለከተው በ7ቱ መፅሀፍት ላይ የምናገኛቸው የመፅሀፍ ዝርዝሮች ወጥነት ያላቸውና ቋሚ አለመሆናቸውንና ይልቁኑ እንደውም በነዚህ በ7ቱ መፅሀፍት ላይ ወደ አንድ አሳማኝ ድምዳሜ የማያደርሱ የተለያዩ አወዛጋቢ አቋሞች በቤተክርስቲያን መሀከል መኖራቸውን ነው።

49 https://www.newadvent.org/fathers/3820.htm , canon 85

በሚገርም ሁኔታ ከላይ እንደተመለከትነው ከ7ቱ መፅሀፍት ራሱ ውዝግብ ያለባቸው ከአምስት ወይም ከስድስት ማይበልጡት መፅሀፍት ብቻ ናቸው። ጉባኤያቱ ሀገር አቀፋዊ ብቻ እንደመሆናቸው ደግሞ የጠቅላላውን ቤተክርስቲያን አቋም አያንፀባርቁምና በሌላ የክርስትና ክፍል ደግሞ የተለየ እይታ ሊኖር ለመቻሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ቤተክርስቲያን ያላት ወጥነት የሌለው ታሪክ ከግምት በላይ ያስጠረጥራል።

በቤተክርስቲያን አባቶች ቀጥታ የተቀመጡ ዝርዝሮች

1 MELITO OF SARDIS (170A.D)

"...having learned accurately the books of the old covenant, 1 set themdown and have sent themto you. These are their names: Five books of Moses - Genesis, Exo-dus, Numbers, Leviticus, Deuteronomy. Joshua the son of Nun, Judges, Ruth , four books of Kingdoms(Samuel & kings), two books of Chronicles. The Psalms of David, the Proverbs of Solomon (also called Wisdom), Ecclesiastes, the Song of Songs, Job. The Prophets: Isaiah, Jeremiah (adds Lementation) , the Twelve in a single book, Daniel, Ezekiel, Esdras (Ezra-Nehemiah)."[50]

ሜሊቶ በ170 ዓ /ም የሰርዴስ ሊቀ ጳጳስ የነበረ ፤ የመጀመሪያውንም የብሉይ መፅሐፍ ዝርዝር ያስቀመጠ ክርስቲያን ነው። ይህንንም ያስቀመጠው አናሲሞስ ለተባለው ወዳጁ በላከው ደብዳቤ ውስጥ ነበር። የብሉይንም መፅሀፍት ብዛት ለማወቅ ከሳርዲስ ወደ ምስራቅ (ፍልስጤም - Palestine) እንደሄደም ተዘግቦልናል። በሜሊቶ የመፅሀፍ ዝርዝር ውስጥ ከአስቴር በስተቀር በአይሁዳውያንና በኛ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሙሉ መፅሀፍት የሚገኙ ሲሆን በ8ነዱ ወይም በ73ቱ ውስጥ ከተካተቱት 7ቱ መፅሀፍት አንድም በዚህ ዝርዝር ውስጥ አልተጠቀሰም። አንዳንዶች የጥበብንና የእዝራ ሱቱኤልን መፅሀፍ እንዳካተተ ይሞግታሉ። ነገር ግን በዚህ ላይ ብዙ ቁጥር ያላቸው ልሂቃን ጥበብ በማለት የገለፀው የምሳሌ መፅሀፍ እንደሆነ እንዲሁም እዝድራስ (Esdras) በማለትም የጠቀሰው እዝራ-ነህምያን እንደሆነ ያስቀምጣሉ። ለአብነት ያህል ለመጥቀስ የNicene and Post-Nicene Fathers በተሰኘ እጅግ ሰፊና ትልቅ ስራው የሚታወቀው ልሂቅ ፊሊፕ ስካፍ ይህንን እውነት በስራው አስረግጦ አስቀምጧል።[51] በተጨማሪ ብሩስ (F.F. Bruce)[52] ፣ ሰንበርግ (Sundberg) [53] ፣ ራጀር (Roger Beckwith)[54] እና ሌሎችም ይህን ያስቀምጣሉ። የእዝራ-ነህምያውን (Esdras) ደግም የካቶሊክ ልሂቃን ሳይቀሩ የሚያስረግጡት እውነት ነው። ከዚህ አንፃር እኛም ሜሊቶ ከ7ቱ መፅሀፍት ምንም እንዳልጠቀሰ እናስረግጣለን። አስቴርንም ያላካተተበት ምክንያት በዛ ጊዜ በአይሁዳውያንም ሆነ በቤተክርስቲያን ዘንድ በቀኖናነቱ ዙሪያ የተለያየ አመለካከትና ጥርጣሬ ስለነበር ነው። ሜሊቶ ባስቀመጠው ዝርዝር ውስጥ ነጥሎ የነህምያንና የሰቆቃው ኤርሚያስን መፅሀፍ አልጠቀሰም። የዚህም ምክንያት በዛ ጊዜ የመፅሐፍ አቀማመጥ ነህምያ ከእዝራ ጋር ሰቆቃው ኤርሚያስ ደግሞ ከኤርሚያስ ጋር በአንድነት ስለሚቀመጡ ነው። ይህንም ከላይ የተጠቀሱት ልሂቃን ባጠቃላይ የሚያስቀምጡት ነው።

---

50 In Eusebius, Hist. Eccl. 4.26.12–14.

51 https://www.ccel.org/ccel/schaff/npnf201.iii.ix.xxvi.html

52 F.F. Bruce , Tge canon of Old testament , 71 (99)

53 A.C. Sundberg , The old testament of the early church (A study in Canon), 220 FN.

54 Roger Beckwith , The Old Testament Canon in the new testament church , 188

2 ORIGEN (185-254)

“lt should be stated that the biblical books, as the Hebrews hand them down, are 22, corresponding with the number oftheir letters .... The 22 books of the Hebrews are the following Genesis , Exodus , Leviticus , Numbers , Deuteronomy , Jesus the son of Nave , Judges and Ruth, among them in one book , the first and secondof Reigns, among them one , the third and fourth of Reigns in one of the Chronicles, the first and second in one , Esdras, first and second in one , the Book of Psalms , the Proverbs of Solomon , Ecclesiastes , the Song of Songs , Isaiah , Jeremiah, with Lamentations and the Epistle, in one , Daniel , Ezekiel , Job , Esther... And out-side these there are the Maccabees "[55]

አርጌን የቅዱሳት መፅሀፍትን ብዛትና ዝርዝር ያስቀመጠው ሌላኛው የቤተክርስቲያን አባት ነው። ይህ ሰው በመፅሀፍ ቅዱስ ቀኖናዋ ዙሪያ የጠለቀ እውቀት ነበራቸው ፤ ብዙ ስራዎችንም ሰርተዋል ተብለው ከሚጠቀሱ አባቶች መሀከል ቀዳሚው ነው። ቅዱሳት መፅሀፍትን ለማወቅ ባለው ፍላጎትም ወደ ፍልስጤም (Palestine) በመሄድ ከባለቤቶቹ ከአይሁዳውያን የተማረ ሲሆን የግሪክና የእብራይስጥ ቋንቋን ጠንቅቆ የሚያውቅ ነበር። የአርጌን የመፅሀፍ ዝርዝር ልክ እንደ ሜሊቶ በአውሲቢዮስ የተዘገበ ነው። በዚህ የመፅሃፍት ዝርዝር ውስጥ የ12ቱ ነብያት መፅሀፍት አልተጠቀሱም። ይህም በራሱ በአርጌን ወይም በአውሲቢየስ ምክንያት ሰነዶች በሚተላለፍበት ጊዜ የግልበጣ ስህተት እንደሆነ ልሂቃን ያስቀምጣሉ። በዛ ጊዜ የነዚህ መፅሀፍት ቀኖናዊነት በአይሁዳውያንም ይሁን በቤተክርስቲያን ዘንድ ጥርጥር የሌለው ጉዳይ ስለሆነና አርጌንም በሌሎች የተለያዩ ፅሁፎቹ ቀኖናዊ ስልጣናቸውን ስለመሰከረ እንዲሁም ደግሞ በአሁን ሰአት የጠፉ ማብራሪያዎችን ወይም ፍታቴዎችን (Commentaries) ፅፎበትም ስለነበር ነው። በዚህ ዝርዝሩ ውስጥ ተረፈ ኤርሚያስንና እዝራ ሱቱኤልን ያካትታል ፤ መቃብያን ከዚህ ውጪ እንደሆነም ያስቀምጣል።

2 ATHANASIUS

" There are, then, of the Old Testament, twenty-two books in number; for, as I have heard, it is handed down that this is the number of the letters among the He-brews; their respective order and names being as follows .... ***"56***

አትናቴዎስ በ39ነኛው የፋሲካ በአል ደብዳቤው ቀኖናዊ ስለሆኑ ቅዱሳት መፅሀፍት ፤ ቀኖናዊ ስላልሆኑ ነገር ግን በቤተክርስቲያን ሊነበቡ ስለሚችሉ መፅሀፍት እና ስለአፖክሪፋል መፅሀፍት በማብራራት አስቀምጧል። ባስቀመጠው ዝርዝር ውስጥም አስቴርን ሳያካትት ባሮክንና ተረፈ ኤርሚያስን ብቻ ያካትታል። በዚህ ላይ "አንደኛና ሁለተኛ እዝራ" ተብሎ የተገለፀው እዝራና ነህምያ እንደሆነ ልሂቃን ይናገራሉ። ለአብነት ያህል ብንመለከት ሀሪንግተን (Daniel J. Harrington) ይህን ያስቀምጣል።[57] ብሩስም ቢሆን እዝራና ነህምያን እንደሆነ አስቀምጧል።[58] አትናቴዎስ በሰባተኛው አንቀፅ ቀኖናዊ ያልሆኑ ነገር ግን ሊነበቡ ስለሚችሉ አምስት መፅሀፍትን ይጠቅሳል።

---

55 apud Eusebius, Eccles. Hist. 6.25 Or http://www.bible-researcher.com/origen.html

56 https://www.ccel.org/ccel/schaff/npnf204.xxv.iii.iii.xxv.html

57 Canon debate , p 199

58 F.F. Bruce , The canon of Old testament , p 118

4 CYRIL OF JERUSALEM

".. For of the Law the books of Moses are the first five, Genesis, Exodus, Leviticus, Numbers, Deuteronomy. And next, Joshua the son of Nave, 7 and the book of Judges, including Ruth, counted as seventh. And of the other historical books, the first and second books of the Kings 8 are among the Hebrews one book; also the third and fourth 8b one book. And in like manner, the first and second of Chroni-cles are with them one book; and the first and second of Esdras 8c are counted one. Esther is the twelfth book; and these are the Historical writings. But those which are written in verses are five, Job, and the book of Psalms, and Proverbs, and Ec-clesiastes, and the Song of Songs, which is the seventeenth book. And after these come the five Prophetic books: of the Twelve Prophets one book, of Isaiah one, of Jeremiah one, including Baruch and Lamentations and the Epistle; 9 then Ezekiel, and the Book of Daniel, the twenty-second of the Old Testament." [59]

በሚገርም ሁኔታ በዚህ ፅሁፉ ውስጥ ከመጀመሪያው ጀምረን ስናነብ ቄርሎስ ከክርስቶስ ልደት በፊት በሰባሊቃናቱ ስለተተረጎመው ትርጉም አንስቶ ዋነኛ ታሪኩን አስቀምጧል። ከዛም ከዚህ ከተተረጎሙት ትርጓሜዎች ውስጥ 22ቱ መፅሀፍትን በሐዋርያቱና በአባቶች እንደተላለፈላቸው ከዚም አልፎ በዛ ጊዜም ቤተክርስቲያን ውስጥ ተነባቢነት የነበራቸው እነዚህ እንደሆኑና ሌሎቹ አፖክራፋ ከዚህ ውጪ እንደሆኑ አስቀምጧል። እንግዲህ ይህ በመጀመሪያ ክፍለዘመን ክርስቶስና ሐዋርያቱ ሰባሊቃናቱን ይጠቀሙ ነበር ማለት ግዴታ የነቱ ሙሉ መፅሀፍትን እንደአምላክ እስትንፋስ ተቀብለው ነበር ማለት እንዳልሆን የሚያረጋግጥ እጅግ ትልቅ ማስረጃ ነው። ቄርሎስ በዘረዘራቸው መፅሀፍት ውስጥ ከ7ቱ መፅሀፍት ሶስት መፅሀፍት ብቻ ነው ያካተተው። እነርሱም እዝራ ሱቱኤል ፣ ባሮክ ፣ ተረፈ ኤርሚያስ።

5 GREGORY OF NAZIANZUS

"... First there is Genesis, then Exodus, Leviticus too. Then Numbers, and the First there is Genesis, then Exodus, Leviticus too. Then Numbers, and the Second Law. Then Joshua and Judges. Ruth is eighth. The ninth and tenth books [are] the acts of Kings,and [the eleventh is] Chronicles. Last you have Ezra. The poetic books are five: Job being first,then [the Psalms of] David; and three of Solomon, Ecclesiastes, Canticles and Proverbs. And similarly five of prophetic inspiration. There are the Twelve written in one book: Hosea and Amos, and Micah the third; then Joel, and Jonah, Obadiah, Nahum also, and Habakkuk, and Zephaniah, Haggai, then Zechariah, and Malachi. All these are one. The second is of Isaiah. Then the one called as an infant, Jeremiah, Then Ezekiel, and the gift of Daniel. I count therefore, twenty-two of the ancient books, corresponding to the number of the Hebrew letters." [60]

ግሪጎሪዮስ ዘእንዚናዙ በ4ተኛው ክፍለ ዘመን የነበረ ፤ በኒቂያ ጉባኤ በስላሴ ላይ ቀዳማዊ የአርዮስ ሞጋች የነበረ ሰው ነበር። የብሉይ መፅሀፍትን ብዛትና አይነትም "Concerning the Genuine Books of Divinely Inspired Scripture" በተሰኘው ፅሁፉ በግጥም መልክ ነው ያቀረበው። በዚህ ዝርዝር ውስጥ ግሪጎሪዮስ ዘእንዚናዙ የአስቴርን መፅሀፍ አላካተተም እንዲሁም ከ7ቱ መፅሀፍት ደግሞ የጥበብን መፅሀፍ ብቻ አካቶ እናገኛለን ፤ ከነዚህ ውጪ ያሉት ሁሉ ደግሞ እውነተኛ እንዳልሆኑ አስቀምጧል።

---

apud Eusebius, Eccles. Hist. 6.25 Or http://www.bible-researcher.com/origen.html

59 https://www.ccel.org/ccel/schaff/npnf204.xxv.iii.iii.xxv.html

6 JEROM

" And so there are also twenty-two books of the Old Law; that is, five of Moses, eight of the prophets, nine of the Hagiographa, though some include Ruth and Ki-noth (Lamentations) amongst the Hagiographa, and think that these books ought to be reckoned separately .... "[61]

ጀሮም በ346 ዓ/ም በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ የተወለደ ፤ የግሪክና የላቲን ስነፅሁፍ (Literature) ልሂቅ የነበረ ከዚህም አልፎ የእብራይስጡን መፅሀፍ ቅዱስን በጥልቀት ያጠና ፤ ለመጀመሪያ ጊዜም ብሉይን ወደ ላቲን የተረጎመ ሰው ነበር (Vulgate translation)። ብሉያትንም ለመተርጎም ሲነሳ በባለቤቶቹ በአይሁዳውያን ላይ መሠረት ማድረግ እንዳለበት ስለተረዳ ከራሳቸው ከአይሁዳውያን ምንጭ በመመርኮዝ (እራሱ እንደሚለው "Hebrew Variety") 24ቱን የብሉያትን መፅሀፍት ተረጎመ። በዚህም ትርጓሜው ከ7ቱ መፅሀፍት ቀኖናዊ አድርጎ አንድም አላካተተም ነበር። ይልቁንም እነዚህ ባጠቃላይ ቀኖናዊ እንዳልሆኑ አስቀምጧል። ከዚህ በተጨማሪ በሶስቱ የሰለሞን መፅሀፍት ሲተረጉም በመግቢያው ላይ የጥበብ የጦቢትና የመቃብያን መፅሀፍት ሊነበቡ የሚችሉ ቢሆኑም ዶግማዊም አስተምሆሮዎችን ልንመሰርትባቸው እንደማንችል አስቀምጧል።[62]

7 RUFINUS (340-410)

" Of the Old Testament, therefore, first of all there have been handed down five books of Moses: Genesis, Exodus, Leviticus, Numbers, Deuteronomy; then Joshua the son of Nun; the book of Judges together with Ruth; then four books of Kings, 2 which the Hebrews reckon two; Paralipomenon, 3 which is called the book of Days [Chronicles], and two books of Ezra, 4 which the Hebrews reckon one, and Esther; of the Prophets, Isaiah, Jeremiah, Ezekiel, and Daniel; moreover of the Twelve [minor] Prophets, one book; Job also and the Psalms of David, each one book. Solomon gave three books to the churches, Proverbs, Ecclesiastes, and Song of Songs. These comprise the books of the Old Testament. " [63]

ሩፊነስ የብሉይንና የሀዲስን መፅሀፍት ብዛትና አይነት "Exposition of the Creed " በተባለው ስራው ውስጥ አስፍሯል። በዚህም ዝርዝሩ ከ7ቱ መፀሀፍት አንድም አላካተተም። በሚገርም ሁኔታ ይህ ብቻ ሳይሆን ጥበብ ፤ ሲራቅ ፤ ጦቢትና መቃቢያን ቀኖናዊ መፅሀፍት እንዳልሆኑ በግልፅ አስቀምጧል።

8 AMPHILOCHUS OF ICONIUM

"For this reason I will state for you the divinely inspired books one by one, so that you may learn them clearly. I will first recite those of the Old Testament. The Pen-tateuch has Creation, then Exodus, and Leviticus, the middle book, after which is Numbers, then Deuteronomy. Add to these Joshua, and Judges, then Ruth, and of Kingdoms the four books, and the double team of Chronicles; after these, Esdras, one and then the second. Then I would review for you five in verse: Job, crowned in the contests of many sufferings, and the Book of Psalms, soothing remedy for the ..

---

[60] Canon debate , p 199

[61] F.F. Bruce , The canon of Old testament , p 118

[62] pud Eusebius, Eccles. Hist. 6.25 Or http://www.bible-researcher.com/origen.html

.. soul, three of Solomon the Wise: Proverbs, Ecclesiastes, Canticle of Canticles. Add to these the Prophets Twelve, Hosea first, then Amos the second, Micah, Joel, Obadiah, and the type of Him who three days suffered, Jonah, Nahum after those, and Habakkuk; and ninth, Zephaniah, Haggai, and Zechariah, and twice-named angel Malachi. After these prophets learn yet another four: The great and fearless Isaiah, the sympathetic Jeremiah, and mysterious Ezekiel, and finally Daniel, most wise in his deeds and words. With these, some approve the inclusion of Es-ther." [64]

ይህ የቤተክርስቲያን አባት ብዙ ፅሁፎችን ቢፅፍም ዛሬ እጃችን ላይ ከደረሱት ከጥቂቶቹ ውስጥ የአምላክ እስትንፋስ የሆኑ የብሉይና ሀዲስ መፅሀፍትን ብዛትና አይነት ያተተበት "Iambics for Seleucus" በተሰኘው ግጥማዊ ዘውግ ባለው ስራው ውስጥ ነው። በዚህም ውስጥ ከ7ቱ መፅሀፍት አንድም አላካተተም። [65]

9 EPIPHANIUS

ይህ የቤተክርስቲያን አባት ስለ ብሉይ መፅሀፍት በዝርዝር ያሰፈረባቸው ሶስት አንቀፆች አሉ። አንድ በአንድ እንመልከታቸው!

የመጀመሪያው በ " Panariyon 8 " ላይ የሰፈረ ነው!

" Genesis. Exodus. Leviticus Numbers. Deuteronomy. The Book of Joshua the son of Nun. The Book of the Judges. Ruth. Job. The Psalter. The Proverbs of Sol-omon. Ecclesiastes. The Song of Songs. The First Book of Kings. The Second Book of Kings. The Third Book of Kings. The Fourth Book of Kings. The First Book of Chronicles. The Second Book of Chronicles. The Book of the Twelve Prophets. The Prophet Isaiah. The Prophet Jeremiah, with the Lamentations and the Epistles of Jeremiah and Baruch. The Prophet Ezekiel. The Prophet Daniel. I Ezra. II Ezra. Esther. These are the twenty-seven books given the Jews by God. "[66]

2ተኛው " De Mensuris et Ponderibus 4 " ላይ የሰፈረ ነው። በዚህ ውስጥ ብቻ በሁለት ቦታ የሰፈረ ነው። አንድኛው በዚህ መልክ አስቀምጦታል።

" ...Genesis , Exodus, Leviticus, Numbers, Deuteronomy, Job, Psalms, Proverbs, Ecclesiastes, Song of Songs, Joshua, Judges & Ruth in one book, 1 & 2 Chronicles in one book, 1 & 2 Book of Kings in one book, 3 & 4 Book of Kings in one book, the Twelve, Isaiah, Jeremiah, Ezekiel, Daniel, 2 books of Esdras, Esther. " [67]

3ተኛው ደግሞ "De Mensuris et Ponderibus 23 " ላይ የተቀመጠ ነው።

" Genesis, Exodus, Leviticus, Numbers, Deuteronomy, Joshua, Job, Judges, Ruth, Psalms, 2 books of Chronicles, 4 books of Kings, Proverbs, Ecclesiastes, Song of Songs, the Twelve, Isaiah, Jeremiah, Ezekiel, Daniel, 2 books of Esdras, Esther."[68]

---

63 apud Eusebius, Eccles. Hist. 6.25 Or http://www.bible-researcher.com/origen.html

64 https://www.ccel.org/ccel/schaff/npnf204.xxv.iii.iii.xxv.html

66 Canon debate , p 199

67 Epiphanius Constantiensis, De Mensuris et Ponderibus, Wilhelm Dindorf / Denis Petau (eds.), [Epiphanii episcopi Constantiae opera 4,1], Lipsiae, 1862..

68 De Mensuris et Ponderibus 23

በአጭሩ ከዚህ አባት አቀማመጥ የምንረዳው በሶስቱ አቀማመጥ ጥቂት ወጥነት አለመኖር ቢታይም በዋነኝነት ከ7ቱ መፅሀፍት እዝራ ሱቱኤልና ተረፈ ኤርሚያስ አካቷል። [69] በመጀመሪያ በተጠቀሰው Panario 4 ላይ ዝቅ ብሎ በግልፅ የሲራቅና የጥበብ መፅሀፍት ቀኖናነት አጠራጣሪ እንደሆነ አስቀምጧል።

10 HILARY OF POITIERS

" The reason for reckoning twenty-two books of the Old Testament is that this cor-responds with the number of the [Hebrew] letters. They are counted thus according to old tradition: the books of Moses are five, Joshua son of Nun the sixth, Judges and Ruth the seventh, first and second Kings 1 the eighth, third and fourth [Kings] 2 the ninth, the two of Chronicles make ten, the words of the days of Ezra the elev-enth, 3 the book of Psalms twelfth, of Solomon the Proverbs, Ecclesiastes, and Song of Songs are thirteenth, fourteenth, and fifteenth, the Twelve Prophets six-teenth, then Isaiah and Jeremiah (with Lamentations and the Epistle) 4 and Dan-iel and Ezekiel and Job and Esther complete the number of the books at twenty-two. To this some add Tobit and Judith to make twenty-four books, according to he number of the Greek letters, which is the language used among Hebrews and Greeks gathered in Rome."[70]

ይህ አባት ፒይተርስ የተባለች ሀገር ጳጳስ የነበረ ሲኖን የአርዮስን አስተምህሮ በመቃወምና ትክክለኛውን የስላሴን አስተምህሮን በመጠበቅ ታዋቂ ነበር። ይህም አባት ባስቀመጠው የቅዱሳት መፅሀፍት ዝርዝር ውስጥ እዝራ ሱቱኤልን ፣ ጦቢትንና ዮዲትን አስገብቷል!

ምንምኳ እነዚህ ብቻ ባይሆኑም በብሉይ መፅሀፍት ብዛትና አይነት ዙሪያ በርከት ያሉ የቤተክርስቲያን አባቶች በቁጥርና በዝርዝር ያስቀመጡትን ተመልክተናል። በተጠቀሱት በሁሉም የቤተክርስቲያን አባቶች ዘንድ 22ት የሚል ቁጥር የተጠቀሰ ሲሆን በቁጥሩም ይሁን በመፅሃፍቱ ዝርዝር አብዛኞቹ ከአይሁዳውያን ዝርዝር ጋር ተዛማጅና ተነፃፃሪነት ያላቸው ናቸው። በግምት ብናስቀምጥ 95% አንድን አይነት ናቸው! የተጠቀሱትን የአጠቃላዩን አበው ዝርዝር ስንመለከት ከሁለት ወይም ከሶስት ባልዘለለ መልኩ ከ7ቱ መፅሀፍት አካተው እናገኛን። ነገር ግን እነኚህም መፅሀፍት በአብዛኛው አንዱ የጣለውን አንዱ አንስቶት ፤ አንዱ ያካተተውን አንዱ ጥሎት የሚገኝ ነው። ለዚህም በጥቂቱ የተጠቀሱትን የአበው ዝርዝሮች እናጢን።

ይህ አባት ፒይተርስ የተባለች ሀገር ጳጳስ የነበረ ሲኖን የአርዮስን አስተምህሮ በመቃወምና ትክክለኛውን የስላሴን አስተምህሮን በመጠበቅ ታዋቂ ነበር። ይህም አባት ባስቀመጠው የቅዱሳት መፅሀፍት ዝርዝር ውስጥ እዝራ ሱቱኤልን ፣ ጦቢትንና ዮዲትን አስገብቷል!

ምንምኳ እነዚህ ብቻ ባይሆኑም በብሉይ መፅሀፍት ብዛትና አይነት ዙሪያ በርከት ያሉ የቤተክርስቲያን አባቶች በቁጥርና በዝርዝር ያስቀመጡትን ተመልክተናል። በተጠቀሱት በሁሉም የቤተክርስቲያን አባቶች ዘንድ 22ት የሚል ቁጥር የተጠቀሰ ሲሆን በቁጥሩም ይሁን በመፅሃፍቱ ዝርዝር አብዛኞቹ ከአይሁዳውያን ዝርዝር ጋር ተዛማጅና ተነፃፃሪነት ያላቸው ናቸው። በግምት ብናስቀምጥ 95% አንድን አይነት ናቸው!

[69] እዝራ ሱቱኤል - ለዚህም Foot Note 65ን ይመልከቱ

[70] Epiphanius Constantiensis, De Mensuris et Ponderibus, Wilhelm Dindorf / Denis Petau (eds.), [Epiphanii episcopi Constantiae opera 4,1], Lipsiae, 1862.

የተጠቀሱትን የአጠቃላዩን አበው ዝርዝር ስንመለከት ከሁለት ወይም ከሶስት ባልዘለለ መልኩ ከ7ቱ መፅሀፍት አካተው እናገኛን። ነገር ግን እነኚህም መፅሀፍት በአብዛኛው አንዱ የጣለውን አንዱ አንስቶት ፤ አንዱ ያካተተውን አንዱ ጥሎት የሚገኝ ነው። ለዚህም በጥቂቱ የተጠቀሱትን የአበው ዝርዝሮች እናጢን።

ሜሊቶ ከ7ቱ መፅሀፍት አንድም እንዳልጠቀሰ ተመልከተናል። የአንዳንዶችን እሳቤ ከግምት ውስጥ አስገብተን የጥበብንና የእዝራ ሱቱኤልን መፅሀፍ አካቷል ብለንም መመልከት እንችላለን። በዚሁ ክፍለዘመን እንደነበር የሚገመተው ጥንታዊው የብሪንዮስ ዝርዝር ከ7ቱ መፅሀፍት አንድም አልተካተተም![71] ከሜሊቶ ጋር የተመሳሳይ ዘመን ምንጮች እንደመሆናቸው ይህ የሜሊቶ ዝርዝር ምንም አለማካተቱን ሊያመለክተን የሚችል ቢሆንም የሜሊቶ ዝርዝር እዝራ ሱቱኤልና የጥበብን መፅሀፍት አካቷል ብለን ብንወስድ ግን ይህ የብሪንዮስ ዝርዝር በዛው ዘመን ካለው ሌላኛው ምንጭ ዝርዝር ጋር እርስ በእርሱ የሚፃረር ሆኖ እናገኘዋለን።

አርጌን በዝርዝሩ መቃብያንን ፣ ተረፈ ኤርሚያስንና እዝራ ሱቱኤልን አካቷል። ይህን በሜሊቶ ዝርዝር ውስጥ የምንመለከተው አይደለም! ምናልባት ሜሊቶ እዝራ ሱቱኤልን እንዳካተተ ብናስብኳ አርጌን መቃብያንንና ተረፈ ኤርሚያስ በማካተቱ ከሜሊቶ ዝርዝር ጋር ሳይጣጣም ሲቀር እንመለከታለን።

የአትናቲዎስን ዝርዝር ስንመለከት ባሮክና ተረፈ ኤርምያስን አካቷል። የባሮክ መፅሀፍ በሜሊቶም ፤ በአርጌንም ዝርዝር ውስጥ የሌለ ነው። ተረፈ ኤርምያስን አርጌን ቢያካትተውም በሜሊቶ ዝርዝር ውስጥ ተካቶ አይገኝም።

የእየሩሳሌሙ ቄርሎስ በዝርዝሩ ውስጥ እዝራ ሱቱኤልን ፣ ባሮክንና ተረፈ ኤርምያስን አካቷል። እዝራ ሱቱኤልን በማካተቱ ከሜሊቶ ዝርዝር ጋር ይስማማል ፤ ነገር ግን ባሮክንና ተረፈ ኤርምያስን ባለማካተቱ ከሜሊቶ ዝርዝር አይጣጣምም። ከአርጌን ዝርዝር ጋር በሁለት መፅሀፍት ቢስማማም መቃብያንን ባለማካተቱ የለያያል። የባሮክ መፅሀፍ ደግሞ በአርጌን ዝርዝር ውስጥ አልተካተተም። ባሮክንና ተረፈ ኤርምያስን በማካተቱ ከአትናቴዎስ ጋር ቢዛመድም እዝራ ሱቱኤልን በማካተቱ የአትናቲዎስን ዝርዝር ይፃረራል።

ግሪጎሪዮስ ዘእንዚናዙ ከ7ቱ መፅሀፍት የጥበብን መፅሀፍ ብቻ ነው ያካተተው። የጥበብ መፅሀፍ በሜሊቶ ፣ በአርጌን ፣ በአትናቲዎስና በቄርሎስ ዝርዝር ውስጥ ጭራሽ አልተካተተም። ምናልባት የአንዳንዶችን እሳቤ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሜሊቶ የጥበብን መፅሀፍ አካቷል ብንልኳ በቀደሙት አራት ዝርዝሮች ውስጥ አልተካተተም።

የጀሮምን ዝርዝር ስንመለከት ጀሮም ቀጥታ የጥበብን ፣ የመቃብያንን ፣ የሲራቅን ፣ የዮዲትንና የጦቢትን መፅሀፍት ቀኖናዊ እንዳልሆኑ በመናገር ከዝርዝሩ ውስጥ አላካተታቸውም። ይህ ደግሞ ከላይ ካካተቷቸው አበው ጋር ሙሉ ሙሉ የማይጣጣም ነው።

ሩፊነስንና አምፊሎከስን ብንመለከት ከጀሮም ጋር ተመሳሳይ አቋም እናገኛለን። ከ7ቱ መፅሀፍት ምንም አላካተቱም ፤ ይልቁኑም ሩፊነስ ልክ እንደ ጀሮም ጥበብ ፣ ሲራቅ ፣ ጦቢትና መቃብያን ቀኖናዊ እንዳልሆኑ በማስቀመጥ ከዝርዝሩ አስወጥቷቸዋል። ይህም ደግሞ ከቀደሙት እዚህ መፅሀፍት ካካተቱት አበው ጋር የማይሄድ አቋም ነው። ምናልባት ሁለቱም እዝራ ሱቱኤልን አካተዋል ብንል በዚህ ከአርጌን ፣ ከእየሩሳሌሙ ቄርሎስና ከአምፊሎከስ ዝርዝር ጋር ቢስማማም ከሜሊቶ ፣ ከአትናቴዎስ ፣ ከግሪጎሪ ዘእንዚናዙና ከጀሮም ዝርዝር ጋር የሚፃረር ነው።

71 Edward Earle Ellis (1991), The Old Testament in Early Christianity, Mohr Siebeck, p. 22, N.70

ከኤፒፋንየስ (Epiphanieus) የተለያዩ ምንጮች በተወሰነ መልኩ የሚለያዩ ዝርዝሮችን እናገኛለን። በሁለቱ ምንጮች ዝርዝር ውስጥ እዝራ ሱቱኤልን ብቻ ሲያካትት በሌላኛው አንድ ምንጭ ውስጥ ደግሞ ተረፈ ኤርምያስን ጨምሮ እናገኛለን። በአንድ ግለሰብ ስራዎች ውስጥ የተለያየ አቋምን መመልከታችን የሚነግረን ትልቅ አለ። እዝራ ሱቱኤልን በማካተቱ ከአርጌንና ከእየሩሳሌሙ ቄርሎስ ጋር ቢያዛምደውም ከሜሊቶ ፣ ከአትናቴዎስ ፣ ከግሪጎሪ ዘእንዚናዙ ፣ ከጀሮም ፣ ከአምፊሎኪስና ከሩፊነስ ዝርዝሮች ጋር አይስማማም። ተረፈ ኤርምያስን በማካተቱ ደግሞ ከአርጌን ፣ ከአትናቴዎስና ከእየሩሳሌሙ ቄርሎስ ዝርዝር ጋር ሲያስማማው ከሜሊቶ ፣ ከግሪጎሪ ዘእንዚናዙ ፣ ከጀሮም ፣ ከአምፊሎኪስና ከሩፊነስ ዝርዝር ጋር ያፃርረዋል።

ሂላሪ በዝርዝሩ ውስጥ እዝራ ሱቱኤልን ፣ ጦቢትንና ዮዲትን አጠቃሏል። እዝራ ሱቱኤልን በማካተቱ ከአርጌንና ከእየሩሳሌሙ ቄርሎስ ጋር ቢያዛምደውም ከሜሊቶ ፣ ከአትናቴዎስ ፣ ከግሪጎሪ ዘእንዚናዙ ፣ ከጀሮም ፣ ከአምፊሎኪስና ከሩፊነስ ዝርዝሮች ጋር አይስማማም። ጦቢትና ዮዲትን በማካተቱ ደግሞ ከላይ የተጠቀሱትን አጠቃላይ የአበው ዝርዝር ይቃረናል።

እንግዲህ የመፅሀፍትን ብዛትና አይነት በዝርዝር ያስቀመጡ ብዙ አበውን በሰፊው እንደተመለከትነው ሁሉም አበው ከ7ቱ መፅሀፍት አንድ ወይም ሁለት ፤ በዛ ከተባለም ሶስት መፅሀፍትን ብቻ አካተው የሚገኝ ነው። ከላይ ዝርዝራቸውን በሰፊው እንዳጤንነው ብዙሀኑን መፅሀፍት በግልፅ ቢጥሉም ባካተቷቸው መፅሀፍት ላይ ደግሞ የፀናና ወጥ የሆነ አቀማመጥ በነሱ ዘንድ አልነበረም። ይልቁኑ ሁሉም በ22ቱ (39ኙ) መፅሀፍት ላይ የተሰካካና ተመሳሳይ አቀማመጥ አስቀምጠው እንመለከታለን። ስለዚህም በዚህ በ7ቱ መፅሀፍት ላይ ባላቸው የተለያየና ወጥነት በሌለው አቀማመጣቸው ወደ አንድ ድምዳሜ መድረስ እጅግ የማይቻል ይሆናል።

የቤተክርስቲያን አባቶች አጠቃቀም - Quotations

እንደ አምላክ እስትንፋስ | As Insipid Scripture

በዚህ ክፍል ምንመለከተው በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ 7ቱ መፅሀፍት ያላቸውን ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ የመጣ አጠቃቀምና በዘመናት ውስጥ ያነበራቸውን ወጥነት ማጣት ነው። ቀደም ተብሎ በመግቢያ ላይ እንደተገለፀው ይህ የቀኖና ርዕሰ ጉዳይ እጅግ ሰፊ ከመሆኑ አንፃር በዚህ ርዕስ ስር ትክክለኛውን ወይም ሐዋርያዊ እይታን ለማግኘት ልኬታችንን እጅግ ጥንታዊ ወደሆኑት የመጀመሪያዎቹ ክፍለዘመናት ላይ በመወሰንና በማተኮር የምንመለከት ይሆናል።

ሀዲስ ኪዳን የቀደመውን የክርስቶስንና የሐዋርያቱን የብሉይ መፅሀፍት አጠቃቀም የሚያሳየን ቀዳሚውና ወሳኙ ምንጫችን ነው። ብሉይ ኪዳን በሀዲስ ኪዳን ውስጥ 283 ክፍል ቃል ለቃል ተጠቅሷል (Direct Quota-tions)። በሚገርም ሁኔታ በሀዲስ ኪዳን የአምላክ እስትንፋስነታቸውን በሚያስረግጥ መልኩ ከ7ቱ መፅሀፍት አንዴም አልተጠቀሰም። ይህ ማለት ኢየሱስም ይሁን ሐዋርያቱ እነዚህን መፅሀፍት እንደአምላክ እስትንፋስ ተቀብለዋቸው የእምነት አቋምና አስተምህሮችን ሲመሰርቱባቸው አንመለከትም። ይህን ስንል ግን 7ቱ መፅሀፍት በክርስቶስና በሐዋርያቱ ጭራሽ አይታወቁም እያልን አይደለም። ቀደም ብለን እንዳየነው እነዚህ መፅሀፍት በአይሁድ የተከተቡ ስለዚህም የአይሁድ ባለቤትነት ያላቸው ፤ በተለያዩ ማህበረሰባቸው ውስጥም

ተጠቃሚነት ያላቸው መሆኑ እርግጥ ነው። ስለዚህ ሐዋርያቱ በአይሁድ ማህበረሰብ ውስጥ እንደተወለደና እንዳደገ አይሁዳዊ በእነዚህ መፅሐፍ ላይ እውቀት (Background knowledge) ይኖራቸዋል። ከዚህ አንፃር እንደውም በፅሁፎቻቸው ውስጥ በጥቂት ቦታዎች ላይ ከነዚህ መፅሀፍት ጋር የሀሳብ መመሳሰል ይስተዋላል። ዋናው ቁምነገር ግን እነዚህን መፅሀፍት እንደ አምላክ ቃል ይመለከቷቸውና ይቀበሏቸው ነበር ወይ የሚለው ነውና ይህን ሊያስረግጥ በሚችል መልኩ ደግሞ የጠቀሱበት አንዳች ክፍል የለም። የአምላክ ቃል አድርገን የምንቀበለው ሀዲኪዳን በነዚህ መፅሀፍት ላይ ያለው ዝምታ ከምንም በላይ ትልቅ አፅንኦት ያለው ነው።

በጥንቷ ቤ/ክ ክርስቲያኖች ይጠቀሙ በነበረው ሰባሊቃናት ውስጥ ባሮክና ተረፈ ኤርሚያስ በኤርምያስ መፅሀፍ ላይ በአንድነት የሚቀመጡ ነበሩ ፤ ሶስናም በዳንኤል መፅሀፍ ውስጥ ፤ እዝራ ሱቱኤልም የእዝራ ቀጣይ ወይም ሙሉ ክፍል ተደርጎ የሚጠቃለል ነበር። ከነዚህ ተጨማሪ መፅሀፍ የጠቀሱ ብዙ አባቶችም መፅሀፍቶቹ ከጥንትም ጀምሮ አንድ እንደሆኑና የዋነኞቹ መፅሀፍት ክፍል እንደሆኑ በማሰብ ቀጥታ በኤርምያስ ወይም በዳንኤል ስም ነው ጠቅው ያስቀመጧቸው። ነገር ግን ተረፈ ኤርምያስም ይሁን የባሮክ መፅሀፍ የኤርምያስ ክፍል አይደሉም። የሶስና መፅሀፍም የዳንኤል መፅሀፍ አይደለም። የአባቶች እነዚህን መፅሀፍት የአምላክ እስትንፋስ አድርገው ያለምንም የቀኖና ጥያቄ እንዲጠቀሟቸው ያደረጋቸው ዋነኛ ምክንያት መፅሀፍቱን ቀጥታ የጥንታውያኑ ቀኖናዊ መፅሀፍት እነዚህም የኤርምያስና የዳንኤል መፅሀፍት ክፍል አድርገው መውረሳቸው ነው። እነዚህ መፅሀፍት ቀድመው በነበሩት መፅሀፍት ላይ ተደምረውተ የተቀመጡበት ምክንያት አለ። በመጀመሪያው ክፍለዘመን በአይሁድ መሀከል መፅሀፍትን የማብራራት ፣ የመተርጎምና ፍታቴ የመስጠት እንቅስቃሴ (Midrashic Expansion) ተነስቶ ነበር። በዚህም ደግሞ አይሁዶች መፅሀፍትን ለማነጽ አላማ (edification) በተለየ መንገድ ያስቀምጡና ይጠቀሙ ነበር። ለዚህም ቲዎዲሽንን መጥቀስ ይቻላል። ቲዎዲሽን 7ቱን መፅሀፍት በነጠላ መፅሀፍትነት በትርጓሜው ውስጥ ባያካትታቸውም በዳንኤል መፅሀፍ ውስጥ የሶስናና 'Bel and Dragon' የተሰኘ መፅሀፍ እንዳካተተ ይታመናል ፤ በኤርምያስ ውስጥ ደግሞ ተረፈ ኤርምያስና የባሮክን መፅሀፍ በአንድነት ተቀላቅለው (append ተደርገው) ተቀምጠዋል። በዚህም የአይሁድ ተፅእኖ ምክንያት ክርስቲያኖች በዳንኤልና በኤርምያስ ላይ ይህንኑ አቀማመጥ ነበር የያዙት። ጀሮም ክርስቲያኖች የሚጠቀሙት የዳንኤል መፅሀፍ የቲዎዲሽኑ ዳንኤል እንደሆነ ተናግሯል። ከዚህ ምንረዳው ቁም ነገር በቤተክርስቲያን ውስጥ አባቶች ከነዚህ መፅፍት እንደ አምላክ እስትንፋስ የመጠቀማቸው ቀንደኛው ምክንያት በrabbinical Judaism ተፅእኖ አማካኝነት በስህተት የወረሱት የመፅሀፉቱ አቀማመጥና አጠቃቀም ነው።

ከላይ እንደተመለከትነው የመፅሀፍቅዱስን ዝርዝር ያስቀመጠልን ጥንታዊው አባት ሜሊቶ ነው። ይህ አባት ያስቀመጠው ዝርዝር በአናሲሞስ በኩል ቢደርሰንም ሌሎች ስራዎቹ በእጃችን ላይ የሉምና ጠቅሶ ይጠቀም አይጠቀም አናውቅም። ነገር ግን ከዝርዝሩ አንፃር መገመት እንችላለን። እርሱም ደግሞ ከነዚህ መፅሀፍት ጠቅሶ ይጠቀም እንደነበር ሊያስረግጥ የሚችል አይደለም። ሜሊቶ የቅዱሳት መፅሀፍትን ብዛትና አይነት ለማወቅ እጅጉን ፈልጎ ስለነበር ለዚህ ፍላጎቱና ጥያቄው መልስ ለማግኘት ወደ ፍልስጤም (Palestine) ነበር ያቀናው። ነገር ግን ሜሊቶ የሰርዴስ ጳጳስ ሆኖ ሳለ ለምን ወደ ፍልስጤም አመራ ? በዛ ጊዜ በሰርዴስ ከተማ እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸው የመፅሀፍቶቹን አይነትና ብዛት ሊነግሩት የሚችሉ አይሁዳውያን ነበሩ። በዛ ላይ ሰርዴስ በኤሽያ ሰባት ሀገራት ውስጥ ካሉት ሰባት አብያተክርስቲያናት መሀከል አንዷ ነች። ምናልባትም በሰርዴስ ከተማ ለጥያቄው መልስ ሊሰጡ የሚችሉ ክርስቲያኖች ባይኖሩኳ በዛው በኤሽያ ስር ወዳሉት አብያተክርስቲያናት በመሄድ መጠየቅና ማወቅ እየቻለ ስለምን ወደ ፍልስጤም ሄደ ? የሜሊቶ ጉዞ የሚያስረግጥልን እውነት በሰርዴስና በአጠቃላይ ኤሽያ አብያተክርስቲያናት መሀከል በዚህ ጉዳይ ላይ ውዝግብ እንደንበርና የጠራና ወጥ የሆነ አቋም አለመኖሩን ነው። በዚህም ምክንያት ፍልስጤም የክርስትና እምነት የወጣባት ከተማ ስለሆነች ትክክለኛው አቋም በዚያ እንደሚያገኝ በማሰብ ወደዚያ አመራ።

ከአጅግ ጥንታዊ አበው መሀከል እነዚህን 7ቱን መፅሀፍት ሙሉ ለሙሉ ያልተጠቀሙ አበው አሉ። ከእነዚህም ሰማእቱ ዮስቲንንና (Justin Martyr 100-163 ዓ/ም) ቲዎፊለስን (169-182 ዓ/ም) መጥቀስ እንችላለን። ዮስቲን በስራው ውስጥ ከብሉያት መፅሀፍት እጅግ ብዙ ጊዜ የጠቀሰ ሲሆን ከ7ቱ መፅሀፍት ግን የአምላክ እስትንፋስነታቸውን በሚያስረግጥ መልኩ አንድም ቦታ አልጠቀሰም። ሚገርመው ነገር እንደ አምላክ እስትንፋስ ብቻ ሳይሆን እንደው እንደማንኛውም የመፅሀፍ አጠቃቀስ ራሱ ከነዚህ መፅሀፍ አልተጠቀመም። (ምንምኳ የአምላክ ቃል መሆኑን በሚያስረግጥ መንገድ ባይሆንም አንዳንዶች ከጥበብ መፅሀፍ እንደጠቀሰ ለማሳየት ይሞክራሉ ነገር ግን በዛ ክፍል ሙሉ ሀሳቡን ከምሳ 8 : 21-25 የወሰደው ነው) የአንፆኪያው ቲዮፊለስንም ብንመለከት የአምላክ እስትንፋስነታቸውን ሊያስረግጥ በሚችል መልኩ አንድም ቦታ ከነዚህ መፅሀፍት አልጠቀሰም። ይህ እንዳለ ሆኖ ከ7ቱ መፅሀፍ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ በየትኛውም አባት ጥቅም ላይ ያልዋሉ መፅሀፍትም አሉ :- ሶስተኛና አራተኛ መቃብያን!

የዮዲትና ሁለቱ የመቃብያን መፅሀፈት ስንመለከት ከመጀመሪያው ክፍለዘመን መጨረሻ አካባቢ አንስቶ እስከ ሁለተኛው ክፍለዘመን መጨረሻ ድረስ እንደ ታሪክ ምንጭነት በጥቂቱ ጥቅም ላይ ውለዋል ፤ ይህም ደግሞ የአምላክ ቃል መሆናቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ አይደለም። የእስክንድርያው ቀለሜንጦስ በ95 ዓ/ም አካባቢ ከዮዲት እንደ ታሪክ ምንጭነት ሲጠቀም ፤ ጠርጡለስም ከዚሁ ከዮዲት መፅሀፍ በተመሳሳይ መንገድ ተጠቅሟል። በ2ተኛ ክፍለዘመን መጨረሻ አካባቢ ጠርጡሊያን አንድ ጊዜ ከነኛ መቃብያን ሲጠቀም ቀለሜንጦስ ሁለት ጊዜ ከ2ተኛ መቃብያን ተጠቅሟል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሶስተኛ ክፍለዘመን መጀመሪያ አካባቢ የነበረው ሂፖሊተስም 1ኛና 2ኛ መቃብያንን እንደ ታሪክ ምንጭ ሲጠቀም ዮዲትን ግን በምንም መንገድ አልተጠቀመም። በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት አበው መፅሀፍቱን የተጠቀሙት እንደ ታሪክ ምንጭነት ብቻ መሆኑን መዘንጋት የለበትም! የጦቢትንና የሲራቅን መፅሀፍ ስንመለከት እነዚህ መፅሀፍት በዋነኝነት ጥቅም ላይ የዋሉት በምስራቅ አበው ነው። በ100 ዓ/ም አካባቢ ዲዳቼ እንዲሁም ቀለሜንጦስ ጦቢትን በታሪክ ምንጭነት ተጠቅመውታል። በርግጥ ቀለሜንጦስ እንደአምላክ እስትንፋስም ተጠቅሞታል። ከዚህ በፊት በዚሁ መንገድ ጦቢትን የጠቀሰው ፖሊካርፕ ነበር። ፖሊካርፕ በኤሽያ ስር ካሉት ከሰባቱ አብያተክርስቲያናት መሀከል አንዱ የሆነው የሰምርኔስ ከተማ ጳጳስ ነበር። ከላይ እንደተመለከትነው ከሜሊቶ ምንጭ አንፃር በኤሽያ ውስጥ በቅዱሳት መፅሐፍት ዙሪያ እርግጥ የሆነ ነገር አልነበረም ፤ ውዝግብና አለመግባባት ነበር። ከዚህ አንፃር ፖሊካርፕ ይህን መፅሀፍ በዚህ መልክ መጠቀሙ የዚህ ውጤት ሊሆን ይችላል። ይህ ማለት በአጠቃላይ የክርስቲያኑ ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት እንደነበረው እርግጠኛ የሚያደርገን ነገር የለም። ከምዕራብ አበው የጦቢትን መፅሀፍ የተጠቀመው የመጀመሪያው ሰው የ3ተኛው ክ /ዘ ሂፖሊተስ ነው ፤ ይህ ሰው ከሲራቅ መፅሀፍ ሙሉ ለሙሉ አልጠቀሰም። የሲራቅን መፅሀፍ ዲዳቼና የበርናባስ መልእክት ተጠቅመውታል ግን እስከ ቀለሜንጦስ ድረስ የአምላክ እስትንፋስነቱን በሚያረጋግጥ መንገድ ጥቅም ላይ አልዋለም። ከምዕራብ አበው የተጠቀመው የመጀመሪያው አበው ደግሞ በ3ኛ ክፍለዘመን አጋማሽ አካባቢ የነበረው ካፕሪያን ነው።

ከሀዲስ ኪዳን የኢየሱስና የሐዋርያቱ አጠቃቀም አንስተን እስከ አራተኛ ክፍለዘመን እያደገ የመጣውን የመፅሀፍቱን አጠቃቀም እንዲሁም ውዝግብ ፤ የራሳቸው ወሳኝ ምክንያት ያላቸው የአንዳንድ መፅሀፍት ጥቅም ላይ መዋልንም ጨምሮ ከላይ ተመልክተናል። ይህ ከመጀመሪያው ክ/ዘ እስከ አራተኛ ክፍለዘመን ያየነው የመፅሀፍቱ የአጠቃቀም እድገት በአምስተኛውና ከዛም ወዲያ ባሉት ክፍለዘመናት ከቀደመው ጋር ባልተገናዘበ መልኩ ይበልጥ እያደገ የቀጠለ ነው። በመጀመሪያዎቹ አመታትና ዘመናት ጭራሽ ጥቅም ላይ ያልዋሉ መፅሀፍት በነዚህ ጊዜያት ጥቅም ላይ እየዋሉ ሲመጡ እንመለከታለን። በተቃራኒም ደግሞ በአንዳንዶች ዘንዳ ጥቅም ላይ ይውል የነበረም መፅሀፍ ጥቅሙ እየቀነሰና ሙሉ ለሙሉ እየጠፋ ሲመጣ እንመለከታለን። ይህም ደግሞ በቀዳማዊነት የሄኖክ መፅሀፍ ነው። ጀሮም ስለሄኖክ ሲናገር ቀድሞ በአብዛኛው ዘንድ ተጠቃሚነት እንዳልነበረውና አፖክሪፋ ከሚላቸው ውስጥ ይካተት እንደነበር ነገር ግን ከዘመናት በኋላ በሱ ጊዜ የአምላክ እስትንፋስ ሆኖ እንደተቀላቀለ ተናገሯል። (On Illustrious Men 4) ይህ ምስክርነት ቀጥታ የሚያሳየን መፅሀፉ ከአምስተኛው ክፍለ ዘመን በፊት ስለነበረው ተቀባይነት ነው ነገር ግን ከዚህ በተቃራኒ በዚሁ ተመሳሳይ ዘመን እንደአምላክ እስትንፋስ ጥቅም ላይ ይውል ነበር። በሚገርም ሁኔታ ደግሞ ጀሮም በጊዜ ሂደት ተቀባይነት እንዳገኘ በተናገረበት በሱና ከሱ በኋላ ባሉት ዘመናት በተቃራኒው ጥቅም ላይ መዋሉ እየቀነሰና እየደበዘዘ የመጣበት ጊዜ ነበር። ይህም ያለውን ውዝግብ የሚያመላክተን ነው! የቀደመ እሳቤ ለማፅደቅ ብለን ይህን የቤተክርስቲያን ታሪክ እስካልተመለከትን ድረስና ታሪክ ራሱ እንዲወስን እስከፈቀድን ድረስ በ7ቱ መፅሀፍት ላይ እርግጥ የሆነ አንድን አቋም የሚያሲዝ አንዳች ምክንያት የለም።

7ቱ መፅሀፍት ላይ የቤተክርስቲያንን አቋም በሶስት መሠረታዊ መንገዶች ተመልክተናል። እነዚህም ጉባኤያት ፤ ዝርዝሮችና አጠቃቀሞች ናቸው። በእያንዳንዱ ርዕስ በተናጥል እንደተመለከትነው በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በ7ቱ መፅሀፍት ላይ ወጥ የሆነ አቋም አልነበረም። አንዳንዶች የአበውን ዝርዝርና የመፅሀፍት አጠቃቀማቸው በማጤን በዝርዝሮቹ የአምላክ እስትንፋስ የሆኑት መፅሀፍት እነዚህ ናቸው እያሉን አይደለም በማለት ይሞግታሉ። ይልቁኑ ቀኖና የሚለው ቃል ካለው የተለያየ ፍቺ አንፃር ቀኖናዊ በማለት ዘርዝረው ያስቀመጧቸው መፅሀፍት በቤተክርስቲያን ውስጥ በገሀድ የሚነበቡትንና በቅዳሴ ሰአት ጥቅም ላይ የሚውሉትን ለመግለፅ እንደሆነ ያስቀምጣሉ።

ነገር ግን ይህ የሙግት ሀሳብ የቤተክርስቲያንን ሙሉ ታሪክና ሙሉ እይታ የሚወክል አይደለም። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው የሮምና የካርቴጁ ጉባኤ ላይ በተቀመጡት መፅሀፍት ውስጥ ከ7ቱ መፅሀፍት አምስቱ ተካተዋል። ከተካተቱት መፅሀፍትም የሚያጋራቸውና የሚያለያያቸውን መፅሀፍት ተመልክተናል። ከዚሁ ጋር በተያያዘም እነዚህ ጉባኤያት በሚደረጉበት ዘመን ውስጥ የሚገመት እድሜ ያለውና የሐዋርያት ቀኖና በተሰኘው ምንጭም ከ7ቱ መፅሀፍት ሶስቱ ብቻ እንደተካተቱ አይተናል። በዚህና በጉባኤያቱ ዝርዝር መሀከልም ያለውን ልዩነት አጢነናል። የቱሩሎ ጉባኤም ከሌሎቹ ጋረ ያለውን ንፅፅር ተመልክተናል።

እነዚህ የጉባኤያትና የሐዋርያት ቀኖና ምንጮች በእርግጥም የአምላክ ቃል የሆኑትን ቀኖናዊ ቅዱሳት መፅሀፍት ዘርዝረው ያስቀመጡ መሆናቸው ምንም ጥርጥር የሌለው ነው። የሮሙ ጉባኤ ባስቀመጠው ድንጋጌ ውስጥ መፅሀፍቱን ከመዘርዘሩ በፊት ቀደም ብሎ ስለመፅሀፍቱ በቤተክርስቲያን ተቀባይነት ያላቸው መሆናቸውንና የአምላክ መፅሀፍት መሆናቸውን ገልፆ የሚጀመር ነው። የካርቴጁም ጉባኤ በግልጥ ቀኖናዊ ከሆኑት ቅዱሳት መፅሀፍት ውጪ በቤተክርስቲያን ውስጥ በአምላክ እስትንፋስነት ስም ምንም እንዳይነበብ እንደተወሰነ አስቀምጦ ቀኖናዊ የሆኑትም መፅሀፍት እነዚህ ናቸው በማለት ዝርዝሩን የሚጀምር ነው።

"It was also determined that beside the canonical scriptures noting be read in the church under the title of divine scripture. The canonical scriptures are these ..."[72]

ይህን በሚያጠናክር መልኩ ደግሞ የሎዶቅያው ጉባኤ በ59ነኛው ድንጋጌ ቀኖናዊ ያልሆኑ መፅሀፍት በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዳይነበቡ ይልቁኑም ቀኖናዊ መፅሀፍት የሆኑት ብቻ እንዲነበቡ ይደነግጋል። ከዚህ ምንረዳው በጉባኤያቱ የተዘረዘሩልን መፅሀፍት በርግጥም የአምላክ እስትንፋስ ተደርገው የተወሰዱ ቀኖናዊ መፅሀፍትን እንደሆነ ነው።

በሚገርም ሁኔታ ከቤተክርስቲያን አበው ያስቀመጡትን ዝርዝር ከሌሎች ንፅፅሮች ውጪ ሆነን ያለምንም ማብራሪያ መነፅር ያስቀመጡትን ብቻ ስንመለከት በርግጥም በመንፈስቅዱስ መሪነት የተከተቡትን የአምላክ እስትንፋስ የሆኑትን መፅሀፍት እየተናገሩ እንደሆነ ከራሳቸው ማብራሪያ ማረጋገጥ እንችላለን። ለምሳሌ የአትናቴዎስን አቀማመጥ ስንመለከት ዘርዝሮ ያስቀመጠው የአምላክ ቃል የሆኑትን መፅሀፍት እንደሆነ ከምንባቡ እንረዳለን። እራሳቸውን በውሸትና ዋጋ ሊሰጠው በማይገባ ሳይንስ ያበለፀጉ በክፉ ሀሳብም ጠፍተው መፅሀፍትን በቅዱሳን ስም እንደፈበረኩ ይናገራል ፤ መጨረሻ ላይም እነዚህ መፅሀፍት (አፖክራፋል) የኑፋቄ ውጤት ሲሆኑ እነዚህ ደግሞ በመረጡት ጊዜ ፅፈዋቸው ፤ የጥንት መፅሀፍት እንዲመስሉም የጥንት ዘመን ጊዜ እየሰጧቸው ፤ በመስማማት ለማሳት ምቹ ጊዜን ይጠብቃሉ በማለት ይናገራል።

የእነዚህ መፅሀፍት ስምም ከእውነተኞቹ መፅሀፍት ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ አንዳንዶች ቀላልና ንፁ አድርገው በማሰብ እንዳይታለሉ እንደሚፈራ ይናገራል። ቀጥሎ ስለመፅሃፍቱ ሲናገር ለመዳን የሚሆኑ ፤ ከአይን ምስክሮችና ከቃሉ አገልጋዮች ለአባቶች የወረዱ በእውነተኛ ወንድሞችም እነዚህ ቀኖናዊ የሆኑት የመለኮት እስትንፋስ ያላቸው መፅሀፍት (.. accredited as Divine) ወደነሱ የወረዱላቸው እንደሆኑ ይናገራል። እነዚህንም የመለኮት እስትንፋስ የሆኑ መፅሀፍትን ከአፕክሪፋል ጋር በመቀላቀል በሚያስቱት ሰዎች ስቶ የወደቀ ሰው እነርሱን እንዲያወግዝ ፤ በንፅህና ከነዚህ ተቆጥበው የቆዩት ደግሞ ይህን በመያዛቸው እንዲደሰቱ ያዛል። በድጋም ስለነዚህ ቀኖናዊ መፅሀፍት ሲናገር የመዳን መሰረት እንደሆኑ ፤ በያዙትም የህይወት ቃል ጥምን ሁሉ የሚያረኩ እንደሆኑ ፤ እግዚአብሔርን ለመምሰል ዶግማዊ መሰረት እንደሆኑ (for the Doctrine of Godliness) ፤ በነዚህም ላይ ማንም እንዳይጨምርና እንዳይቀንስም ያዛል።

---

72 http://www.bible-researcher.com/carthage.html

ይህም ብቻ ሳይሆን በዚሁ ንግግሩ መሀል በሚገርም ሁኔታ ማቲ 22፤29ና ዮሐ 5:39 በመጥቀስ ኢየሱስ "መፅሀፍት" (scripture) በማለት ሰዱቃውያንን ሲወቅስ የገለፀው ከላይ እሱ እያወራላቸው ያሉትን መፅሀፍት መሆኑን በሚናገር አውድ ይገልፃል።

የእነዚህ መፅሀፍት ስምም ከእውነተኞቹ መፅሀፍት ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ አንዳንዶች ቀላልና ንፁ አድርገው በማሰብ እንዳይታለሉ እንደሚፈራ ይናገራል። ቀጥሎ ሰለመፅሃፍቱ ሲናገር ለመዳን የሚሆኑ ፤ ከአይን ምስክሮችና ከቃሉ አገልጋዮች ለአባቶች የወረዱ በእውነተኛ ወንድሞችም እነዚህ ቀኖናዊ የሆኑት የመለኮት እስትንፋስ ያላቸው መፅሀፍት (.. accredited as Divine) ወደነሱ የወረዱላቸው እንደሆኑ ይናገራል። እነዚህንም የመለኮት እስትንፋስ የሆኑ መፅሀፍትን ከአፕክሪፋል ጋር በመቀላቀል በሚያስቱት ሰዎች ስቶ የወደቀ ሰው እነርሱን እንዲያወግዝ ፤ በንፅህና ከነዚህ ተቆጥበው የቆዩት ደግሞ ይህን በመያዛቸው እንዲደሰቱ ያዛል። በድጋም ስለነዚህ ቀኖናዊ መፅሀፍት ሲናገር የመዳን መሰረት እንደሆኑ ፤ በያዙትም የህይወት ቃል ጥምን ሁሉ የሚያረኩ እንደሆኑ ፤ እግዚአብሔርን ለመምሰል ዶግማዊ መሰረት እንደሆኑ (for the Doctrine of Godliness) ፤ በነዚህም ላይ ማንም እንዳይጨምርና እንዳይቀንስም ያዛል። ይህም ብቻ ሳይሆን በዚሁ ንግግሩ መሀል በሚገርም ሁኔታ ማቲ 22፤29ና ዮሐ 5:39 በመጥቀስ ኢየሱስ "መፅሀፍት" (scripture) በማለት ሰዱቃውያንን ሲወቅስ የገለፀው ከላይ እሱ እያወራላቸው ያሉትን መፅሀፍት መሆኑን በሚናገር አውድ ይገልፃል። በዚህ ንግግሩ ምንም ተጨማሪ ማብራሪያ እስከማያስፈልገው ድረስ ያለምንም ጥርጥር ቀኖና እያለ የገለፀው ቀጥታ የመለኮት እስትንፋስ ያላቸው መፅሀፍትን እንደሆነ እንረዳለን ፤ ሁለቱንም ሀሳብ ያለመነጣጠል ነው ገልፆ ያስቀመጣቸውና።

ከዚህም በመቀጠል ቀኖናዊ ስላልሆኑ ነገር ግን ሊነበቡ የሚገቡ እንዲሁም በክርስትና አዲስ ለሆኑ የሚውሉ መፅሀፍት በማለት ይዘረዝራል። እነዚህንም የተናገረው አንባቢዎቹ የበለጠ እርግጠኝነትና እውቀት እንዲኖራቸው በማሰብ በስተመጨረሻ የጨመረው ናቸው። አትናቴዎስ በቅዳሴ ሰአት የሚነበቡትን መፅሀፍት ብቻ ከሆነ የመዘርዘር የፈለገው ግልፅ ባለ መልኩ ማስቀመጥ ሲችል በዚህ መልኩ ያስቀምጣል ብሎ ማሰቡም ራሱን የቻህ ስሜት ማይሰጥ ነገር ነው።

በዚህ ላይ የእየሩሳሌሙን ቄርሎስ ጨምረን መመልከት እንችላለን። ቄርሎስ ወደ ዝርዝሩ ከመግባቱ በፊት ሰፋ ያለ መክፈቻ ስለመፅሀፍቱ ይሰጣል። አቀማመጡም በሚያስገርም መልኩ ከሰባሊቃናቱ በመነሳት ነበር። የግብፅ ሀገር ግዝ የነበረው ቶለሚ በፍልስጤም ላሉ አይሁዳውያን መፅሀፍትን እንዲተረጉሙለት እንደጠየቃቸው ሰባሁለትም ሊቃናት ወደእርሱ በመሄድ እንደተረጎሙ ያስቀምጣል። በሚተረጉሙበት ጊዜም የአምላክ እስትንፋስ የሆኑትን መፅሀፍት ለማወቅ በማሰብ እያንዳንዱን ተርጓሚ ለየብቻቸው እንዲተረጉሙ እንዳደረገና በስተመጨረሻም ትርጓሜያቸው እርስ በእርሱ ሲነፃፀር የቃላት ወጥነት ሳይቀር ሙሉ ለሙሉ ተመሳሳይ ሆነው እንደተገኙ ፤ እነርሱም ደግሞ በርግጥ ቅዱሳት መፅሀፍት እንደሆኑ ይናገራል። ታድያ እነዚህ ቅዱሳት መፅሀፍት በቁጥር 22 እንደሆኑ ፤ በቤተክርስቲያንም የሚነበቡ መነበባቸውንና በቀደሙ አባቶች እየተላለፉ የወረዱላቸው እንደሆኑ ይናገራል። ይህ የቄርሎስ ግልፅ ማብራሪያ ቀጥሎ ያስቀመጠውን ዝርዝር በቅዳሴ ሰአት የሚነበቡት መፅሀፍት ብቻ ናቸው ብለን እንዳንል የሚያስገድደን ነው። በርግጥም የአምላክ ቃል የሆኑት መፅሀፍት ነውና ያስቀመጠው። በተጨማሪ ቄርሎስ ቤተክርስቲያንን በመወከል ነውና የተናገረው ይህ አቋሙ በጊዜው የነበረበትን ቤተክርስቲያን አቋም ጭምር ሊወክል የሚችል እንደሆነ መገመት እንችላለን።

አጭሩ ለማየት የሞከርነው የቤተክርስቲያን አበው መፅሀፍትን ዘርዝረው ሲያስቀምጡ ብዙ ሳንርቅ በዛው ስፍራ ከሰጡት ማብራሪያ አንፃር እንደምናርጋግጠው እንደተባለው በቅዳሴ ሰአት የሚነበቡትን መፅሃፍት ብቻ የዘረዘሩ አድርገን እንዳንረዳ የሚያደርጉን መሆናቸውን ነው።

ከላይ የቤተክርስቲያንን አበው ዝርዝር በሰፊው እንደተመለከትነው የአብዛኞቹ ወይም ደግሞ የሁሉም የመፅሀፍት ዝርዝር አቀማመጥ በጉባኤያቱና በሐዋርያት ቀኖና ከተቀመጡት ዝርዝር ጋር የሚነፃፀሩ ናቸው። ከ7ቱ መፅሀፍት በተካተቱት ላይ የተለመደው ልዩነትና አለመጣጣም መኖሩ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም። ለምሳሌ የአትናቴዎስን ዝርዝር ብንመለከት ከ7ቱ መፅሀፍት ሁለት መፅሀፍትን ብቻ እነርሱም የባርክና የተረፈ ኤርምያስን መፅሀፍ ያካትታል። ይህን ከሮሙም ይሁን ከካርቴጁ ጉባኤ ጋር ስናነፃፅረው ሙሉ ለሙሉ የማይገኝ ነው። ነገር ግን በሌሎቹ መፅሃፍት ተነፃፃሪነት አለው። የእየሩሳሌሙ ቄርሎስ ስንመለከት ከ7ቱ መፅሀፍት ሶስት እነሱም እዝራ ሱቱኤል ፤ ባሮክና ተረፈ ኤርምያስን ያካትታል። በዚህም ከሮሙም ይሁን ከካርቴጁ ጉባኤ ጋር አይጣጣምም። በሌሎቹ መፅሀፍት ግን ሙሉ ለሙሉ ተነፃፃሪነት አለው። በአበው ዝርዝር ውስጥ ከ7ቱ መፅሀፍት የተካተቱ መፅሀፍት በጉባኤያት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ አልያ ከአንድ መፅሀፍ በዘለለ አልተካተቱም። ይህ ትልቅ የሚነግረን ነገር የአበውን ዝርዝር ከላይ እንደተባለው በቅዳሴ ሰአት የሚነበቡ መፅሀፍት ዝርዝር ብቻ ነው ብለን ብናስብ በዚህ ውስጥ የተካተቱ መፅሀፍት በቅዱሳት መፅሀፍት ዝርዝር ውስጥ አለመገኘታቸው ይህን እሳቤ የሚያስጥል ነው።

ስለዚህ ከላይ ከቀረበውን ሙግት ጋር ተስማምተንኳ የቤተክርስቲያን አበው በተናጥል ዝርዝራቸው ውስጥ ያስቀመጡት መፅሀፍት እንደተባለው ቀኖናዊ የሆኑ ቅዱሳት መፅሀፍትን እየዘረዘሩ ካልሆነና 7ቱን መፅሀፍት ያላካካቱተበት ምክንያት በቤተክርስቲያን ውስጥ በቅዳሴ ሰአት የሚነበቡት መፅሀፍት ለመዘርዘር በማሰባቸው ከሆነ ቀጥታ አፊዎተ አምላክ የሆኑ ቅዱሳት መፅሀፍት በተቀመጡበት የጉባኤያት ዝርዝር ስለምን እነዚህ መፅሀፍት በሙሉነት አልተዘረዘሩም ፤ ስለምንስ በጉባኤያቱ ዝርዝር ውስጥ በተካተቱት እጅግ ጥቂት መፅሀፍት በራሱ ወጥነት አለመኖር ይታያል የሚልን ወሳኝ ጥያቄ ያስነሳል።

የአበውን ዝርዝር ቀጥታ የአምላክ ቃል አድርገን ብንመለከት በተለያዩ ስራዎቻቸው ከሚታዩ አጠቃቀማቸው አንፃር ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ከ7ቱን መፅሀፍት ውስጥ የአምላክ ቃል በማድረግ ተጠቅመዋቸዋልና ቅዱሳት መፅሀፍትነታቸውን ከተቀበሉ ለምን በዝርዝራቸው ውስጥ አላስገቧቸውም የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ከዚህም በመነሳት ነው ከላይ የቀረበው ሙግት የአበውን ዝርዝር በቅዳሴ ሰአት የሚነበቡ በማድረግ ለማጣጣም የሞከረው። ነገር ግን ከላይ እንዳየነው ይህ እሳቤ እንዳለ ሆኖ በሌላኛው ጎን ደግሞ ቅዱሳት መፅሀፍትን ለመዘርዘራቸው የሚሆን በቂ ምክንያት እንዳለ አይተናል።

ቀደም ብለን በጉባኤያት ፤ በአበው ዝርዝርና አጠቃቀም ያለውን ወጥነት አለመኖር እንደተመለከትነው ምንጮቹን እርስ በእርስ በምናነፃፅርበት ጊዜም የበለጠ አለመጣጣምና ውዝግብ እናገኛለን። ምንምኳ የአበው ዝርዝር ከተመለከትናቸው የተለያዩ መንገዶች አንፃር በአምላክ እስትንፋስነታቸው መሆኑን ቢመሰክሩም በራሳቸው አጠቃቀሞች ውስጥ ደግሞ ከዚህ ጋር አለመጣጣም ይታያል። ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ የአበውን ዝርዝር ከአጠቃቀማቸው አንፃር አይተን በሙግቱ እንደቀረበው አይነት እሳቤ ብንይዝ ከላይ በሰፊው የተመለከትናቸውን ቅራኔዎች ከጀርባው ይዞ የሚመጣ ነው። ይህ በ7ቱ መፅሀፍት ላይ በሁለቱም በኩል ብንሄድ ያለ ወጥነት መታጣትና ውዝግብ አሁንም ወደ አንድ ድምዳሜ እንድንደርስ የሚያስችለን አይደለም።

የሚነሱ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

በመቀጠል 7ቱን መፅሀፍት የአምላክ ቃል አርገን መቀበል አለብን ፤ 66ቱ ሙሉ አይደለም! የሚሉ ወገኖች ለዚህ ሀሳባቸው ማፅደቂያነት እንደጥያቄ የሚያነሷቸውን የተለያዩ ክፍሎች እናብራራለን።

1. ይሁዳ 1 : 4-15

“ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ፦ እነሆ፥ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ፥ በኃጢአተኝነትም ስላደረጉት ስለ ኃጢአተኛ ሥራቸው ሁሉ ዓመፀኞችም ኃጢአተኞች በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩ ስለ ጭከና ነገር ሁሉ ኃጢአተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለእነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ።”

ይሁዳ 1፥14-15

በዚህ ክፍል ላይ ይሁዳ ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ የተናገረውን ትንቢት ጠቅሶ(citation) ተጠቅሞ አልፎበታል። ኦርቶዶክስ ወገኖች ይህን ክፍል በመያዝ በእጃቸው ላይ ያለውን የሄኖክን መፅሀፍ የአምላክ እስትንፋስነት ለማስረገጥ እንደማስረጃ ይጠቀሙታል። ከሁሉ ቀደም ብለን በእጃችን ላይ ስላለው ፤ 'የሄኖክ-መፅሀፍ'ም ተብሎ ስለተሰየመው መፅሀፍ ማወቅ ያለብን ነገር አለና እሱን እናስቀድም።

የሄኖክ መፅሀፍ በአምስት ክፍል የሚከፈል ሲሆን በአጠቃላይ ወደ 108 የሚደርሱ ምዕራፎች አሉት። እጅግ ጥንታዊው ክፍል (the Book of the Watchers) ከ3 እስከ 2 bc century ድረስ የሚገመት እድሜ ሲኖረው የመጨረሻው ገፋ ያለ እድሜ ያለው ደግሞ (the book of parables) እስከ 100bc-100ad የሚደርስ ነው። መፅሀፈ ሄኖክ Pseudepigrapha ከሚባሉት የመፅሀፍት ዝርዝር ውስጥ የተመደበ መፅሀፍ ነው። pseudepigrapha ማለት በሌሎች ሰዎች ስም የግል ስራዎችን መሠየም ነው። ይህም ማለት መፅሀፈ ሄኖክ ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛው የሆነው ያ ሄኖክ የፃፈው መፅሀፍ ሳይሆን ከ2nd እስከ 100ad century ድረስ በነበሩ በተለያዩ ሰዎች ተፅፎ በሄኖክ ስም የተሰየመ መፅሀፍ ነው ማለት ነው። በዚህ ጊዜያት ደግሞ ይህ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ብዙ መፅሀፍትም በቅዱሳን ስም ይፃፉ ነበር። ስለዚህ ይሁዳ ከአዳም ሰባተኛ የሆነው ሄኖክ ከፃፈው መፅሀፍ ነው የጠቀሰው ብለን የምንልበት ምንም አይነት ማስረጃ የለም ማለት ነው! ይህ ከመጀመሪያው ሙሉ የሙግት ሀሳቡን የሚያከሽፍ ነው!

ከዚህ በዘለለ እንግዲህ ይህ መፅሀፍ በውስጡም ብዙ ከመፅሀፍቅዱስ ጋር የሚጋጭ ታሪካዊና አስተምህሯዊ ስህተትን የያዘ መፅሀፍ ነው! በሚገርም ሁኔታ በጠቅላላው በአለማችን ላይ ከኢትዮጲያ የኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን ውጪ የሄኖክን መፅሀፍ የአምላክ እስትንፋስ አርጋ የምትቀበል አንድም ቤተክርስቲያን የለችም!

አንዳንዶች ይህ መፅሐፍ በሙት ባህር [በDead see scroll] በመገኘቱ ምክንያት የአምላክ እስትንፋስ አርገው ለመቀበላቸው እንደ ማስረጃነት ያቀርቡታል። ነገር ግን ይህ irrelevant የሆነ እጅግ የወረደ ሙግት ነው! ምክንያቱም በሙት ባህር መፅሀፍቅዱሳዊ ይዘት ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ የሌላቸውም ሌሎች ብዙ ጥቅሎችና ቁርጥራጮች ተገኝተዋልና! ስለዚህ በዚህ መሀል በመገኘቱ ብቻ የአምላክ ቃል ነው ወደሚል ድምዳሜ መድረስ አይቻልም። ይህ ከክርስቶስ ልደት በፊት በአይሁዳውያን ዘንድ የነበረ መፅሀፍ መሆኑን የሚያስረግጥ ብቻ ነው! ከዚህ ጋር በተያያዘም ፦ አይሁዳውያን በታሪካቸው በጭራሽ ይህን መፅሀፍ የአምላክ ቃል አርገው አለመቀበላቸው ፤ ተቀብለውም እንደሚያውቁ አንድም ማስረጃ አለመኖሩ ሙግተ ሀሳቡን የሚያፈርስ ቀጣዩ

ነጥብ ነው! በተጨማሪም በሰባሊቃናቱም ይሁን በMasoretic text ውስጥም ጭራሽ አልተካተተም። እንግዲህ በባለቤቶቹም ጭምር የተመሠከረ እውነት ነው ማለት ነው።

እንግዲህ ዋናው መነሻችን የሆነው ሀሳብ "ይሁዳ ጠቅሶታልና ይህን መፅሀፍ የአምላክ እስትንፋስ አርገን መቀበል አለብን" የሚል ሙግት ነው። ይህ እጅግ አግባብነት የሌለው ሙግት ነው! ምክንያቱም መጠቀሱ ብቻ ወዲህ ድምዳሜ እንድንደርስ ስለማያደርገን ነው። ለመጥቀስ ለመጥቀስ ሉቃስ በሐዋርያት ስራ እንዲሁም ጳውሎስ በቲቶ ላይ ከሌሎች የአለም ሰዎች ፅሁፍ ጠቅሰው ተጠቅመዋል ፥ ነገር ግን ይህ ፅሁፎቹን የአምላክ ቃል አላደረጋቸውም። ምናልባት ይሁዳ "ትንቢትን ተናገረ" በማለቱ ምክንያት ታድያ ይህ የእግዚአብሔር መልእክት ስለመሆኑ አያረጋግጥም ወይ የሚል ሊኖር ይችላል። ነገር ግን ሲጀመር ይሁዳ "በሄኖክ መፅሀፍ እንደተፃፈ" ብሎ ወይም "እንዲህ ተብሎ እንደተፃፈ" በማለት መፅሀፉን አልጠቀሰም ይልቁኑ ራሱኑ ሄኖክን ትንቢት ተናገረ በማለት ማስቀመጥን ነው የመረጠው። ስለዚህ ግዴታ (necessarily) ዛሬ ከያዝነው መፅሀፍ ጠቅሷል ብሎ ለመደምደም የሚያስደርስ ሙሉ ድፍረት የለንም። ም/ቱም ይሁዳ በመንፈስቅዱስ ምሪት ስለሆነ የሚፅፈው በመንፈስቅዱስ ተገልጦለት አስቀምጦት ሊሆን ስለሚችልም! በሌላ እይታ ደግሞ ማንኛውም ፀሀፊ የሚፅፈውን ሀሳብ የሚያፀድቅ ትክክል የሆነን ነገር በማይቀበለው መፅሀፍ ውስጥ ቢያገኝ እንደሚጠቅሰው ሁሉ ፤ ነገር ግን ይህ ማለት ያ ፀሀፊ ፦ የጠቀሰውን ሙሉ መፅሀፍ እንደተቀበለው እንደማያስረግጠው.. ይሁዳም ጠቅሷል ቢባልኳ በመንፈስቅዱስ ምሪት በተናጥል ከዚህ መፅሀፍ ውስጥ ይህን እውነት አውጥቶ እንዳስቀመጠልን ብቻጂ መቀበል ያለብን ፤ በግልፅ ባልተቀመጠና ማስረጃ የለሽ በሆነ ነገር ተመስርተን ሙሉ መፅሀፉን ይቀበለው ነበር ወደ ሚል ድምዳሜ መድረስ አንችልም። ከሁሉ በላይ ደግሞ ይሁዳ አይሁዳዊ እንደመሆኑ በአይሁዳውያንም ባህልና እምነት ውስጥ እንደማደጉ ፥ በነሱ በአይሁዳውያን ዘንድም ይሁን በሐዋርያቱ እንደ የአምላክ እስትንፋስ ተቀባይነት ያልነበረውን መፅሀፍ እሱ ተነጥሎ ተቀብሎ ነበር ማለት ታሪክን እርስበእርስ ማፋለስ ነው! ከዚህም በዘለለ ከጥቂት የቤተክርስቲያን አባቶች በስተቀር ብዙሀኑ የቤተክርስቲያን አባቶች ይህን መፅሀፍ አልተቀበሉትም!

2 ማቲዎስ 27:9

“በዚያን ጊዜ በነቢዩ በኤርምያስ የተባለው፦ ከእስራኤል ልጆችም አንዳንዶቹ የገመቱትን፥ የተገመተውን ዋጋ ሠላሳ ብር ያዙ፥”

— ማቴዎስ 27፥9

አርቶዶክስና ካቶሊክ ወንድሞቻችን ይህን ክፍል በመያዝ ማቲዎስ በዚህ ክፍል የጠቀሰው የኤርሚያስ ትንቢት በ66ቱ ውስጥ የለም! የአምላክ እስትንፋስ 66ቱ ብቻ ናቸው የምትሉ ከሆነ ማቲዎስ ከየት አምጥቶ ጠቀሰው? የሚል ጥያቄ ያነሳሉ! ጥያቄአቸው ተገቢ ነው! ነገር ግን ይህ እነሱ ወደደረሱበት ድምዳሜ አያስደርስም! ምክንያቱም መልሱ በራሱ በ66 ውስጥ ስለሚገኝ!

የዚህን ጠያቄ መልስ ለመረዳት ቀደም ብለን መረዳት ያለብን ነገር አለ! አይሁዳውያን በባህላቸው ለመግለፅ የፈለጉትን ሀሳብ ከሁለትና ከዛ በላይ ከሆነ ክፍል አዋቅረው የማስቀመጥ ልማድ አላቸው። ከዚያም በኋላ ያስቀመጡትን ሀሳብ የጠቀሱበትን ክፍል ሲያሰፍሩ በሁሉም መፅሀፍ ስም ሳይሆን የሚሰሙት በአብይ ነብያት (Major Prophet)ስም ነው። በዛ ጊዜ መፅሀፍት የነበሩት በጥቅል መልክ ስለነበርና በነሱም ባህላዊ መፅሀፍ አቀማመጥ መሠረት ብዙ ጥቅልሎች በአንድነት ስለሚቀመጡ የሚጠቅሱበት መፅሀፍና የጠቀሱትን ክፍል የሚሰይሙበት ስም ሊለያይ ይችላል። ለመረዳት እንዳይቸግረን ለአብነት ያህል ጥቂት የዚህ አይነት ክፍሎችን ልጥቀስ።

- ምሳሌ 1

“ እነሆ፥ መንገድህን የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ተብሎ በነቢዩ በኢሳይያስ እንደ ተጻፈ፥ ”

ማርቆስ 1፥2-3

ምንምኳ ማርቆስ ሙሉ ክፍሉን በነብዩ ኢሳይያስ ቢሰይምም ፤ ጥቅሱ ግን የሁለት ክፍሎች ውቅር ውጤት ነው። ይህም የመጀመሪያው "እነሆ፥ መንገድህን የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ" የተሰኘው አረፍተነገር ከሚልክያስ 3፡1 የተወሰደ ነው።

“ እነሆ፥ መልእክተኛዬን እልካለሁ፥ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል፤ እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል፤ የምትወዱትም የቃል ኪዳን መልእክተኛ፥ እነሆ፥ ይመጣል፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።”

ሚልክያስ 3፥1

ቀጣዩ ሀሳብ ደግሞ ከኢሳይያስ 40:3 የተወሰደ ነው!

ኢሳይያስ 40

3 የአዋጅ ነጋሪ ቃል፦ የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም ጐዳና በበረሀ አስተካክሉ።

ስለዚህ ማርቆስ ሀሳቡን ከሁለት የትንቢት መፅሀፍት አዋህዶ አስቀመጠና ሙሉ ክፍሉን ግን የሰየመው የሚልክያስን ትኖ አብይ ነብይ በሆነው በኢሳይያስ ነው። ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ልስጥ።

- ምሳሌ 2

“ በኤርምያስም አፍ የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል የተነገረው፦ ምድሪቱ ሰንበትን በማድረግዋ እስክታርፍ ድረስ በተፈታችበትም ዘመን ሁሉ፥ ሰባ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ፥ ሰንበትን አገኘች። ”

2 ዜና 36፥21

በዚህ ክፍል የተቀመጠው ሙሉ ሀሳብ በኤርምያስ የተነገረ እንደሆነ የተገለፀ ቢሆንም ነገር ግን ሙሉው ሀሳብ በኤርሚያስ ብቻ አይገኝም! ይህም ሁለት የመፅሐፍቅዱስ ክፍሎች ተዋቅረው የተቀመጠ ነው! ምድሪቱ ሰንበትን እንደምታደርግና በተፈታችበት ዘመንም እንደምታርፍ የተገለፀው ሀሳብ የተወሰደው ከዘሌዋውያን 26 ነው።

ዘሌዋውያን 26

34 በዚያም በተፈታችበት ዘመን ሁሉ እናንተም በጠላቶቻችሁ ምድር ሳላችሁ፥ ምድሪቱ ሰንበት በማድረግዋ ትደሰታለች፤ በዚያም ጊዜ ምድሪቱ ታርፋለች፥ ሰንበትንም በማድረግዋ ትደሰታለች። "

ቀጥሎ ያለው ሰባ አመት እስኪያልቅ እንዳረፉ ሰንበትንም እንዳገኙ የተገለፀው ደግሞ የተወሰደው ከኤርምያስ 29 ነው። ለዚህም ነው በኤርምያስ የተነገረው ቃል የተባለው።

“እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፦ ሰባው ዓመት በባቢሎን በተፈጸመ ጊዜ እጐበኛችኋለሁ፥ ወደዚህም ስፍራ እመልሳችሁ ዘንድ መልካሚቱን ቃሌን እፈጽምላችኋለሁ።”

ኤርምያስ 29፥10

ከነዚህ ግልፅ እውነቶች መረዳት እንደሚቻለው ከተለያዩ ክፍሎች ሀሳብን በመውሰድ መግለፅ በመፅሀፍቅዱሳችን ፀሀፊያኖች የተለመደ ነው። ወደ መነሻችንም ስንመለስ መልሱ ልክ እንደዚሁ ነው! ማቲዎስ በ27ተኛ ምዕራፉ በ9ነኛው ቁጥር ላይ ያስቀመጠው ጥቅስ ሙሉ ለሙሉ ከኤርምያስ የተወሰደ ሳይሆን በዘካርያስ 11፡12 ላይና በኤርምያስ 32:6-8 ፤ 19:1- 13 ላይ የሚገኘውን ሀሳብ በማዋሀድ የተቀመጠ ነው። በኤርምያስም የተሰየመበት ምክንያት አብይ ነብይ ስለሆነ ነው።

“እኔም፦ ደስ ብሎአችሁ እንደ ሆነ ዋጋዬን ስጡኝ፤ ያለዚያ ግን ተዉት አልሁ። እነርሱም ለዋጋዬ ሠላሳ ብር መዘኑ።”

ዘካርያስ 11፥12

ስለዚህ ማቲዎስ በአይሁዳውያንም ይሁን በሐዋርያቱ ዘንድ ተቀባይነተ ያልነበረውን መፅሀፍ አልጠቀሰም። በሚገርም ሁኔታ ይህን እውነት እኛ ብቻ ሳንሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ ራሱ መስክራለች! ይህም በ1879 የታተመው የአዲስ ኪዳን መፅሀፍ ቅዱስ ሕዳግ ላይ ፤ በቀዳማዊ ሀይለስላሴ የአዲስ ኪዳን መፅሀፍ ሕዳግ ላይና ከሁሉም በይበልጥ ደግሞ በ2000 እትሙ የ81 መፅሀፍ ሕዳግ ላይ ማቲዎስ 27:9 ከዘካርያስና ከኤርምያስ የተወሰደ እንደሆነ ተቀምጧል!

3 የቃየን ሚስት ከየት መጣች ?

የአምላክ እስትንፋስ መፅሀፍት 66ቱ ብቻ አይደሉም ብለው የሚያምኑ ካቶሊክና ኦርቶዶክስ ወገኖቻችን 7ቱን መፅሀፍ ለማፅደቅ አዘውትረው የሚጠይቁት ሌላው ጥያቄ በዘፍጥረት 4 ላይ የቃየን ሚስት ከየት መጣች የሚለውን ነው። ይህ ጥያቄ ቀለል ያለና ግልፅ መልስ ያለው ሲሆን ለዚህም ከመፅሀፍቅዱስ ማለትም ከ66ቱ ሳንወጣ ምንመልሰው ነው።

በመጀመሪያ ይህ ጥያቄ የሚነሳው የመፅሀፍቅዱስን የአፃፃፍ አይነት ካለመረዳት ነው። በመፅሀፍቅዱስ እያንዳንዱ ነገር በተናጥል ተብራርቶ አልተቀመጠም። በጠቅላላው መታወቅ ያለባቸውን ነገሮች ነካ ነካ በማድረግ ፤ ወሳኝና አስፈላጊ የሆኑ ክፍሎችን ደግሞ በስፋት ዘርዘር ተደርጎ የተቀመጠ ነው። ለምሳሌ ሲጀምርኳ "እግዚአብሔርም ሰማይና ምድርን ፈጠረ! " ብሎ አጭርና ቀጭን በሆነ አረፍተነገር ነው ሚጀምረው። ይህ እግዚአብሔር ስለ ሰራው ስራ ከመንገሩ በፊት ስለሰሪው ማንነት ማብራሪያ ሰቶን አስተዋቆን አይደለም ሚጀመረው። ቀጥሎም በተዘረዘሩት የፍጥረታት ዝርዝር ውስጥ በየቀኑ የተከናወነውን ነገር ልናውቅ የሚገባንን ያህል አጠር አጠር አርጎ ዘርዝሮ ያልፋል። ልክ እንደ ሰው አፈጣጠር ደግሞ ያሉትን በድጋሜ ሙሉ ምዕራፍ ሰቶ በስፋት ያብራራል። በአጭሩ ሚያስፈልጉን እውነቶች ብቻ በመንፈስቅዱስ አማካኝነት የተካተቱበት ነው። ይህን ስንረዳ ለምን አልጠቀሰም or አልተናገረም ብለን ለመውቀስ ልንነሳ አለመቻላችንን እንገነዘባለን!

ለጥያቄው መልስ ለማግኘት መጀመሪያ አዳምና ሄዋን ከቃየንና ከአቤል በተጨማሪ ሌሎች ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንደወለዱ ማወቅ ግድ ይለናል።

“አዳምም ሴትን ከወለደ በኋላ የኖረው ሰባት መቶ ዓመት ሆነ፤ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ።”

ዘፍጥረት 5፥4

ምንምኳ ግልፅ ቢሆንም ቀጥለን መረዳት ያለብን ደግሞ የአለማችን ህዝብ ሙሉ ለሙሉ የተቀዳው ከአንድ እንደሆነ ነው! ይህም ከአዳምና ሄዋን!

“ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደ ሆነ፥ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ ፥ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው። ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም።”

ሐዋርያት ስራ 17፥26-27

“አዳምም ለሚስቱ ሔዋን ብሎ ስም አወጣ፥ የሕያዋን ሁሉ እናት ናትና።”

ዘፍጥረት 3፥20

እንግዲህ የሰው ዘር ሁሉ ከአዳምና ከሄዋን የተቀዳ እንደሆነ እርግጥ ከሆነ ፤ ቀጥሎም አዳምና ሄዋንም ብዙ ልጆችን ከወለዱ አንድና አንድ ልጆቻቸው ልጆችን የወለዱት እርስ በእርስ በመጋባት ነው ማለት ነው። ስለዚህ በቀላሉ የቃየን ሚስት አዳምና ሄዋን ከወለዷቸው ልጆች ውስጥ አንዷ ናት ማለት ነው!

ምናልባት ይህ ሲባል እንዴት ቃየን እህቱን ያገባል? እግዚአብሔር በሕጉ አልከለከለም ወይ የሚል ሊኖር ይችላል! ይህም ቀላል ነው! ሕጉ በሙሴ በኩል እስኪመጣ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ሕግ አልነበረም! አልተከለከለምም![73] በዚያ ጊዜ የቅርብ ዘመድን ማግባትና መውለድ ሁሉም የሚያደርጉት የተለመደ ነገር ነበር! ለአብነት ያህል ትንሽ ልጥቀስ!

1 የአብርሀም ሚስት የአባቱ ልጅ ናት! (Half-sister)

“እርስዋም ደግሞ በእውነት እኅቴ ናት፤ የእናቴ ልጅ አይደለችም እንጂ የአባቴ ልጅ ናት፤ ለእኔም ሚስት ሆነች።”

- ዘፍጥረት 20፥12

2 የአብርሀም ልጅ ይስሀቅ ያጎቱን ልጅ (cousin) ነው ያገባው!

“ነገር ግን ወደ አገሬና ወደ ተወላጆቼ ትሄዳለህ፥ ለልጄ ለይስሐቅም ሚስትን ትወስድለታለህ።”

- ዘፍጥረት 24:4

“ይህን መናገሩንም ሳይፈጽም እነሆ፥ ሚልካ የወለደችው የባቱኤል ልጅ ርብቃ እንስራዋን በጫንቃዋ ተሸክማ ወጣች፤ ሚልካም የአብርሃም ወንድም የናኮር ሚስት ናት።”

- ዘፍጥረት 24፥15

3 የይሰሀቅ ልጅ ያዕቆብ ያገባው ያጎቱን ሁለት ሴት ልጆች ነው!

“ተነሣና ወደ እናትህ አባት ወደ ባቱኤል ቤት ወደ ሁለቱ ወንዞች መካከል ሂድ፤ ከዚያም ከእናትህ ወንድም ከላባ ሴቶች ልጆች ሚስትን አግባ።”

- ዘፍጥረት 28:2

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ ግልፅ ማስረጃ በኋላ የቃየን ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ አይገባም! በተጨማሪም "እንዴት እህቱን ሊያገባ ይችላል?" ለሚለው ጥያቄ በተረፈ ባሮክ ላይም ይህው እውነት ተቀምጦ ይገኛል።

"በስደስተኛው ሱባዔ ልጁን ኣራን ወለዳት ቃየንም እህቱ ኣዋን ሚስት ትሆነው ዘንድ አገባት በአራተኛውም ኢዮቤልዩ መጨረሻ ኢኖንን ወለደችለት።"

- ተረፈ ባሮክ 5÷1

"ለሚወጣ ሁሉ በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት።"

— 2ኛ ዮሐንስ 1÷9

"Whosoever transgresseth, and abideth not in the doctrine of Christ, hath not God. He that abideth in the doctrine of Christ, he hath both the Father and the Son."

— 2 John 1÷9
